# የባሕረ ሐሳብ እወጃ ፎክሎርነት

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ኤም.ኤ.ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ሔኖክ ያሬድ ፈንታ

S ABABA UNIVERSITY
I.S LIBRARY

ሰኔ 2000 ዓ.ም.

# የባሕረ ሐሳብ እወጃ ፎክሎርነት

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ኤም.ኤ.ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ
ሔኖክ ያሬድ ፈንታ

አማካሪ
አባ ዳንኤል አሰፋ (ዶክተር)

ሰኔ 2000 ዓ.ም

# አበርክቶ

- በዘመናችን የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ህልው እንዲሆን ላስቻሉት ለአባቴ ለአለቃ ያሬድ ፈንታ፣
- በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት የባሕረ ሐሳብ ትምህርት አጋጥሞት ከነበረው አደጋ መጻሕፍቱንና ዕውቀቱን ይዘው ለተሰደዱትና ለትውልደ ትውልድ ላስተላለፉት እጨጌ አበሞ (ወርቁን ቅሞ አፉን ጠቅሞ የተባለላቸው)፣
- የኢትዮጵያን ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው የአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመት ዘመን የትመጣ በጥልቅ ጥናት ላዘጋጁት ለአለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ

# አጠቃሎ

በኢትዮጵያ በየዓመቱ የአዲስ ዓመት መባቻ ለመቀበል ከሚደረጉት ክብረ በዓላት አንዱ በሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓት የሚከበረው ቅዱስ ዮሐንስ ርእሰ ዐውደ ዓመት ነው::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያዎች በቅኔ ማሕሌትና በዐውደ ምሕረት በሚኖረው ሥነ ሥርዓት ከትንሣኤ ጋር የተያያዙ የየዘመኑ አጽዋማትና በዓላት የሚታወቁበት፣ የባሕረ ሐሳብ እወጃና ዘመኑ መለወጡ የሚበሰርበት መንገድ ፎክሎርነት ያለው መሆኑ ጥናቱ ያሳያል:: ይህ «የባሕረ ሐሳብ እወጃ ፎክሎርነት» በሚል ርእስ የቀረበው ጥናት መሠረት ያደረገው በ1999 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ማኅደረ ሰብሐት ቅድስት ልደታ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን የአከባበር ሥነ ሥርዓት ነው::

የባሕረ ሐሳብ ሥርዓታዊ ብያኔ፣ የዘመን መለወጫው ልዩ ልዩ መጠሪያዎች እንዴትነት፣ የበዓሉ ትእምርቶችና ውክልናቸው፣ የወራትና ቀናት ስያሜ ፎክሎሪዊ መሠረት ታትቶበታል::

የባሕረ ሐሳብ እወጃው ከፎክሎር ዐበይት ተግባራት አኳያ ተመዝዝው የሚወጡ ቁምነገሮችን ጥናቱ አግኝቷል::

# ምሕፃረ ቃል

ዓ.ም. = ዓመተ ምሕረት

ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ የሚቈጥር የኢትዮጵያ አቈጣጠር

ዓ.እ. = ዓመተ እግዚእ (የጌታ ዓመት)

በምዕራባውያን (ጎርጎርዮሳዊ፣ ዩልዮሳዊ) አቈጣጠር ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ የሚቈጥር

ዓ.ዓ. = ዓመተ ዓለም

ከአዳም ፍጥረት ጀምሮ የሚቈጥር የኢትዮጵያ አቈጣጠር

ዓ.ቀኃሥ = ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከነገሡበት 1923 ዓ.ም. ጀምሮ የሚቈጥር፣ የመጻሕፍት የኅትመት ዘመን ሲጠቀስበት የኖረ፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## ማውጫ


ርእስ ገጽ

አበርክቶ

አኰቴት

አጠቃሎ

ምሕፃረ ቃል

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

አጠቃላይ ዳራ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .. 1

1.1 የጥናቱ አኪያሄድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ..1

1.1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት . . . . . . . . . . . . . . . . . .. . . 1

1.1.2 የጥናቱ ዓላማ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .. 2

1.1.3 የጥናቱ ትኩረትና ወሰን . . . . . . . . . . . . . . . . . .. 4

1.1.4 የአጠናን ዘዴ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

1.1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

1.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

1.2.1 የታተሙ ሥራዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6

1.2.2 ያልታተሙ ሥራዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 12

1.3 የፎክሎር ምንነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .15

ምዕራፍ ሁለት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 17

ከባሕረ ሐሳብ ወደ ባሕረ ሐሳብ እወጃ. . . . . . . . . . . . . . . ... . 17

2.1 ባሕረ ሐሳብ ምንድን ነው ? . . . . . . . . . . . . . . . . . .. 17

2.2 የኢትዮጵያ ሐሳበ ዘመን መነሻ . . . . . . . . . . . . . . . . 18

2.2.1 የዕለታት ስያሜ መነሻ . . . . . . . . . . . . . . . . . . ..21

2.2.2 የወራት ስያሜ መነሻ . . . . . . . . . . . . . . . . . ... 23

2.3 የቀመር መነሻ (የኢትዮጵያ ዓመታት መነሻ). . . . . . . . . . . .. 26

ምዕራፍ ሦስት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 29

የባሕረ ሐሳብ እወጃ ክብረ በዓሉ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . 29


ADDIS ABABA UNIVERSITY I.L.S LIBRARY

3.1 የባሕረ ሐሳብ እወጃ ምንድን ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 29
3.2 የክብረ በዓል ምንነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 29
3.3 የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ ልዩ ልዩ መጠሪያዎች እንዴትነት . . . . . . . . 33
3.4 የርእሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ አከባበር . . . . . . . . . . . . . . . . . 36
3.5 በባሕረ ሐሳብ እወጃ ሰዓት የሚደረጉ ክዋኔዎች . . . . . . . . . . . . . . 41
3.6 የባሕረ ሐሳብ እወጃ ከሮክለር ተግባራት አኳያ . . . . . . . . . . . . . . . .45

ምዕራፍ አራት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 49
የርእሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ በዓል ትእምርቶች . . . . . . . . . . . . . . 49
4.1 የትእምርት ምንነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 49
4.2 በባሕረ ሐሳብ እወጃ ላይ የሚታዩ ትእምርቶችና ውክልነታቸው. . . . . . . . 49
ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .. 55
ይሁንታ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .. 56
ስምዓት (ቢብሊዮግራፊ) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 58
አባሪ

- የ1999 ዓ.ም. የባሕረ ሐሳብ እወጃ ሙሉ ቃል
- የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ትረካ
- መረጃ አቀባዮች

# ምዕራፍ አንድ

# አጠቃላይ ዳራ

የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ ክብረ በዓልን ተከትሎ የሚመጣውና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመባቻው ዕለት የሚካሄደው የባሕረ ሐሳብ አዋጅ ፎክሎርነት የሚያሳየው ጥናት የሚካሄድበት አቀጣጫ በዚህ ምዕራፍ ቀርቧል።

"ሳንቃ ሳይከፈት ጓዳ አይገባም" ነውና ለጥናቱ መንደርደሪያ የሚሆነውን ልዩ ልዩ ክፍል የሚጠቁም ስለሆነ በአጠቃላይ ዳራነት ከእዚህ ተጽፏል። ስለጥናቱ ፍኖት አኪያሄድ መረጃ በሚሰጠው የመጀመሪያ ክፍል ስለጥናቱ ርእሰ ጉዳይና የሚቀርብበት ዘዴ ጥናቱን ለማድረግ ስለአነሳሳው ምክንያትና አስተነባበሩ ያለውን ሂደት ያመለክታል።

በሁለተኛው ክፍልም በጥናቱ ዙሪያ ስለተደረጉ ጥናቶች የሚደረገው የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ስለ ፎክሎር ምንነትም በሦስተኛው ክፍል ይቀርባል።

## 1.1 የጥናቱ አኪያሄድ

### 1.1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ኢትዮጵያ ካላት ልዩ ልዩ የባህል መገለጫዎች አንደኛው የዘመን አቈጣጠር ስልት ነው። ይህም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ሐሳብ ተብሎ ይጠራል። አሮጌ ዓመት አልፎ አዲስ ሲመጣ በመስከረም መባቻ በየቤተ ክርስቲያኑ የቅኔ ማሕሌት ወይም ዐውደ ምሕረት ዘመኑ ይታወጃል፤ በዓመቱ ውስጥ ተዘዋዋሪ አጽዋማትና በዓላት የሚገቡበትና የሚውሉበት ዕለት ይነገራል።

ስለ ሥነ ፍጥረት በስድስቱ ዕለታት ስለተፈጠሩ ፍጥረታት፣ ስለ አዳምና ሔዋን ፍዳ ቃላዊ ተረክ ይቀርባል። እወጃውና ትረካው በተመረጠው ካህን በቃል የሚፈፀም ሲሆን ክዋኔ አለው፤ በቁሳዊ ባህልም ይገለጻል።

ምእመናንና ካህናት ዓመት ጠብቀው የሚከታተሉት የመስከረም መባቻ የባሕረ ሐሳብ አዋጅና አሥርቆት ፎክሎራዊ ገጽታ እያለው እስካሁን በጥናት አልተዳሰሰም።

በመሆኑም አጥኚው ይህን የአገር ቅርስ በጥናት ለምን ይፋ አይሆንም ከሚል አስተሳሰብ በመነሳት ላጠናው ወደድኩ።

ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቤተኛነቴ ባሻገር በቤተ ክርስቲያኒቱም ሆነ በሌሎች ተቋማት ብዙም የጥናትም ሆነ የትምህርት ትኩረት ያላገኘውን ባሕረ ሐሳብ ትውፊቱና ትምህርቱ ከቅድመ አያቴ፣ አያቴና አባቴ ሲተላለፍልኝ የተቀበልኩት ነው። በአሥራዎቹ መጨረሻ ዕድሜዬ ቤቴ ውስጥ የዘመን መቁጠሪያ፣ ቀለንቶን[1] (ካላንደር) አጥቼ በምነጫነጭበት ጊዜ አባቴ «ና!፣ ብርዕ እና ወረቀት ይዘህ ቁጭ በልና የምነግርህን አስላ» ብለው በቃል ስሌት የምፈልገውን ቀን ዕለት ለማወቅ ቻልሁ፤ ትምህርቱም ባሕረ ሐሳብ እንደሚባል ተገነዘብኩ። ከዚያን ዘመን ጀምሮ ስለ ባሕረ ሐሳብና ጓዙ ይበልጥ ማወቅ መጓጓቴ አልቀረም።

ከኮሌጅ ትምህርቴ በተጓዳኝ አባቴ ወንበር ዘርግተው ባሕረ ሐሳቡን ለእኔ ማስተማራቸው «ተቀመጥ በወንበሬ ፣ተናገር በከንፈሬ» ብለው ባህላዊ ዕውቀቱን ማስረፃቸው፤ እኔም በፋንታዬ በካፑቺን ፍራንቸስካዊ የነገረ መለኮትና ፍልስፍና ተቋም «የባሕረ ሐሳብ መግቢያ» (Ethiopic Calendar) የአጽዋማትና በዓላት አወጣጥ መንገድ ማስተማሬ ይበልጥ አትግቶኛል። ዘመን የሚቀመርበት፣ ዓመት የሚቈጠርበት መስከረም አንድ ቀን፣ ርእሰ ዐውደ ዓመት በየዓመቱ በየቤተ ክርስቲያኑ በመገኘት፣ በተለይ በአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት በመዘዋወር ባሕረ ሐሳብ ሲታወጅ ያለውን ሥርዓት በመቅረጸ ድምፅ በመቅረጽ ሳዳምጥ ኖሬያለሁ። የድኅረ ምረቃ ትምህርት በፎክሎር ዘርፍ መከታተል መጀመሬና ዕውቀት ማግኘቴ የባሕረ ሐሳብን ፎክሎርነት ለማጥናት አነሳስቶኛል።

### 1.1.2. የጥናቱ ዓላማ

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከማኅበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር የተገናዘቡ የእምነትና አምልኮ ሥርዓቶች ይገኛሉ። እነዚህ ሥርዓቶች ከፎክሎር ጋር የተያያዙ ሆነውም ይገኛሉ። ከነዚህም መገለጫዎች አንዱ የዘመን መለወጫ በዓል አከባበር ውስጥ ያለው ሥርዓት ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱን ማኅበረሰብ በፎክሎር መረዳት፣ መገንዘብ ይቻላል። ማኅበረሰቡ የራሱ የሆኑት መገለጫዎች እምነቱንና አኗኗሩን የሚጠቁሙ

[1] ካሌንደር መነሻው ከጽርዕና (ግሪክ) ሮማይስጥ ካሌንዶ ሆኖ ፍቺ መባቻ፣ የወር መጀመርያ ማለት ነው። በኪዳነ ወልድ ክፍሌ "ቀለንቶን" ተብሎ ተጠቅሷል። በግእዝ ድርሳናት ቃሉ ለመኖሩ ከሚያሳዩት መካከል ተረፈ ቄርሎስ ይጠቀሳል (1948፣794)።

ናቸው። እነርሱንም እንዴት እንደጀመሩቸው፣ እንዴትስ እንደተጠቀሙባቸውና በሒደት ያሳየው ለውጥም የሚታይበት ነው።

ማኅበረሰቡ ዘመን በተለወጠ ቁጥር ዓመታቱን የሚቀበልበት ሥርዓት አለው። ይህን ፎክሎር ጠቀስ የሆነውን ሥርዓት መፈተሽ የጥናቱ ትኩረትና ዓላማ ነው።

«ባሕረ ሐሳብ» የተሰኘው የቤተ ክርስቲያኒቱ ብሎም የአገሪቱ እሴት የትመጣውን ይመለከታል። በመስከረም መባቻ የባሕረ ሐሳብ አዋጅና አሥርቆት ፎክሎራዊ ገጽታ እንደሌሎቹ የፎክሎር ቅርሶች በወጉ ለመዳሰስ እንዲቻልና መልካም በረከት ለማትረፍ ጥናቱ ቀጥለው የተመለከቱት አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ይዟል።

አጠቃላይ ዓላማ

ከመነሻው እንደተገለጸው ትውፊታዊውን ባሕረ ሐሳብ ምንነቱን፣ የባሕሉን ቅርሱንና የዕውቀቱን ገጽታ ማሳየት፣ እውቅናም እንዲያገኝ መጠቆም ይሆናል።

ዝርዝር ዓላማ

- ከባሕረ ሐሳብ እወጃና አሥርቆት ጋር የተያያዙ ሥነ ቃሎች ትውፊቱን፣ ክዋኔውን፣ ቁሳዊ ባህሉን መሰብሰብ፣ መለየት የትመጣውን መመርመር።
- «ቅዱስ ዮሐንስ፣ ርእሰ ዐውደ ዓመት» ተብሎ በቤተ ክርስቲያኒቱ የሚታወቀውን ስያሜ በዕለቱ በዐውደ ምሕረት ወይም በቅኔ ማሕሌት የሚደረገውን አጠቃላይ ሥርዓትና ሒደት፣ ዐውዱንና ክዋኔውን በቪዲዮና በቴፕሪከርደር መቅረጽ፣ በፎቶግራፍም በማንሳት እንዲታወቁ ማድረግ።
- የቅዱስ ዮሐንስ ርእሰ ዐውደ ዓመት ክብረ በዓል የአከባበር ሁኔታ በየዘመኑ ያሳየውን ልዩነት ለማሳየት መሞከር፤ ለዚህም አበውን ከመጠየቅ ሌላ አጥኚው ከ1988 ዓ.ም ወዲህ በተለያዩ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት ባደረገው ስንድ ቅኝት አማካይነት ልዩነት ማሳየት።
- ኅብረተሰቡ (ምእመኑ) ለክብረ በዓላዊ እወጃ የሚሰጠውን ግምት ማሳየት ይሆናል።

ጥናቱ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል::

- ✓ በባሕረ ሐሳብ ውስጥ ፎክሎርነት እንዴት ይገለፃል?
- ✓ የእወጃው ፎክሎራዊ ተግባራት ምን መልክ አላቸው?
- ✓ በአዲስ ዓመት መባቻ ቅዱስ ዮሐንስ አከባበርና የሥነ ሥርዓቱ መንፈሳዊና ባህላዊ ገጽታ ትእምርት ምን ይመስላል?
- ✓ የዕለታት፣ የወራትና የዓመታት ስያሜ መሠረት ምንድን ነው?

### 1.1.3. የጥናቱ ትኩረትና ወሰን

ጥናቱ በዋናነት ትኩረት ያደረገው በአዲስ የዘመን መለወጫ ዕለት በተለይም በቤተ ክርስቲያን የአቆጣጠር መሠረት ያለውን የእወጃና ክዋኔ ሒደትና ትእምርቱን ማሳየት ነው:: በመስከረም መባቻ ያለውን ዓለማዊ የአከባበር ሥርዓትና በርሱ ላይ የተመሠረቱ ባህላዊ ጨዋታዎችን ግን አይመለከትም:: ጥናቱ በተለይ መስከረም 1 ቀን 1999 ዓ.ም በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ቤተ ክርስቲያን የተደረገውን በዓላዊ ሥርዓት ይመለከታል:: ከፎክሎር መሠረተ ሐሳቦች አንፃር ይፈትሻል::

### 1.1.4. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በመስክ ሥራና በአብያተ መጻሕፍት የሚደገፍ ይሆናል:: አጥኚው በመስክ ሥራው በሁለቱ የአጠናን ዘዴዎች፣ በቃለ መጠይቅና በምልከታ መረጃዎችን አሰባስቧል::

በመስክ በዓመቱ መባቻ የተደረገውን የባሕረ ሐሳብ እወጃ ክዋኔውን ከባለ አዋጁ እና አድማጩ ጋር ያለውን ሁኔታ በመመልከት መረጃዎች በቴፕሪከርደር፣ በቪዲዮ ካሜራ የቀረፀ ሲሆን በፎቶግራፍም አንስቷል::

### 1.1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

"ባህል የሰው ልጅ ሰብአዊና ምክንያታዊ ፍጡር እንዲሆን ካስቻሉት ሀብቶች አንዱ እንደሆነ" በ1995 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ባህል ፖሊሲ ይጠቁማል::

ኢትዮጵያ ካሏት ልዩ ልዩ ባህሎች አንደኛው ከሌላው ዓለም የለያትን የዘመን አቈጣጠር ስልት መያዟ እንደሆነ በመግቢያው ተጠቅሷል:: በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ባሕረ ሐሳብ ተብሎ የሚታወቀው ሥርዓት የአገሪቱም ሆነ የኅብረተሰቡ አተያይና አኗኗር ውጤት ነው። ይህን ውጤት በአግባቡ ጠብቆ ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ፣ እውቅናም ያገኝ ዘንድ ማሰብ ይገባል።

የጥናቱ አስፈላጊነት አንዱ ከዚህ ይነሳል። የአቈጣጠሩ አነሳስ ወይም አጀማመር በተለይ ቀመር ከአጽዋማትና በዓላት ጋር ያለው መስተጋብር፣ ሁዳዴና ፋሲካ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ሥፍራ፣ በዓመቱ መባቻ በርእሰ ዐውደ ዓመቱ "ሁዳዴ (ዐቢይ ጾም) መቼ ይያዛል? ፋሲካ (ትንሣኤ) መቼ ይውላል? የሚለውን ለማወቅና ተጓዳኝ ተረኮችን ለመስማት ምእመኑ በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ለመገኘት ይጓጓል።

ስለሆነም የጥናቱን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ በነዚህ ሦስት ነጥቦች መግለጽ ይቻላል።

(ሀ) ጥናቱ ለአገሪቱ የፎክሎር ጥናት፣ ለባህል፣ ለሥነ ሰብእ (አንትሮፖሎጂ) እና ለሥነ ጽሑፍ አጥኚዎች አስተዋጽዖ ይኖረዋል።

(ለ) የቤተ ክርስቲያኒቱን የዘመን አዋጅና አሥርቆት ቃላዊ ጥበብ ለማቆየት ወደፊት ለሚደረግ ቀጣይ ጥናት ጠቀሜታ ያስገኛል።

(ሐ) በባሕልና ቱሪዝም መስክ ስለተለያዩ ክብረ በዓላት ከመነገር፣ ከመዘከር ውጪ ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የባሕረ ሐሳብ አዋጅና ክዋኔ ተጠንቶ የቀረበ የጎላ ነገር አጥኚው አላጋጠመውም። በመገናኛ ብዙኀንም አጥኚው እስከሚያውቀው ድረስ (በውስጡም በሙያው ስላለበት) ላለፈው ሩብ ምእት ዓመት ተገልጾም አያውቅም።

ስለዚህ ጥናቱ የክብረ በዓሉን ገጽታ በቪዲዮና በቴፕሪከርደርና በፎቶግራፍ አስደግፎ ስለሚያቀርብ በማስተዋወቅ ረገድ ጠቀሜታ እንደሚሰጥ ይታመናል።

## 1.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

አጥኚው ከሚሠራው "የባሕረ ሐሳብ እወጃ ፎክሎርነት ገጽታ" ጋር የሚዛመድ ጥናት እንዳለ ቅኝት አድርጓል። ይሁን እንጂ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ጥናት ባያገጥመውም በመጻሕፍትና በምርምር ድርሳናት በተያያዥ የቀረቡ ቁምነገሮችን ተመልክቶአል። ከኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ አከባበር ጋር ተያይዞ ስለሚገኘውና የዘመን

ቆጠራው ምንጭ ስለሆነው ባሕረ ሐሳብም የተጠቀሱ ጽሑፎች መኖራቸው አልቀረም:: በዚህ ንኡስ ምዕራፍ የታተሙትና ያልታተሙት ሥራዎች ይዳሰሳሉ::

### 1.2.1. የታተሙ ሥራዎች

ስለኢትዮጵያ ደንበኛ የዘመን አቈጣጠር ትውፊታዊ ቀመር የሚያወሱ በተለያዩ ቋንቋዎች የተጻፉ መጻሕፍት አሉ:: በዚህ ዳሰሳ በዋናነት አጥኚው የሚመለከተው ከጥናቱ ጋር የሚቀራረቡትን ብቻ ይሆናል:: አንደኛው ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በ1993 ዓ.ም በአሜሪካ ሚኒሶታ (ኮሌጅቪል)፣ *ባሕረ ሐሳብ-የዘመን ቈጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋር* በሚል ርእስ ያሳተሙት መጽሐፍ ነው::

መጽሐፉ የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ዘዴ የባሕረ ሐሳብ ታሪክና ይዘት መሠረታዊ ትምህርቱን፣ ስለ ዕለታትና ወራት ዓመታትም ስያሜዎች መነሻ ይገልጻል:: በአዲስ ዓመት መባቻ ስለሚደረገው የዘመን አዋጅ ገጽታ ያወሳል:: በሥነ ሥርዓቱ ላይ የሚነገረውን ተረክ ሁሉ አስፍሯል:: በተለይ የተዘዋዋሪዎቹን አጽዋማትና በዓላት አወጣጥ መንገድ አግኝቷል ስለሚባለው የሦስተኛው ምእት ዓመት ጳጳስ ድሜጥሮስ በቃል የሚተረከውን ጽፎታል:: የብራና መጻሕፍት ስለ ዘመን ጠቀስ ጉዳዮች የሚሉትንና ሰንጠረገሮችንና ስምንቱን አቅጣጫዎች የሚያሳይ ዐውደ መናዝል (ዞዲያክ) ማብራሪያ ባይኖርውም አካትቷል:: ጸሐፊው ትውፊታዊውን ባሕረ ሐሳብ ለዘመኑ ትውልድ በዘመናዊ አቀራረብ ያስተዋወቀበት መንገድ ይጠቀሳል::

መጽሐፉ ለጥናቴ ጠቀሜታ ይኖረዋል:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ቦታ ላይ የተፈጠሩ ዝበቶችንና ለየት (ለወጥ) ያሉ ሐሳቦችን ከመፈተሽ አይመለስም::

ፕሮፌሰር ጌታቸው ባሕረ ሐሳብ ተዘዋዋሪ (ተንቀሳቃሽ) በዓላት የሚውሉበትን፣ አጽዋማት የሚገቡበትን ለማወቅ እንጂ በቋሚነት በየወሩም ሆነ በየዓመቱ የሚከበሩትን በዓላትና አጽዋማት ለማወቅ አያስፈልግም:: የሚል አስተሳሰብ በጽሑፋቸው ገጽ 8 አስተጋብተዋል::

እርሳቸው መስከረም 1 ቀን ከሚታወጀው የተዘዋዋሪ በዓላት ጋር ባሕረ ሐሳብ በጠባቡ መመልከታቸው ነው ችግሩ:: ቋሚ በዓላትን ለማወቅ መቼ እንደሚውሉ ዕለቱን ለመግለጽ ባሕረ ሐሳብ መሣርያ ነው::

ባሕረ ሐሳብ ሁሉንም በዓላት ይመለከታል። ከጠባቡ ፍች ስንወጣ የሚያሳየን እርሱን ነው። ለምሳሌ ልደት (ገና) ቋሚ በዓል ነው። ከገና አስቀድሞ ተያያዥነት ያላቸው ስብከት፣ ኖላዊ ወዘተ የሚገኙት ከጥንተ ቀመር በመነሳት ነው።

ከተዘዋዋሪው አጽዋማት መካከል ጾመ ሐዋርያት የመፍቻው ቀን ከሌሎቹ በተለየ መልኩ ቋሚ ነው። ምንጊዜም ጾሙ ሲያዝ ይዘዋወራል። ሲፈታ ግን ሁሌም ሐምሌ 5 ነው። ይህም በመሆኑ በመውጣትና በመውረድ ጊዜ (ኢየዓርግና ኢይወርድ) የጾሙ ቀኖች ከ13 ቀናት እስከ 43 ይዘልቃል።

ስለዚህ ባሕረ ሐሳብ ለሁሉም መሠረት ነው። ሁለተኛው ነጥብ ስያሜን የተመለከተ ነው። እንዲህ ይላል «የዘመን አቈጣጠርን ዘዴ በኛ ሀገር ባሕረ ሐሳብ ('የሐሳብ' ወይም 'የሒሳብ ባሕር') ይሉታል። መርሐ ዕውርም ይባላል። «የዕውር መመሪያ» «ዕውርን የሚመራ» ማለት ነው። ለምን መርሐ ዕውር እንዳለት አላውቅም።» (ገጽ 19)

በባሕረ ሐሳብ ከሚታዩት ችግሮች አንዱ የስያሜ ጉዳይ ነው። ባሕረ ሐሳብ፣ መርሐ ዕውር፣ አቡሻክር፣ ሐሳበ ዘመን ሁሉም አንዳይነት ናቸው የሚል አስተሳሰብ የሚያንፀባርቁ አሉ። የጌታቸው መጽሐፍም አንዱ ነው። በባሕረ ሐሳብ ዙርያ የግእዝ የተጻፉ ድርሳናት በቅጡ አለመታየታቸው፣ የባሕረ ሐሳብ ተጠያቂ ሊቃውንት አለመጠየቃቸው ነው እንጂ ስያሜዎቹ ልዩነትና ትስስርም አላቸው።

«መርሐ ዕውር» ዘይቤ ነው። ካለማወቅ ድንቁርና ወደማወቅ ዕውቀት የሚመራ የተዘዋዋሪ አጽዋማትና በዓላት አወጣጥ መንገድን የሚያሳይ፣ ሰንጠረዥ ያለው ነው። ባሕረ ሐሳብ ግን መርሐ ዕውርንም ይዞ ሌሎች ሐሳባትን ያካተተ ነው።

አቈጣጠሩ አቡሻክር ተብሎም ይጠራል የሚል አስተሳሰብ የሚያራምዱም አሉ። ጌታቸው፣ «ዘዴውን (ለሁለተኛ ወይም ለሦስተኛ) ጊዜ ያገኘነውና እኛ ያስፋፋ ነው። በ13ኛ ምእት ዓመት የኖረ አቡሻክር የሚባል አንድ የግብፅ ዲያቆን በዐረብኛ ካቀነባበረው ባሕረ ሐሳብ ስለሆነ ራሱን አቈጣጠሩንም አቡሻክር እንለዋለን» (ገጽ 19) ብሏል።

የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር «አቡሻክር» ነው የሚል አስተሳሰብ ተገቢ አይደለም። አለቦታው የገባ ነው። አቡሻክር የሚታወቅበት ዐቢይ ሥራው በስሙ የተጠራውን ባለ59 ምዕራፎች መጽሐፍ ማዘጋጀቱ ነው። ከምዕራፎቹ ውስጥ ስምንት የሚሆኑት ከዘመን ጋር የተያያዙ ሌሎቹ ከታሪክ ጋር የተዛመዱ ናቸው። ይኸ መጽሐፍ ወደ ግእዝ የተተረጐመው በ16ኛው ክፍለ ዘመን ነው። ከጨረቃ ዑደት ጋር የተያያዙ

ነጥቦችን የያዘ በመሆኑ «ሐሳበ አቡሻክር» ተብሎ ከባሕረ ሐሳብ አንድ ክፍል ሆኖ ይታያል እንጂ መላውን ባሕረ ሐሳብ የሚይዝ አይደለም፡፡ አቡሻክር (አቡሻህር) ታላቅ ስመ ጥር የቁጥር መጽሐፍ ብዙ ወግ ታሪክ ያለበት ነው፡፡ (ኪ.ወክ፣ 1948፣ 195)፡፡

አቡሻክርን የዘመን አቈጣጠር የሚል ስያሜ በስህተት የተሰጠው በ1962 ዓ.ም. በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አማካይነት የታተመው «አቡሻክር» ነው፡፡ መጽሐፉ በግእዙ ውስጥ ያሉትን 59 ምዕራፎች አርእስት ያስተዋውቃል እንጂ እንዳለ አላቀረበውም፡፡ በአቡሻክር ውስጥ የሌለውን የአጽዋማት በዓላት ማውጫ ሰንጠረዥ ከ1962-2480 ዓ.ም. ተዘጋጅቶለታል፡፡ አቶ ኒኅባር የኢትዮጵያን አቈጣጠር አቡሻክር ነው የሚለው አስተሳሰብ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በማነፃፀር ይገልጻል፡፡

ፕሮፌሰር ጌታቸው ያነሱት ሌላው ነጥብ ዕለተ ምጽአትን የተመለከተ ነው፡፡ «ካባቴ መጻሕፍት አንዱ እስከ 1950 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ዓመታት ውስጥ የበዓላቱንና የአጽዋማቱን ዕለታት እንደሚያሳይ አስታውሳለሁ፡፡ አባቴ እንደነገረኝ እስከ 1950 ዓ.ም. ባለው ዘመን ውስጥ የበዓላቱንና የአጽዋማቱን ዕለታት ያወጣልን መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት የእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ድሜጥሮስ ነው፡፡»

በሦስተኛው ምእተ ዓመት የነበረው ድሜጥሮስ የበዓላት ማውጪያ ሐሳብ አበቅቴ ማግኘቱ እሙን ነው፡፡ መሠረታዊው የአወጣጥ መንገዱን በማሳየት አንድ ዐውደ አበቅቴ መሥርቶ ያሳየ በመሆኑ ተከታዮቹ በየዘመኑ እየተቀባበሉ ሠርተውታል እንጂ እርሱ እስከ 1950 ዓ.ም. ድረስ ያለውን አዘጋጅቷል የሚል ጽሑፍ ድርሳናት አልተመዘገበም፡፡

ባሕረ ሐሳብን የሚያውቅና መጻሕፍቱን ያነበበ የዐውድ መነሻና መድረሻ በአዕዋዳት እንደተመለከተው በማቴዎስ ዐውደ ጳጉሜን አንደኛ ተነሥቶ በዮሐንስ አራተኛ ያበቃል፡፡ 1950 ዓ.ም. ወንጌላዊው ማርቆስ የዐውደ ጳጉሜን ሁለተኛ ነበር፡፡ በትምህርቱ ምጽአት የሚጠረጠረው በዐውደ ቀመር የ532 ዓመት ዑደት ማብቂያ ላይ ነው፡፡ ይህም 1948 ዓ.ም. ነበር፡፡ በወቅቱ ጥርጣሬና ፍርሀት አድሮ እንደነበር መ/ር ያሬድ ያስታውሳሉ፡፡

ኢትዮጵያ የጨረቃ አቈጣጠሯን መተዋን የሚገልጽ ክፍልም አለ፡፡ ጌታቸው እንዲህ ይላሉ «እኛም ብንሆን በጨረቃ መቁጠሩን ብንተወውም ስሙን አልተውነውም፡፡ ወራችን በጨረቃ ሂደት ባንለካም» (1993፣ 34) ብለዋል፡፡

ይህም አያስኬድም፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አቈጣጠር ፀሐያዊውንም ሆነ የጨረቃውንም እንዲሁም የሁለቱ ጥምር አቆጣጠር ትከተላለች። በተግባርም ታውለዋለች።

ወሮቻችንን በጨረቃ ሂደት፣ በሠርቀ ሌሊትም እንለካለን። በባሕረ ሐሳብ እወጃ ጊዜ ካህኑ ሲያሠርቁ ይጠቀሙበታል። በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት በየዓመቱ እየታተመ በሚወጣው ተንጠልጣይ ቀለንቶን (ካሌንደር) ከመደበኛው ከቈጣጠር ሌላ የጨረቃና የሠርቀ ሌሊት ቀመርም ይዞ ይወጣል።

«እኛ ክርስቲያኖች ዓመቱን በጨረቃ ወራት ስለማንከፍል ለጨረቃ ወራት ስም የለንም። ኑሮንም እንደሆነ አላቆየነውም» (ገጽ 37) የሚል ጽሑፍም አስፍረዋል።

የወራት ስያሜው መደበኛውን ይዞ የጨረቃ መስከረም እያለ ይዘልቃል። ለምሳሌ በዐውደ አበቅቴ መነሻ 354 ቀን የያዘው የጨረቃ ዓመት የሚያበቃው ነሐሴ 24 ቀን ነው። ነሐሴ 25 የጨረቃ አዲስ ዓመት የጨረቃ መስከረም ተብሎ ይብታል። (ያሬድ 1993 ዓ.ም.)

መጽሐፉ ለዘመን ቈጠራ የማይጠቅሙ፣ ለባሕረ ሐሳብ ማውጫ የማያስፈልጉ በማለት ከዘረዘራቸው ዐውደ ሰንበት (133 ዓመት)፣ ዐውደ ፀሐይ (28 ዓመት) ይገኝ ብታል። (ገጽ 72) ይሄም የተዛባ ነው (ሱባኤ) ዋናው ዐውድ የ532 ዓመቱ ዐውደ ቀመር ለአራቱ ወንጌላውያን እኩል 133 ዓመት ደርሷቸው ይመረታል። አንድ ዘመን በየትኛው ሰንበተ ወንጌላዊና ዓመተ ወንጌላዊ እንደሚገኝ ለማወቅ የሚረዳና አስፈላጊ ሐሳብ ነው።

ዐውደ ፀሐይም የዓመት መባቻን ለማወቅ፣ በፀሐይና በጨረቃ ጥምር አቆጣጠር የተገኘውን የአይሁድ ፋሲካ፣ ከአይሁድ ፋሲካ ቀጥሎ በሚውለው እሑድ የሚገኘው ትንሣኤ ለማወቅ እጅግ አስፈላጊው ሐሳብ ነው። ዐውደ ፀሐይ ከሌለ መባቻው መቼ እንደሚውል እንዴት ይታወቃል?

ፕሮፌሰሩ «ከመስከረም 1 ቀን እሑድ ዕለት መዋለን መምህሩ እንዴት ያውቃል? ለምን አያውቀውም ያለው እኮ ጳጉሜን ወር ነው። ጳጉሜ እስከታልቅ ያሉትን ቀናት በጣት ቈጥሮም ቢሆን ማግኘት አያስቸግርም» (ገጽ 80) ይላሉ። በመቈጠር ብቻ ሳይሆን ሳይንሳዊ የሆነ ማረጋገጫ ዐውደ ፀሐይን በመጠቀም ማረጋገጥ ይቻላል።

ሌላው ስህተት በመጽሐፉ ምዕራፍ 2 «የባሕረ ሐሳብ አወጣጥ» በሚለው ስለተለያዩ ሐሳባት ስለ ቢዘን፣ ጉንዳጉንዲና ሳቤላ ሲዘረዝር ቁጥሮቹን ማዛባቱ ነው።

ከአዳም እስከ ክርስቶስ የነበረው ዘመን 5500፣ በሐሳበ ሳቤላ 5481 ዓመት የሆነውን 4481 ዓመት ማለቱ፣ በሐሳበ ቢዘን 5272 የሆነውን 4272 ዓመት ማለቱ፣ በሐሳበ ጉንዳጉንዲ 5044 የሆነውን 4265 ዓመት ማለቱ ለስህተትና ዝበት ዳርጎታል፡፡ ደብረ ቢዘንን ቢዛንታይን ነው ማለታቸውም (ገጽ 54) ስህተት ነው፡፡

በባሕረ ሐሳብ እወጃ ጊዜ በካህኑ የሚተረከው ቃል ተረክ በመጽሐፉ በመገኘቱ ካሁኑ ጋር ለማነፃፀርም ይረዳል፡፡ የሚያመሳስል ነገርም አለው፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸው ቃል ተረኩን በጽሑፍ ያሰፈሩት ሲሆን ይህ ጥናት ግን በቪዲዮ በቴፕና በፎቶግራፍ ከነዐውዱ ጭምር ስለሚያቀርብ ይለያል፡፡

ሁለተኛው መጽሐፍ የመሠረት ስብሐት ለአብ ነው፡፡ በ1981 ዓ.ም ሆንግ ኮንግ የታተመ ሲሆን፣ መጠሪያውም *ትውፊታዊ ኅሳበ ዘመንና ታሪኩ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አቋም* ይሰኛል፡፡ ጸሐፊው ባሕረ ሐሳብ ተብሎ ስለሚታወቀው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ጥንተ ታሪክ፣ ይዘታና መነሻ፣ በጥንታዊው የሐሳበ ዘመን ይዘታ የኢትዮጵያ ድርሻ ምን እንደሚመስል፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው 5500 ዓመት ነው የሚለውን ኢትዮጵያዊ ቀመር ትውፊታዊ አመጣጥ ይዘረዝራሉ፡፡ የአቆጣጠሩ ልዩ ልዩ ስያሜዎችና የአዲስ ዓመት ርእሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ ስለመባሉ መንስዔም ያትታሉ፡፡ "ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገሮች የተቀበለቻቸው የሚመስሉ የኅሳበ ዘመን ጠቀስ ነባር ባህሎች" ቢኖሩም የራስዋ አበርክቶ የሆኑ እንዳሏት ይጠቅሳሉ፡፡ የመሠረት መጽሐፍ በአጠቃላይ ባሕረ ሐሳቡን፣ በተለይም የአዲስ ዓመት መባቻ ስያሜዎችን የትመጣ በተመለከተ ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ ነው፤ በቦታው ይጠቀሳል፡፡

ከመጽሐፉ የኔ ጥናት የሚለይባቸው ነጥቦች አሉ፡፡ አንደኛውና ቀዳሚው የዘመን መለወጫ ዕለት በቤተ ክርስቲያን የሚደረገውን የባሕረ ሐሳብ እወጃና ክዋኔና ዐውዱን ይዘረዝራል፡፡ ፎክሎርነቱን ገጽታውን ይመረምራል፡፡ በፎቶግራፍ፣ በቪዲዮና በቴፕሪከርደር አስደግፎ ያቀርባል፡፡

በተለያዩ ዓመታት በተካሄዱ ሁለት ዐውደ ጥናቶች ላይ ያሬድ ፊንታ (1986 ዓ.ም) እና ዳንኤል ሰይፈሚካኤል (1994 ዓ.ም) ባሕረ ሐሳብን በተመለከተ ያቀረቧቸውና በስንኙት (ፕሮሲዲንግስ) የታተሙ ጥናቶች አጥኚው ተመልክቷል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ያሬድ፣ «ባሕረ ሐሳብ» በሚል ርእስ ያቀረቡት ጥናት ስለ ባሕረ ሐሳብ ትምህርት ምንነት «መርሐ ዕውር» እና «አቡሻክር» በማለት እንደሚከፈል ገልጸዋል። አቡሻክር ሙፃአ ፀሐይ (የፀሐይ መውጣትን)፣ ምሕዋረ ከዋክብትን (ከዋክብት ጉዞ) የጨረቃ ብርሃን ምልዐትና ሕፀፅን (ጉድለት) የሚያስተምር መጽሐፍ መሆኑ፣ መርሐ ዕውር ደግሞ የአቅማራትን (ቀመሮች) ምሥጢር፣ የአጽዋማትና የበዓላትን ሥርዓት የሚያስረዳ መጽሐፍ መሆኑ፣ የትምህርቱ ምንጭ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ቢገኝም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቁጥር ሊቃውንት እያገናዘቡ ትምህርቱን ማስፋፋታቸው ተገልጿል። ከክርስቶስ ልደት በፊት ስለነበረው 5500 ዓመት መሠረት ከነቢያት ሰባኤ (ኤርምያስ፣ ዳንኤል፣ ሄኖክ፣ ዕዝራ) አኳያ ይተነትናል። የትምህርቱ ስያሜዎች ምንነትና መነሻ መግለጹ ለጥናቴ ማገናዘቢያ ይጠቅመኛል።

ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል «ሐሳበ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን» ብሚል ርእስ ያቀረበው ጽሑፍ ስለ ባሕረ ሐሳብ የሚያነሳ ነጥብ አለው። ስያሜን በተመለከተ በገለጸው አስተሳሰብ ችግር ያለበት መስሎ ይሰማኛል።

እንዲህ ይላል፦ «ሐሳበ ዘመን ወይም አቡሻክር በርካታ ስያሜዎች አሉት። ከእነዚህም ባሕረ ሐሳብ፣ ዘመነ ዓለም፣ መርሐ ዕውር፣ የቁጥር ትምህርት እየተባለ ይጠራል።» (1994፣ 29) የተዘረዘሩት በባሕረ ሐሳብ ውስጥ የሚካተቱ ንኡሳን ክፍሎች ናቸው።

ሌላው የተዛባው ደግሞ የኖረበት ዘመን በውል የማይታወቀው አቡሻክር በኢትዮጵያ ሊቃውንት በመወደዱ የሐሳበ ዘመን መጽሐፉን ዮሐንስ አቡሻክር ብለው ሰየሙት።

እንዲሁም ለምንገለገልበት የዘመናትና የበዓላት የአጽዋማትና የዕለታት ቀመር እንደመነሻ የሚቆጠረው አቡሻክር ነው (ገጽ 30) ይላል። በ13ኛው ክፍለ ዘመን የኖረው ግብፃዊው ዲያቆን አቡሻ ክር ከጨረቃ ዓመት ጋር የሚገናዘብ ሐሳበ አቡሻክርን አደራጀ እንጂ የአጽዋማትና በዓላት የዘመናትን መነሻ ሐሳብ ያመጣ አይደለም። 11 ክፍለ ዘመን ሙሉ የዘመን ሥርዓት አልነበረም ማለት ነው ወደሚለው ይመራል።

ይሁን እንጂ ክርስትና ከባተበት በተለይም ከ4ኛው ምእት ዓመት ወዲህ የባሕረ ሐሳብ ልዩ ልዩ ገጽታዎችና የበዓላት አከባበር ሥርዓት መኖሩ ይታወቃል።

ባሕረ ሐሳብ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ከውስጥና ከውጭ የተገኙ ልዩ ልዩ ሐሳቦችን ያደራጁበት ነው። ድሜጥሮስ የባሕረ ሐሳብ አንዱ ቅርንጫፍ ሐሳበ አበቅቴን ያዘጋጀ እንጂ የኢትዮጵያን ባሕረ ሐሳብ አላቀናበረም።

የስንክሳር የጥቅምት 12 የድሜጥሮስ ምንባብ የግእዙ ዘርዕ «ወእምዝ ሠርዐ ሐሳበ አበቅቴ» (ከዚህ በኋላ አበቅቴ የሚገኝበትን መንገድ አዘጋጀ) የሚለውን ተርጓሚው «ከዚህም በኋላ ባሕረ ሐሳብ የተባለውን የዘመን መቁጠሪያ ሠራ።» (1994፣ 183) ብለው መጻፋቸው አግባብ አይደለም።

### 1.2.2. ያልታተሙ ሥራዎች

ከሁለተኛና ከመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የምርምር ድርሳኖች መካከል ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥታ ተያያዥነት ባይኖራቸውም በተወሰነ መልኩ የሚዛመዱ ሁለት ሥራዎች ተገኝተዋል። የመጀመሪያው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሶሻል አንትሮፖሎጂ ክፍለ ትምህርት በጁን 2003 ዓ.እ (ዓመተ እግዚእ) ዋለልኝ እምሩ አድገህ ያቀረበው ነው። ርእሱ "The Dynamics of Religious Rituals and Secular Ceremonies in Public Places of Addis Ababa (Spatial, Temporal and Symbolic Aspects)" ይሰኛል። ጥናቱ በአዲስ አበባ ከተማ አደባባዮች ስለሚከበሩ የመስቀልና የጥምቀት በዓላት በዋናነት ሲመለከት፣ ለአከባበሩ መነሻ ስለሚሆነው የዘመን አቈጣጠር ስልት ያነሳል። የዘመን መለወጫ የመስከረም አንድ ቀን አከባበርን እግረ መንገዱን ሲጠቅስ በመባቻው በቤተ ክርስቲያን ስለሚደረገው ሥርዓት ያወሳል። ከዚህ ጥናት ጋር በውስን ነጥቦች ይገናኛል። በተሟላ መልኩ ባይገልጸውም በዘመን_መለወጫ ዕለት ስለሚደረገው የአቀባበል ሥርዓትና ስላለው የጊዜ (ዘመን) ጽንሰ ሐሳብ፣ የዐውዶች ዓይነቶች፣ የዕለታትና የወራት ስያሜ መነሻ ይገልጻል።

ጥናቱ ለበዓላት ኹሉ መከበር መነሻ የሚሆነውን ትውፊታዊው አቆጣጠር ሲጠቅስ ባቀረባቸው አንዳንድ ነጥቦች ላይ አጥኚው የማይስማማበት ሁኔታ አለ። የተዛባም ነው ብሎ ያምናል። ዋለልኝ ስለ መስቀልና ጥምቀት በዓላት በጥናቱ ሲገልጽ እግረመንገዱንም ስለኢትዮጵያ ዘመን መባቻ ቈጠራ ያነሳው ነጥብ አለ።

የዓመተ ዓለም ዐቢይ የዘመን አቈጣጠር ከኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ሐሳብና መርሐ ዕውር ተብለው ከሚታወቁት ጽሑፎች የተተረጐሙ ናቸው። ባሕረ ሐሳብም በ240 ዓ.ም. ሰድሜጥሮስ የተጻፈ ነው ይላል (2007፣ 97)።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የኮፕቲክ ያገኘችው ከትንሣኤ ጋር የተዛመዱ በዓላትና አጽዋማት የሚወጡበት የሚገኙበትን የሐሳበ አበቅቴ መንገድ እንጂ መላውን ባሕረ ሐሳብ አይደለም። የዘመን አቈጣጠር ከጥንት ግብፃውያን የፀሐይ አቈጣጠር

መንገድ ጋር ተገናዝቦ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የደራጀ ነው። ዋለልኝ ድሜጥሮስ ባሕረ ሐሳብን ጻፈ ያለው አግባብ አይደለም።

እርሱ የተከተለው መጽሐፍ ስንክሳርን ከግእዝ ወደ አማርኛ የተረጐሙት መምህር በስህተት «ባሕረ ሐሳብ» ብለው የጻፉትን ነው።

ግእዙ «ወእምዝ ሠርዐ ሐሳበ አበቅቴ» የሚለውን «ከዚህም በኋላ ባሕረ ሐሳብ የተባለውን የዘመን መቁጠሪያ ሠራ።» (ላዕከ ማርያም፣ 1994፣ 183) (ሠረዝ የተጨመረ) ድሜጥሮስ ያዘጋጀው ሐሳበ አበቅቴ መሆኑን የሚገልጸውን ባሕረ ሐሳብ መባሉ ነው ስህተቱ።

ባሕረ ሐሳብም ሆነ መርሐ ዕውር ሁለቱም ኢትዮጵያዊ ስም ናቸው። ሊቃውንቱ በየፊናቸው ከውጭም ከሀገር ውስጥም ያገኙትን ልዩ ልዩ ሐሳቦች እያስተባበሩ እያዛመዱ ያዘጋጁት ነው። መርሐ ዕውር የማን ነው? ለሚለው በአፄ ተክለ ሃይማኖት ዘመነ መንግሥት በጎንደር የነበሩት ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ የጻፉት ማብራሪያ ግልጽ ያደርገዋል።

> «መርሐ ዕውር የእስክንድርያ ሊቀጳጳሳት የድሜጥሮስ መጽሐፍ ይሁን እንጂ የሌሎች ጠቢባን ነገር ተጨምሮበታል። ይህም ይታወቅ ዘንድ መርሐ ዕውር እየተባለ በሚጠራ መጽሐፍ ሁሉ ጠቢባን በየራሳቸው ሲጽፉ ቃላቸው አንድ ሆኖ አለመገኘቱ ነው። የአንዱ ቃል ከሌላው ቃል የተለየ ሆኖ ይታያል። አንዱ ይጨምራል። ሌላው ያጎድላል። ስለዚህም መርሐ ዕውራን የተባለ መጽሐፍ ያንዱ የድሜጥሮስ ብቻ ቢሆን ኖሮ ያንዱ መጽሐፍ ቃል ከሌላው ተለይቶ ባልተገኘ ነበር» (መሠረት፣ 1981፣43)።

ሌላው የተዛባው የአዲስ ዓመት ዋዜማ የቅዱስ ሩፋኤል መታሰቢያ ቀን መሆኑን የገለጸበት ነው። (ገጽ 28) በመጽሐፈ ግጻዌ እንደተጻፈው ጳጉሜ 5 የአሞጽ ነቢይ መታሰቢያ እንጂ ሩፋኤል አይደለም። መታሰቢያው ጳጉሜን 3 ዕለቱም ርኅወተ ሰማይ ይባላል። በዕለቱ የሚዘንበው ዝናብ እንደጠበል ይቆጠራል። ወደ አዲስ ዓመት ለመሸጋገር የጳጉሜን 5 ቀናት (በአራት ዓመት 6) ማለዳ ላይ በመነሣት በውሃ የሚታጠቡ (የሚጠመቁ) በተለይ በገጠሩ ወፍ ሳትቀምስ ወንዝ ወርደው የሚለቃለቁ አሉ።

የዕለት ስያሜ አመጣጥ በገለጸበት ሰንጠረዥ ውስጥ መጻሕፍት ከማሉት ውጪ ያለው ነገር አለ። ሦስተኛው ቀን በግእዝ «ሠሉስ» በአማርኛ «ማክሰኞ» ሲባል በዋለልኝ

ግን የማክሰኞ መነሻ የግእዝ ሥርወቃሉ «ምንጋሁ ሰኑይ» ብሏል:: ከምን እንደአገኘው አልጠቀሰውም:: ቅዳሚንም «ተቀዳሚ» ከእሑድ በፊት ብሏል::

የወራት ስያሜንም ሲዘረዝር 13ኛዋን ጳጉሜን ዘሏታል:: ጳጉሜን ተጨማሪ፣ ተውሳክ ማለት እንደሆነ ይታወቃል::

በበዓለ ጥምቀት ጊዜ የታቦተ ሕጉ እና የተሸካሚው ካህን ትእምርትነት በተመለከተ ዋለልኝ ባቀረበው ጥናት ታቦት ሕጉን የተሸከመው ካህን መጥምቁ ዮሐንስን ይወክላል ብሎ ባቀረበው ላይ ሊቃውንቱ አይስማሙም:: በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ታቦተ ሕጉ የክርስቶስ ምሳሌ፣ ታቦቱን የተሸከመው ካህን ደግሞ የጸወርተ መንበር ኪሩቤል ምሳሌ ነው:: (ሰይፈ ሥላሴ፣ ካሴት ቁጥር 2)::

የአጥኚው ሌላው ስህተት የስምንተኛው ሺሕ ማብቂያ ብሎ ያሰፈረው የዓመቱ ቁጥር ነው:: የኢትዮጵያ የዘመን (ጊዜ) ገደብ ከክርስቶስ ልደት በፊት 5500 ዓመት ጀምሮ የሚያበቃው 2509 ዓ.እ. (2501 ዓ.ም.) ነው ይላል (ገጽ 49)::

በኢትዮጵያ የዘመን ይትበሃል ከአዳም ጀምሮ የሚቈጥር «ዓመተ ዓለም» የተሰኘ መስፈርያ አለ:: ክርስቶስ እስከሚወለድበት ዓመት ድረስ የነበረው 5500 ዓመት ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ካለው የዓመተ ምሕረት ቁጥር ጋር እየተደመረ መላው ዓመተ ዓለም (ዓ.ዓ.) ይባላል:: ስምንተኛው ሺሕ የሚያበቃው ዘመኑ 8000 ሲሞላ ነው:: ይህም የሚሆነው ዋለልኝ እንዳለው 2501 ዓ.ም. ሳይሆን 2500 ዓ.ም. ላይ ነው:: (5500 + 2500 = 8000) 2501 ዓ.ም. (8001 ዓ.ዓ) የዘጠነኛው ሺሕ መባቻ ነውና::

ጥናቱ ስለ ባሕረ ሐሳብ አዋጅ ቢያወሳም ስለይዘቱ ስለ ዐውዱና ክዋኔው ባጠቃላይ ስለፎክሎራዊ ጉዳዮች የሚለው ነገር የለም:: የቃል ተረኮቹ አልተጠቀሱም:: በቪዲዮም በቴፕም በፎቶግራፍም አልተደገፈም:: እና ይህ ጥናት በዚህ ይለያል::

ሁለተኛው የምርምር ጽሑፍ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት በ1986 ዓ.ም. ስምለም በቀለ ያቀረበው/ያቀረበችው ነው:: የጥናቱ ርእስ "እንቁጣጣሽ በአዲስ አበባ የልጃገረዶች ዘፈን ይዘት ቅርስና ስነቃላዊ ባህርያት ትንተና" ይሰኛል:: ጥናቱ በአንድ ርእሰ ጉዳይ ብቻ ከዚህ ጥናት ጋር ይዛመዳል:: ይህም ሥነ-ቃላዊ የዘመን መለወጫ ስያሜዎች በሚል የመስከረም አንድ ቀን ልዩ ልዩ መጠሪያዎች መንስዔ መፈተሹ ነው:: ቢሆንም ጥናቱ በምልዐት ያልቀረበ ከመሆኑ ሌላ በዘመነ ዮሐንስና በዕለተ ዮሐንስ (ቅዱስ ዮሐንስ) መካከል ያለውን ልዩነት ባለመረዳትና መረጃን ካለማስተዋል የተፈጠረውን ዝበት ይህ ጥናት ያስተካክላል::

## 1.3 የፎክሎር ምንነት

በሕዝብ አማካይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ማንኛውም ዓይነት እምነት፣ ልማድና ትውፊት (ትራዲሽን) ፎክሎር ይሰኛል። ፎክሎር ከሚባሉት መካከል ፎክቴልስ (ሕዝባዊ ተረቶች)፣ አፈ ታሪኮች (legends) እና ሚቶች (Myths) ይገኙበታል። እንዲሁም ፎክሎር ሥነ ጥበባትን (Arts)፣ ጥበባተ ዕድ (crafts)፣ ዳንኪራዎችን፣ ጨዋታዎችን፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን፣ እንቆቅልሾችን፣ መዝሙሮችን፣ ሱፐርስቲሽንስ (superstitions) እና ዐውደ ዓመትን (holiday) እና ሃይማኖታዊ ክበራዎችን (celebrations) ያካትታል። (ዳንደስ (Dundes) 1994 ዓ.እ. 1922)።

ፎክሎር ከሰው ልጅ ዕድሜ ጋር የተሳሰረ ጥንታዊ ነገርና ባመዛኙ ከሰው ወደ ሰው በቃል የሚተላለፍ ነው። በቀደምት ሕዝቦች ተጽፈው (ተቀርጸው) ለዘመነ ትውልድ ከደረሱት ውስጥ ፎክሎሮች አሉበት። ሰዎች ሥርዓተ ጽሕፈትን በየጊዜው እያዳበሩ ሲመጡ ሕዝባዊ ታሪኮች (folk stories) መጻፍ ጀምረዋል።

በአሁኑ ዘመን የጽሕፈት ቋንቋ የሌላቸው ብዙ ሰዎች ሕዝባዊ ዘፈኖች (folk songs)፣ አፈ ታሪክ (ሌጀንድስ) ሚቶችና ሌሎች የፎክሎር ዓይነቶች አሏቸው። አንዳንዴ ፎክሎር በምሰላ (ኢሚቴሽን) ሲከናወን፣ ለምእት ዓመታት ልጆች የተለያዩ ጨዋታዎችን፣ ገመድ ዝላይ፣ የድንጊያ ጨዋታ የሚማሩት ከታላላቆቻቸው፣ ከእኩዮቻቸው በማየትና በምሰላ ነው። ሰዎች ከአንዱ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ ሲጓዙ ፎክሎራቸውን ይዘው በማምራት ከአዲሱ አካባቢ ጋር ያዛምዱታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ፎክሎር የተባለው ቃል የጥናት ወይም የሙያ መስኩም መጠርያ (ፈቃደ ሆኖ ያገለግሏል 1992፣ 16)። ፎክሎር የሚለውን ስረይ[2] (term) ለመጀመርያ ጊዜ የተጠቀመው ዊልያም ጆን ቶምስ የተባለ እንግሊዛዊ ነው። ከዚያ በፊት እንግሊዝ ሀገር ውስጥ የዳበሩት የጥንታዊ ሕንጻ፣ የጥንታዊ ተረት፣ የጥንታዊ ባህል፣ የጥንታዊ ዘፈን፣ የጥንታዊ መዝገብ ጥናቶች ወዘተ የሚጠሩባቸው ስሞች "ፖፑላር አንቲኩቲስ"፣"ፖፑላር ሊትሬቸር" (Popular antiquitites, Popular literature) ነበር (ፈቃደ 1992፣ 2)።

በቶምስ ደብዳቤ (1846 ዓ.እ.) ውስጥ በፎክሎር ውስጥ ይካተታሉ ተብለው የተዘረዘሩት የነገራት አሠራርና የሰዎች አኳኋን፣ ልማድ፣ በዓላትና ሥነ ሥርዓት፣ እምነትና አምልኮን፣ ዘፈን፣ ምሳሌያዊ ንግግር ወዘተ ናቸው።

በአሜሪካ የፎክሎር ተመራማሪዎች የተሰጡ ልዩ ልዩ ብያኔዎች ዶርሰን በአራት ዐበይት ክፍሎች መድቧቸዋል። እነዚህም በፈቃደ እንደተጻፉት ሥነ ቃል (ኦራል ሊትሬቸር)፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (ፐርፎርሚንግ ፎክ አርትስ)፣ ሀገረ ሰባዊ ልማድ (ሶሻል ፎክ ከስተምስ)፣ ቁሳዊ ባህል (ማቴሪያል ካልቸር) ናቸው (ፈቃደ 1992፣ 10)።

ሥነ ቃል ኦራል ሊትሬቸር ወይም ኦራል ፎክሎር የሚለውን ስያሜ ለመመለስ አገልግሎት ላይ የዋለ ነው። ፈቃደ ዶርሰንን ጠቅሶ እንደገለጸው ኦራል ፎክሎር (ሥነ ቃል) ያነጣጠረው በቃላት አማካይነት በሚፈጠሩት በተረት፣ በሌጀንድ፣ በሚት፣ በቃል

[2] ስረይ፣ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ «የአንድምታ ትርጓሜ በኢትዮጵያ ባህልና ትምህርት» በሚለው ጥናታቸው (1995 ዓ.ም.) 'term' የሚለውን ቃል የተረጐመበት ነው።

ግጥም፣ በምሳሌያዊ ንግግር፣ በእንቆቅልሽ፣በእንካ ሰላንቲያ እና በመሳሰሉት ላይ ያተኮረ ነው (1991፣ 11)።

ዶርሰን ሀገረ ሰባዊ ልማድ ባለው የፎክሎር አንዱ ዘርፍ ውስጥ አራት ዐበይት ነገሮችን የሚያትቱ መጣጥፎች እንደሚገኙ ፊቃደ ይጠቅሳል። እነርሱም "ፌስቲቫልና ክብረ በዓል (ከበራ)" (ፌስቲቫል ኤንድ ሴሌብሬሽንስ)፣ "መዝናኛዎችና ጨዋታዎች" (ሪክሬኤሽንስ ኤንድ ጌምስ)፣ "ሀገረሰባዊ መድኃኒት (ፎክ ሜዲሲን) እና "ሀገረሰባዊ ሃይማኖት" (ፎክ ሪሊጂን) ናቸው (ፊቃደ 1992፣ 13)።

ከላይ ከተዘረዘረው የፎክሎር ምንነት ከኢትዮጵያ ባሕረ ሐሳብ የአዲስ ዓመት መባቻ እወጃ አንጻር ሊፈተሽበት የሚችሉ ነጥቦች በመኖራቸው ጥናቱ በየምዕራፉ ትኩረቶችን መዝዞ ያወጣቸዋል። ያመሰጥራቸዋል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ምዕራፍ ሁለት

## ከባሕረ ሐሳብ ወደ ባሕረ ሐሳብ እወጃ

### 2.1 ባሕረ ሐሳብ ምንድን ነው?

ኢትዮጵያ ካሏት ልዩ ልዩ ባሕሎች አንደኛው የዘመን አቈጣጠር ስልት ነው ። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ሐሳብ በመባል ይታወቃል። በቤተ ክርስቲያኒቱ ነባር ትውፊትና ጥንታዊ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በአምስተኛ ጉባኤነት ተመድቦ ይገኛል[3]። ልዩ ልዩ ጸዋትውም አሉት።

ባሕረ ሐሳብ ቍጥር ያለው ዘመን፣ ዓመተ ዓለም ማለት ነው (ኪዳነ ወልድ፣ 1948፣ 261)። ሐሳብ፤ ሐሰበ፣ ቈጠረ ከሚለው ግስ ሲወጣ በዘመን ከተመሳሰለው ባሕር ጋር ተናብቦ ባሕረ ሐሳብ የተሰኘውን ሥረይ አስገኝቷል ። ሐሳብ ከተለያዩ ሐተታዎች ማለትም ከደራሲ ስምና ከርእሰ ጉዳይ ጋር ተዛምዶ ይቀርባል፤ ይናበባል ። ለምሳሌ ከደራሲ ስም ጋር ሲናበብ ሐሳበ ሄኖክ፣ ሐሳበ ድሜጥሮስ፣ ሐሳበ አቡሻክር ወዘተ ይሰኛል። ከርእሰ ጉዳይም ጋር ሲሄድም ፤ ሐሳበ ዘመን፣ ሐሳበ አበቅቴ፣ ሐሳበ ጾም፣ ሐሳበ ፋሲካ፣ ሐሳበ ቢዘን፣ ሐሳበ ጉንዳጉንዲ ወዘተ ይሆናል። የእነዚህና የሌሎች በርካታ ሐሳቦች የጋራ መጠርያ ባሕረ ሐሳብ ተብሎ ይታወቃል (Neugebauer, 1979: 68-69) ። ከአጽዋማትና በዓላት እንዲሁም ከአቅማራት ጋራ የተያያዙት ሐሳቦችም በተለይ "መርሐ ዕዉር" ተብለው ይጠራሉ (ያሬድ፣ 1994 ዓ.ም.፣ 187)።

ባሕረ ሐሳብን በሁለት መንገድ በሰፊውና በጠባቡ በማለት መበየን ይቻላል። በሰፊው መንገድ ከላይ የተዘረዘረው ሲሆን በጠባቡ ደግሞ በተለይ ትንሣኤን እየተከተሉ ከሚዘዋወሩት አጽዋማትና በዓላት አወጣጥ መንገድ ጋር ይያያዛል።

ባሕረ ሐሳብ ቍጥር ያለው ዘመን ነው ብለናል። ዘመኑ የሚለካበት ደግሞ ምድር ከፀሐይና ከጨረቃ ዑደት ጋር ካላት ግንኙነት የሚነሳ ሆኖ ዘመኑ የሚለካበትም በዕለት፣ በወርና በዓመት ነው።

የዘመን መለኪያዎቹ አዕዋዳት (ዐውዶች) ተብለው ይጠራሉ። የእነዚህ አዕዋዳት ልኬት ተመላላሽ ክስተቶች በሚከሰቱበት ጊዜ ወይም ዘመን ላይ የተመሰረቱ ናቸው። እነሱም ዐውደ ዕለት[4]፣ ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት 7ቀኖች፤ ዐውደ ወርኀ፣ በጨረቃ

---

[3] አምስቱ ጉባኤዎች ብሉያት ፤ሐዲሳት ፤ መነኮሳት ፤ ሊቃውንት ፤ ባሕረ ሐሳብ ናቸው።

[4] በኢትዮጵያ አቈጣጠር የሳምንቱን ዕለታት በተለያዩ መነሻዎች ጥንተ ዕለት፣ ከእሑድ ተነሥቶ እስከ ቅዳሜ፤ ጥንተ ቀመር፣ ከማክሰኞ እስከ ሰኞ፤ ጥንተ ዮን፣ ከሮብ እስከ ማክሰኞ ያሙቱን መባቻ

29/30 ቀን በፀሐይ ዘወትር 30 ቀን፤ ዐውደ ዓመት፣ በጨረቃ 354 ቀን፣ በፀሐይ 365 ቀን ነው፤ ዐውደ ጳጉሜን 4ዓመት፣ ዐውደ አበቅቴ 19 ዓመት፣ ዐውደ ፀሐይ 28 ዓመት፣ ዐውደ ማኅተም 76 ዓመት፣ ዐውደ ቀመር 532 ዓመት ናቸው።

እነዚህ መለኪያዎች በዘመን መለወጫ ዕለት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘመኑ የፋሲካ (ትንሣኤ) በዓልና ከእርሱ ጋር የተያያዙትን ተዘዋዋሪ አጽዋማትና በዓላትን ለማወጅ የሚረዱ ናቸው።

## 2.2 የኢትዮጵያ ሐሳበ ዘመን መነሻ

ደንበኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በፀሐይ ቀመር ላይ የተመሰረተ ነው። ምድር በፀሐይ ዙርያ በምታደርገው የ365 ከሩብ ቀናት ጉዞ አንድ ዓመት ይገኝበታል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በታካይነት በፀሐይና በጨረቃ ጥምር አቈጣጠርና በጨረቃ ለብቻዋ የምትቆጥርበት ሥርዓት አላት። ይህም ሐሳበ አቅሌሲያ (Eccleciastical Calendar) የሚሰኘው ነው።

የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሐሳበ ግእዝ (Ethiopic Calendar) ተብሎም ይታወቃል። ደንበኛው አቆጣጠር ዓመቱን እያንዳንዳቸው 30 ቀናት ባላቸው 12 ወሮችና ተጨማሪ 5 ቀናት በየአራት ዓመቱ 6 የምትሆን አንድ ንኡስ ወርኅ የሚይዝ ነው። የወር አመዳደብ ስልቱ ከጥንት ግብጻውያን አቆጣጠር እንደሚመሳሰልና የእስክንድርያ (ኮፕቲክ) ቤተክርስቲያን ቅጅ እንደሆነ የሚገልጹ አሉ (Fritsch, E. 2001, 21)። ወርን በ30 ቀኖች የመመደብ ስልት ከዓመተ አዳም መገኘቱን ያሬድ ፈንታ ይገልጻሉ።

አጽዋማትና በዓላትን የሚያሳውቀው የዐቢይ ቀመር ሠንጠረዥ፣ በሐሳበ ድሜጥሮስ፣ በሐሳበ ጉንዳጉንዲና በሐሳበ ቢዘን በተለያዩ መነሻዎች ይነሡበታል። ሐሳበ ድሜጥሮስ በዐቢይ ቀመሩ ሰንጠረዥ አንድ ብሎ የሚጀምረው ከማክሰኞ (ጥንተ ቀመር)

---

ይቆጥራል። በተለያዩ መነሻዎች ቢነሱም ግባቸው ተመሳሳይ ነው። ለምሳሌ እሑድ በጥንተ ዕለት አንደኛ፣ በጥንተ ቀመር ስድስተኛ፣ በጥንተ ዮን አምስተኛ ነው። ይህ ሆኖ ሳለ ሲልቪያ ፓንክረስት በመጽሐፏ የኢትዮጵያ የዓመት መባቻና የእያንዳንዱ ሳምንት መጀመርያ ረቡዕ እንደሆነና ይህም የሆነው ክርስቶስ ረቡዕ ስለተወለደ ነው ብላ ጽፋለች (1955፡ 281)። የተሳሳተና የኢትዮጵያን ባሕረ ሐሳብ ካለመረዳት የመነጨ ነው። ኢትዮጵያ በሶስቱ ጥንታት (መነሻዎች) ብትጠቀምም ለመደበኛ አገልግሎት የምትጠቀመው የጥንተ ዕለት መነሻው እሑድን ሲሆን፣ የተፈላጊውን ወር ቀን ለማግኘት በተለይ ከረቡዕ የሚነሳውን ጥንተ ዮን ትጠቀማለች። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ተወለደ ብላ የምታምነውና በባሕረ ሐሳብ አስልታ ያገኘችው በ5501 ዓመተ ዓለም፣ ማክሰኞ ታኅሣሥ 29 ቀን ሲሆን፣ ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን መስከረም የባተው ረቡዕ ነው። ሲልቪያ ፓንክረስት የቅዱስ ዮሐንስ ዕለትን ለልደቱ መስጠቷ ነው ስህተቷ።

ሲሆን፣ 532 ብሎ የሚያበቃው ሰኞ ላይ ነው:: ማክሰኞ የተመረጠበትም ቁጥር መቁጠር የተጀመረበት ጨረቃ የተፈጠረችበት፣ ስለሆነ ነው::

በትግራይ አዲግራት አካባቢ ከሚገኘው የጉንዳጉንዲ ገዳም ሲቃውንት የተፈጠረው ሐሳበ ጉንዳጉንዲ የዐቢይ ቀመር ሠንጠረዥ የሚጀምረው ከድሜጥሮስ ሰንጠረዥ 457 ዓመት ላይ ሲሆን አንድ ብሎ የሚጀምረው ከዓርብ ነው:: የሰው ልጅ ለዚህ ዓለም መሠረቱ ስለሆነ ማዕከላችን አዳም የተፈጠረበት ዓርብ ነው ይላል:: በኤርትራ ከአስመራ ከተማ አቅራቢያ የሚገኘው ደብረ ቢዘን ገዳምም የራሱ ሐሳበ ቢዘን ሲኖረው የሰንጠረዡ መነሻ ከ229 ዓመት ላይ ሲሆን አንድ ብሎ የሚነሳው ከእሑድ ነው:: ይህች ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር የመጣችበት የመጀመሪያ ቀን እሑድ ስለሆነ የቀመራቸው መጀመሪያ አድርገውታል::

የደብረ ቢዘን ገዳም ከአስመራ ምጽዋ መንገድ 25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ በ1367 ዓ.ም በትግራይ ተወላጅ በአቡነ ፊልጶስ የተመሠረተች ሆና ሳለ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ «ታሪካቸውን አልተመራመርኩም ግን በግምት Byzantium ቢዘንታይን የሚለው ሳይሆን አይቀርም» ብለው መጻፋቸው ትክክል አገላለጽ አይመስለንም (1993፣54):: ፕሮፌሰሩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው ዘመን 5500 ብላ እንደምታምን ገልጸው በሐሳበ ሳቤላ 4481፣ በሐሳበ ቢዘን 4272፣ በሐሳበ ጉንዳጉንዲ 4265 አድርገው የጻፉትም ዘመን የሚሰፈርበት፣ አጽዋማትና በዓላት የሚታወቁበት የዐቢይ ቀመር (532 ዓመት) ሰንጠረዥ መሠረታዊ መስፈሪያ ነው:: መደበኛው የሐሳበ ድሜጥሮስ መሻ በዘመነ ማቴዎስ ከማክሰኞ አንድ ብሎ የማነሣው ቀመር የተጀመረበት ቀን ስለሆነ ነው:: ይህንኑ ሰንጠረዥ ይዞ በቢዘን አስተሳሰብ ዓለም ከተፈጠረበት እሑድ መነሻውን በማድረግና ከዘመነ ማቴዎስ ለመነሣት መነሻውን ያደረገው ከ229ኛው ቀመር ላይ ነው:: በጉንዳጉንዲ አስተሳሰብም ሰው (አዳም) ከተፈጠረበት ዓርብ እና ዘመነ ማቴዎስ አንድ ብሎ ለመነሣት መነሻ ያደረገው ከ457ኛው ቀመር ላይ ነው::

በመሆኑም ቢዘንና ጉንዳጉንዲ ከመደበኛው ጋር ያላቸው የዘመን ልዩነት 228 ዓመት እና 456 ዓመት ይሆናል:: ይህ ልዩነት በዓመተ ዓለም አቈጣጠር ላይም ተንፀባርቋል:: ከአዳም እስከ ክርስቶስ የነበረው 5500 ዘመን በፕሮፌሰር ጌታቸው አገላለጽ ተለውጧል::

> «ለማወቁ ያህል ግን በሳቤላ ግምት 4481፣ በቢዘን 4272፣ በጉንዳጉንዲ 4265 የሚል ይገኛል::» (ገጽ 54)

ገበቱ የተፈጠረው ጸሐፊው በመግቢያ ጽሑፋቸው ሲያስሉ አሊያም ምንጫቸው ተሳክቶ ይሆናል:: ትክክለኛው ቁጥር ግን የሚከተለው ነው::

ከ5500 - 228 = 5272 (ቢዘን)

ከ5500 - 456 = 5044 (ጉንዳጉንዲ)

ከ5500 - 19 = 5481 (ሳቤላ)

ጸሐፊው ከራሳቸው የመግቢያ ትንተና ጋራ «መጻሕፍቱ ምን ይላሉ» ባሉት ምዕራፍ ውስጥ ስለነዚህ ሐሳቦች (ቢዘን፣ ጉንዳጉንዲና ሳቤላ) በትክክል የተጻፉትን አለማገናዘባቸው ስህተት ሊፈጥሩ ችለዋል:: የተዛባ ነው:: ከእያንዳንዱ አንድ ሺሕ ዓመት ቀንሰውባቸዋል::

ስለ ሐሳበ ቢዘን የጻፈው አቶ ኒጉባር የቢዘን ዓመት መነሻ ዋዜማ 456 መሆኑና የሚብተው በ457 ላይ እንደሆነ ያመለከተውም (1979፣ 123) ከስህተት አላመለጠም:: የቢዘን መነሻ 229 ሲሆን የተጠቀሰው ቁጥር በመጽሐፉ ያልተጠቀሰው የጉንዳጉንዲ ስሌት ነው::

የኢትዮጵያ ዓመት፣ ዓመቱን በአራት ክፍላተ ዘመን (ወቅቶች) ክረምትና መጸው፣ በጋና ጸደይ ብሎም ይመድባቸዋል[5]:: የአዲስ ዓመት መባቻው መስከረም 1 በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት "ቅዱስ ዮሐንስ ርእሰ ዐውደ ዓመት" ሲባል፣ በዓለማዊው ገጽታ ደግሞ "እንቁጣጣሽ" ይሰኛል:: በአራት ዓመት ዐውድ መሠረት እያንዳንዱን ዓመት በአራቱ ወንጌላውያን (ማቴዎስና ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ) በመሰየም ቤተ ክርስቲያን ትጠራለች::

የዘመን መባቻ መስከረም ቢሆንም የኢትዮጵያ ሊቃውንት ጳጉሜን ከዓመት መጨረሻ ይልቅ ዓመት ከመግባቱ በፊት እንደሚቀድም ይጠቅሳሉ::

> ስለ ጳጉሜን ለማወቅ ከፈለግህ የመጀመሪያይቱ ዕለት፣ ማግስቷ፣ ሳልስቷ፣ ራብዕቷ፣ ኀምስቷ፣ እነዚህ 5 ናቸው:: የጳጉሜን ዕለቶች፣ እነዚህ ዕለቶች ከ12ቱ ወሮች አስቀድመው ስለተፈጠሩ እስከዛሬ ድረስ ዓመት ከመግባቱ በፊት ይቀድማሉ:: የዓመት መጨረሻ አይደሉም:: (ጌታቸው፣ 1993፣ 107)

የኢትዮጵያ የዘመን አቈጣጠር የዓመት አመዳደብ ፀሐያዊ መሠረቱ ከጥንት ግብፃውያን ሥርዓት ጋር ቢመሳሰልም፤ በወቅት አከፋፈል፣ በወራትና ዕለታት በዓመታት ስያሜ የራሱን ፍኖት የተከተለ ነው::

---

[5] በቅዱስ ያሬድ ድጓ መሠረት ዓመቱ በሦስት ክፍለ ዘመን ይመደባል:: እነርሱም የመጀመርያው ዮሐንስ፣ ከመስከረም እስከ ህዳር 30፣ ሁለተኛው አስተምሕሮ፣ ከታህሣስ 1 እስከ መጋቢት 30፣ ሦስተኛው ፋሲካ፣ ከትንሣኤ እስከ ዓመቱ ማብቂያ ናቸው::

ግብፃውያን ኢትዮጵያ ዘመንና ጓዙን ከግብፅ እንዳለ ወሰደች አይሉም። ግብፃዊው አቡሻክር ግብፃዊ አቡሻክር መጽሐፉ አንቀጽ 12 ላይ እንዲህ የሚል ይገኝበታል።

> ወለሰብአ ኢትዮጵያሂ ቀዳማይ ዓመቶሙ ይከውን በቀዳማይ ዓመተ ግብፃውያን ዘውእቱ ተውት ወርእስ ዐውደ ዓመቶሙኒ ይገብሩ በሠርቀ ተውት። ወሠግረሙ የኀብር ወይሰነዐው ምስለ ሠግረ ግብፃውያን ወእሙንቱሰ ይገብሩ ክልዔ ታሪካተ ታሪከ ሥጋዌ ወታሪከ ዲዮግልዲያኖስ

የኢትዮጵያ ሰዎች የዓመት መጀመሪያ ተውት (ቱቶ) በሚባል በግብፃውያን የመጀመሪያ ዓመት ይውላል። ርእሰ ዐውደ ዓመታቸውንም በተውት (መስከረም) መባቻ ያደርጋሉ። ሠርግ የሚያደርጉበት ጊዜም ከግብፃውያን ሠግር ይተባበራል። ሁለት ታሪኮችም ያደርጋሉ። እነርሱም የዘመነ ሥጋዌ (ዓመተ ምሕረት) ታሪክንና የዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ (የዓመተ ሰማዕታት) ታሪክን ነው (መሠረት፣ 1981፣ 32-33)። ኢትዮጵያ ለዓመታቱ ዐውደ ወንጌላውያንን በመጠቀም፣ የዓመቱን መባቻም ቅዱስ ዮሐንስ በማለት ከግብፅ ትለያለች። ግብፅ ዘመናቱን በወንጌላውያን፣ መባቻውን በቅዱስ ዮሐንስ የመሰየም ትውፊቱ የላትም።

### 2.2.1. የዕለታት ስያሜ መነሻ

በባሕረ ሐሳብ ከሚገኙት አዕዋዳት መሠረታዊ ዐውደ ዕለት መሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። አንድ ሳምንት ሰባት ቀን ነው የማለት መሠረቱ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ አራት ዘፍጥረት ሆኖ አንደኛም ቀን ሆኖ እያለ ከሚዘምትበት የአይሁድ ባህል የተገኘ ነው። የኢትዮጵያ የሰባቱ ቀናት ስያሜ መነሻ ከአኀዝ ጋር የተያያዘ ነው። ሰንጠረዡ ይህን ያሳያል።

| ዕለት | | ሥርወ ቃሉ | ፍች |
|---|---|---|---|
| ግእዝ | አማርኛ | | |
| እሑድ | እሑድ | አሐደ (አንድ አደረገ) | አንደኛ ቀን |
| ሰኑይ | ሰኞ | ሰነየ (ሁለት ሆነ) | ሁለተኛ ቀን |
| ሠሉስ | ማክሰኞ | ሠለሰ ማግስተ ሰኞ (ሦስት ሆነ) | ሦስተኛ ቀን |
| ረቡዕ | ሮብ | ረብዐ (አራት ሆነ) | አራተኛ ቀን |
| ኀሙስ | ኀሙስ | ኀመሰ (አምስት ሆነ) | አምስተኛ ቀን |
| ዓርብ | ዐረበ | ዐረበ (ገባ፣ መሸ) | ስድስተኛ ቀን |
| ቅዳሚ | ቅዳሜ | ቀዳሚት ሰንበት | ሰባተኛ ቀን (ዕረፍት) |

የሳምንት መባቻ ሰኞ በማድረግ እሑድን ሰባተኛ ቀን የዕረፍት ቀን የሚያደርግ ሥርዐትም በዐውደ ዕለት ውስጥ አለ። ፕሮፌሰር ጌታቸው «የሳምንቱ መጀመሪያ ሰኞ እንዲመስል ያደረገው የውዳሴ ማርያም አዘገጃጀት ነው» (1993:32) ይላሉ።

በውዳሴ ማርያም የምስጋና ድርሰቱን ከሰኞ በመነሣት እሑድ ሰባተኛ ቀን አድርጎ ያበቃል። ጌታቸው ጊዜውን ባይገልጹትም ሥርዓቱ በኋላ የመጣ መሆኑና ቀደም ብለው በተቀዱ ዳዊቶች ውስጥ ወዳሴ ማርያም የሚጀምረው ከእሑድ መሆኑን ገልጸዋል (ዝኒከማሁ)። ለየት ያለ አስተሳሰብ ያላቸው ያሬድ ፈንታ (1993) በአንድ ጽሑፋቸው ያሰፈሩት የሚከተለው ነው:-

> በኢይወርድና በኢየዐርግ ሥርዓት የጾኑ ዐበይት በዓላት (ደብረ ዘይት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራቅሊጦስ) ከእሑድ፣ አጽዋማት (ነነዌ፣ ዐቢይ ጾም፣ ጾመ ሐዋርያት) ከሰኞ በቀር በሌላ ቀን እንዳይጀመሩ ቅዱስ ድሜጥሮስ ወስኖታል። ምስጢሩም በብሉይ ኪዳን በዕለተ ቀዳሚት ሥጋዊ ዕረፍት እንደተገኘ፣ በሐዲስ ኪዳንም በዕለተ እሑድ የመንፈሳውያን ዕረፍት ጌታችን መነሣቱን ያመለክታል።

በያሬድ እንደተገለጸው ከሰኞ መነሣት በኋላ የመጣ ሥርዓት ሳይሆን በተለይ በሦስተኛው ምእት ዓመት ከነበረው ድሜጥሮስ ጀምሮ የተደራጀ ነው።

ውዳሴ ማርያምን እንደደረሰ የሚነገርለት ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም የሰኞን ሥርዓት በዐውደ ዕለት ቀዳሚ ያደረገበትን ምክንያትም ከድርሰቱ በመነሣት ያሬድ እንደሚከተለው ገልጸውታል።

ለቅዱስ ኤፍሬም ምስጢሩ ተገልጾለት በደብተራ ኦሪት[6] በዕለተ ቀዳሚት ሌዋውያን ይገለገሉባቸው በነበሩ በመሶበ ወርቅ፣ በተቅዋመ ወርቅ[7]፣ በማዕጠንተ ወርቅ[8]፣ በበትረ አሮን እየመሰለ በዕለተ እሑድ እመቤታችንን ሲያመሰግን አድሯል። ስለዚህ ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን ምሳሌ እንደሆነ ሰንበተ አይሁድም ለሰንበተ ክርስቲያን ምሳሌ ናትና ዕለተ ቀዳሚት [ቀዳሜ] ለጥንተ ዕለት ለእሑድ ሰባተኛ እንደሆነች እሑድም ለጥንተ ሣኒታ፣ ለጥንተ አስተርእዮ ለሰኞ ሰባተኛ ናት። በዘመነ ሐዲስ የተሠሩ አጽዋማትና በዓላት መነሻቸው ሰኞ መድረሻቸው እሑድ እያደረጉ በየሳምንቱ የሚመላለሱትም ስለዚህ ነው።

---

[6] ቤተ መቅደስ
[7] ባለ ሰባት ቅርንጫፍ መብራት (ሻማ) የሚቆምበት
[8] ዕጣን የሚጨስበት፣ የሚታጠንበት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

የሰባቱ ዕለታት ዐውድ በተለያዩ መነሻዎች (ጥንታት) ሲነሣ የሚከተለው መልክ እንዳለው ከሰንጠረዡ መረዳት ይቻላል።

| ደረጃ | ጥንተ ዕለት | ጥንተ ቀመር | ጥንተ ዮን | ጥንተ ሣኒታ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | እሑድ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሰኞ |
| 2 | ሰኞ | ረቡዕ | ኀሙስ | ማክሰኞ |
| 3 | ማክሰኞ | ኀሙስ | ዓርብ | ረቡዕ |
| 4 | ረቡዕ | ዓርብ | ቅዳሜ | ኀሙስ |
| 5 | ኀሙስ | ቅዳሜ | እሑድ | ዓርብ |
| 6 | ዓርብ | እሑድ | ሰኞ | ቅዳሜ |
| 7 | ቅዳሜ | ሰኞ | ማክሰኞ | እሑድ |

ከእሑድ እስከ ኀሙስ ቁጥር ሆኖ ዓርብ ላይ «ሰዱስ» አለማለቱ የሳምንቱ ማብቂያ፣ መካተቻ፣ የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ስለሚገልጽ ነው፤ በማለት የኢትዮጵያ ሊቃውንት «ዓርብ» የሚለውን ስያሜ እንደሰጡ ይታመናል።

2.2.2. የወራት ስያሜ መነሻ

በአዕዋዳት ሥርዓት መሠረት ከዕለት ቀጥሎ ያለው መስፈርያ ወር ነው። ዐውደ ዓመቱ በወራት ይከፈላል። የኢትዮጵያ ወራት 12 ባለ 30 ቀኖችና 13ኛው ባለ 5 ቀኖች በአራት ዓመት 6 ቀኖችን ያቀፈ ነው።

እያንዳንዱ ወር የራሱ መጠርያና ፍች አለው። ሥርወ ቃሉን በምንመረምርበት ጊዜ የምናገኘው ስያሜዎች ከማኅበረ ባህላዊና እርሻ ጋር ተዛምዶ እንዳላቸው ነው። ጌታቸው «ከጳጉሜን በቀር የነዚህን ስሞች ትርጉም የሚያውቅ የለም» (1993፣36)፤ ኦቶ ኒጉባርም «የኢትዮጵያ (ግእዝ) ወራት ስሞች ምንጭና ፍች ከመስከረም፣ ኅዳር እና ሐምሌ በቀር አይታወቅም» (1979:192)፤ ብለው ቢጽፉም ከትውፊትም ሆነ ከነባር መጻሕፍት የተላለፈልን ግን ስያሜዎቹ መነሻ እንዳላቸው ነው። (ኪዳነ ወልድ:1948)፣ (ደስታ፣ 1962)፣ (ሔኖክ፣ 1976)፣ (ክፈለው፣ 1985)።

*መስከረም*

መስከረምን በሁለት መንገድ ይፈቱታል። አንደኛው «መሰስ» እና (ከረም) ከተሰኙ ሁለት ቃላት ቅንጅት የፈጠረ ነው። ክረምቱ መሰስ ብሎ ያለፈበት መሆኑን ያሳያል። እንደ ኪዳነ ወልድ አገላለጽ ምሴተ ክረምት ተብሎ ይፈታል። ምስጢሩ ፀአትና መሰስ

(መውጣትና ማለፍ) ማለት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከመዘክረ ዓም መውጣቱን የዓመት መታወሻ፣ ከባሕረ ሐሳብ እወጃ አኳያ የበዓልና ጾም ማሳወቂያ፣ የአዲስ ዓመት መባቻና 26ኛው ቀንም የመፀው ክፍለ ዘመን መግቢያ ስለሆነም የዘመን መታወሻ ሆነ ይሉታል። «ሰ» እና «ዘ» ተወራራሽ ስለሆኑ መዝከረም መስከረም መባሉም ይጠቀሳል።

*ጥቅምት*

ጥቅምት፣ ጥቅም ጥንት የአዝመራ ውጤት በመነሻ የሚገኝበት የጥቅም መጀመሪያ ማለት ነው። የፍሬ ወር፣ የእሸት ጊዜ ያሰኛል።

*ኅዳር*

ኅዳር፣ ኅዳር (አደረ) ከሚለው ግስ የተገኘ እረኞች ወይም ገበሬዎች የአዝመራ ፍሬያቸውን ለመጠበቅ ከደጅ ማማ ሠርተው ውጪ የሚያድሩበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው።

*ታኅሣሥ*

ታኅሣሥ፣ ኀሠሠ መፈለግ፣ መፈተሽ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ማሰስ መጥረግ ይሆናል። አዝመራ ከመፈለግ ከመመርመር ጋር ይያያዛል።

*ጥር*

ጥር፣ ጠየረ፣ አዘጋጀ፣ አደራጀ ከሚለው የወጣ ይመስላል። ጸርሐ፣ ጠርዓ ለበዓል ለድግስ መጥሪያ፣ መጥራትን ያመለክታል።

ጥህር መንፃትን፣ መጠመቅን ያመለክታልና በዚህ ወር የሚውለውን የጥምቀት በዓል ይመለከታል።

*የካቲት*

የካቲት፣ ከቲት፣ ማካተቻ ሲሆን የተሰበሰበውን አዝመራ ከጎታ መክተት ጋር ይያያዛል። የመከር ጫፍ መካተቻ ነው።

*መጋቢት*

መጋቢት፣ መገበ ከሚለው ቃል ጋር ይዛመዳል። ድኅረ አዝመራ ምግቡ በበቂ ስለሚገኝ መመገቢያ ስለሆነ ቀኑና ሌሊቱ የሚተካከሉበት እኩል፣ 12፣12 ሰዓት የሚሆኑበት ስለሆነ መጋቢት ተባለ ይላሉ።

*ሚያዝያ*

ሚያዝያ፣ መሐዘ ጓደኛ አበጃ ከሚለው ቃል የወጣ ነው፡፡ ከሙሽራና ጋር የሚያያዝ ሚስት የመፈለጊያ፣ ጋብቻ መመሥረቻ ወር ነው፡፡ ሚዜ፣ ሚዝት (ሚስት) ከሚያዝያ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

*ግንቦት*

ግንቦት፣ ገነባ ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን ያገዳን እህል ገነበበ ከመረ ቆለለ ማለት ነው፡፡ የአገዳው እህል ክምር የሚገባደደው በግንቦት ወር ነው፡፡ በሌላ በኩልም ገቦ ክረምት የክረምት ጎን አጠገብ ነውም ይባላል፡፡

*ሰኔ*

ሰኔ፣ ሰነየ፣ አሳመረ ካለው ቃል የወጣ መልካም ዘርን የሚጠቅስ ነው፡፡ የእርሻ መለዘብና የዘር ልስላሴን ያመለክታል፡፡

*ሐምሌ*

ሐምሌ፣ ሐሚል፣ ሐመለ ማበብ፣ ማፍራትን የሚመለከት ቅጠላ ቅጠል፣ ሣር፣ ቡቃያ፣ ጎመን የሚበላና የማይበላ የሚያብብበት ወር በመሆኑ ስሙን ከግብሩ ያገኘበት ነው፡፡

*ነሐሴ*

ነሐሴ፣ ነሐሰ-ግንብን መደብን ሠራ ወይም ገነባ ከሚለው የተገኘ ነው፡፡ የዓመት ወራት ማገባደጃ መደምደሚያ ማመልከቱ ነው፡፡

*ጳጉሜን*

ጳጉሜን የቃሉ መነሻ ከጽርዕ (ግሪክ) ኤፓጎሜኔ ሆኖ ቷግሜ ጭማሪ ተውሳክ ማለት ነው፡፡ ዳግመኛም ከዐውደ ወርኅ ስለተረፈና ስለተገኘ የወር ትርፍ ይባላል፡፡

የኢትዮጵያ ደንበኛ ቀመር መሠረቱ ሃይማኖታዊ (ክርስትና፣ አይሁድ) ቢሆንም ከዚያ በፊት ልዩ ልዩ ዓይነት ቀመር መኖሩ አይሳትም፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ባህላዊ ቀመሮች በተለይ በጨረቃ ዑደት ላይ የተመሠረቱ እንደነበሩ፣ አሁንም እንዳሉ እናያለን፡፡ የወር እና የዕለት አከፋፈልም አላቸው፡፡ ለምሳሌ የሲዳማ ቀመር ፍቺ (ሐሳበ ሲዳማ ብለን ከባሕረ ሐሳብ ውስጥም መክተት እንችላለን) ሳምንቱ በአራት ቀኖች መመደቡና በገበያ ላይ የተመሠረተ ስያሜ መኖሩ ይታወቃል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ክርስትና በሰሜን ኢትዮጵያ ሲገባና ሲስፋፋ የውጭ ግንኙነቱ ሲጠናከር አዳዲስ አስተሳሰቦች ሲገቡ ነባር አቈጣጠር ተለወጠው ወይም ተተተው ይሆናል። የግእዙ ቀመር የወራት ስያሜው ሃይማኖታዊ ይዘት ባይኖረውም የዕለታቱ ስያሜ ግን ከአይሁድ ትውፊት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻን የያዘ መሆኑ ይታያል። ዕለታትን በቁጥር ከመሰየማቸው በፊት ሌላ ስያሜ ኖሮን እንደሆነ ቀጣይ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል።

## 2.3. የቀመር መነሻ (የኢትዮጵያ ዓመታት መነሻ)

ኢትዮጵያ ለደንበኛው የዘመን አቈጣጠርዋ መነሻ የምታደርገው "ዓመተ ምሕረት"ን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደበት ዘመን አንድ ብላ በመነሳት ትቆጥራለች።

ቀደም ብለው በተጻፉት የግእዝ ድርሳናት ይበልጥ የሚታወቀው "ዓመተ ሥጋዌ" ነው። በዓመተ ምሕረት ስም የሚታወቁ ሌሎች አቈጣጠሮችም አሉ። በቤተ ክርስቲያኒቱ ትውፊት መሠረት ከክርስቶስ ልደት በፊት፣ አዳም ከተፈጠረበት ዘመን አንስቶ የሚቆጥር የዓመተ ዓለም አቈጣጠር አለ። ከአዳም እስከ ልደተ ክርስቶስ የነበረው ዘመን 5500 ዓመት እንደሆነ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታምናለች። የቁጥሩ መነሻ የሰብዓ ሊቃናት የብሉይ ኪዳን እትም ሚከተለው የግእዝ መጽሐፍ ቅዱሷ ነው።

በዓመተ ምሕረት ስም የሚጠሩት በተለይ ሁለት የአቈጣጠር መንገዶች ሲኖሩ፣ አንደኛው የዓመተ ዓለም ቁጥርን ለዐቢይ ቀመር (532 ዓመት) በማካፈል ከሚገኘው ድርሻ የሚተርፈው ቀሪ ዓመተ ምሕረት ሲባል፣ በዓመተ ሥጋዌ ላይ ከሚደመረው 8 ጋር የሚገኘው ውጤትም ዓመተ ምሕረት ይሰኛል። ዓመተ ዓለሙንም ዓመተ ምሕረት ብለው የሚጠቅሱ ድርሳናት አሉ። የምሕረት ዓመት ከአምስት ቀን ተኩል (5500 ዓመት) በኋላ ይመጣል፤ የሚለውን ቃለ ተስፋ ይዘው ዓመተ ዓለሙን ዓመተ ምሕረት ማለታቸው በሊቃውንት ይነገራል።

ቤተ ክርስቲያኒቱ በነባር ሥርዓቷ ዓመተ ሰማዕታት የተሰኘ አቆጣጠር በ3ኛው ምእት ዓመት በደረሰው የክርስቲያኖች እልቂት መታሰቢያ እንዲሆን ከ277 ዓመተ ሥጋዌ አንድ ብሎ የሚነሳ አቆጣጠር አላት። በግብጽ የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ደንበኛው ቀመሯ ሆኖ እየሠራችበት ትገኛለች።

ኢትዮጵያ የጊዜ መስፈርያዋ በአዕዋዳት መመላለስ ላይ የተመሠረተ ነው። በቤተ ክርስቲያኒቱ ስሌት መሠረት ይህ ዓለም መነሻና መድረሻ አለው። ከጥንተ ፍጥረት

አዳም ተነሥቶ እስከ ምጽአት ይደርሳል:: ምጽአቱም ስምንተኛው ሺሕ ሲፈጸም ይሆናል ይላል::

በ2000 ዓ.ም. ዓመተ ዓለሙ 7500 ዓመት ሲሆን ይህም የተገኘው በዓመተ ምሕረቱ ላይ ከአዳም እስከ ክርስቶስ ልደት የነበረው 5500 ዓመት ተደምሮበት ነው:: የስምንተኛው ሺሕ ማብቂያ በ2500 ዓ.ም. እንደሆነ ይታመናል::

ኢትዮጵያ ዘመኗን በዋናነት የምትመድበው በዐቢይ ቀመር ሲሆን 14 ዐቢይ ቀመር የሞላው በ1948 ዓ.ም. ነበር:: (14 X 532 = 7448 ዓመት) 15ኛው ዐቢይ ቀመር በ1949 ዓ.ም ተጀምሮ 2000 ዓ.ም ላይ 52ኛ ዓመት ላይ ይገኛል:: ቀመሩ የሚሞላው 2480 ዓ.ም. ወይም 7980 ዓ.ዓ. ላይ ነው:: ዐሥራ አራተኛው ዐቢይ ቀመር ሲሞላ ምጽአት ይሆናል ተብሎ ተፈርቶ ነበር:: ሰባት ሺሕ ሲሞላም እንደዚሁ ተሰግቶ ነበር:: ሕይወት ግን ቀጥላለች::

የኢትዮጵያ ዓመታት መነሻ በተለይ በአራት ዓመት ዑደት፣ በ28 ዓመት ዑደት፣ በ532 ዓመት ዑደት መነሻው ሁልጊዜ የዐውደ ጳጉሜን አንደኛ የሚሆነው ዘመነ ማቴዎስ ሲሆን መካተቻው ደግሞ ዘመነ ዮሐንስ ይሆናል:: የምእት ዓመትም ኾነ የሺሕ ዓመትም መባቻ ከዚህ የተለየ አይደለም::

ለዘመን ቁጥር መነሻ የኾነው ኢየሱስ የተወለደው በ5501 ዓ.ም. መሆኑ፣ 2000 ዓ.ም. በዓመተ ዓለም ሲቈጠር ከ7500 ዓመት መሆኑ ታውቋል:: በዚህ መሠረት በዓመተ ምሕረት 20ኛው ምእት ወይም ሁለተኛው ሺሕ፣ በዓመተ ዓለም 80ኛው ምእት ወይም ስምንተኛው ሺሕ ውስጥ እንገኛለን::

እያንዳንዱ ምእት ሆነ ሺሕ ዓመት የሚገባበት የራሱ የዐውድ ሥርዓት አለው:: በዘመን አቈጣጠር ውስጥ ላዕለይና ታህታይ የሚባሉ መደቦች አሉ:: ታህታዩ መደብ ምእት ዓመት (ሲንቸሪ) ሲሆን፣ ላዕላዩ ደግሞ ሺሕ ዓመት (ሚሌኒየም) የሚሰኘው ነው::

እነዚህ ዓመታት «ዐውደ ጳጉሜን» ተብሎ በሚጠራው የአራት ዓመት ዐውድ በመመደብ የእያንዳንዱን ምእት ሆነ ሺሕ ዓመት መነሻን የሚያሳይ ትውፊት መኖሩንና እያንዳንዱን ዓመት አራቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ሲያፈራርቁት መነሻው ቁጥር 1 (ማቴዎስ) ሲሆን፣ ማብቂያው ቁጥር 4 ወይም አልቦ ዮሐንስ ነው::

በዚሁ ስሌት መሠረት ኢትዮጵያና ባሕረ ሐሳቧ ምእትና ሺሕ ዓመታቱን ሲቀበሉ ኖረዋል:: አቈጣጠሩ መነሻውን ከኢየሱስ ልደት አንድ ብሎ እንጂ አልቦ (ዜሮ) ብሎ የመጀመር ትውፊት የለውም::

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

የመጀመሪያው ምእት ዓመት ከ1 ዓ.ም. አንስቶ እስከ 100 ዓ.ም.፣ ሺሑ ዓመትም እስከ 1000 ዓ.ም. ድረስ ዘልቋል:: ለአብነት 20ኛው ምእት ዓመት የባተው በ1901 ዓ.ም. ዘመነ ማቴዎስ ላይ ሲሆን የሚፈጸመው ደግሞ በ2000 ዓ.ም. በዘመነ ዮሐንስ ላይ ይሆናል:: በሺሕ ዓመት አቈጣጠርም ተመሳሳይ መሆኑና በ1001 ዓ.ም. ዘመነ ማቴዎስ የገባው ሁለተኛው ሺሕ በ2000 ዓ.ም. ዘመነ ዮሐንስ አብቅቶ፣ በ2001 ዓ.ም. በዐዲሱ ዐውድ ሦስተኛው ሺሕ እንደሚገባ ባሕረ ሐሳቡ ይገልጻል::

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ መንግሥት ባቋቋመው የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት ከታኅሣሥ 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ባደረገው እንቅስቃሴና፣ ባሰራጫቸው የሕትመት ውጤቶቹ የኢትዮጵያ ሺሕ ዓመት የባተው በ2000 ዓ.ም. እንደሆነ አድርጎ የገለጸበት መንገድ ከኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ባሕረ ሐሳብ ትውፊት ጋር የማይሄድ ስህተት ፈጽሟል (ሔኖክ፣ 1999)::

በኢትዮጵያ ባሕረ ሐሳብ ድርሳናት ውስጥ በዓመተ ዓለምም ሆነ በዓመተ ምሕረት የሺሕ ዓመታት መሻና መድረሻ በሚከተለው መልኩ ተመዝግቦ እናገኘዋለን::

ሀ) በዓመተ ዓለም

1ኛው ሺሕ በ1 ዓ.ዓ. ማክሰኞ ተነሥቶ በ1000 ዓ.ዓ. ዓርብ ተፈጽሟል::

2ኛው ሺሕ በ1001 ዓ.ዓ. ቅዳሜ ተነሥቶ በ2000 ዓ.ዓ ማክሰኞ ተፈጽሟል::

3ኛው ሺሕ 2001 ዓ.ዓ.-ረቡዕ ተነሥቶ በ3000 ዓ.ዓ. ቅዳሜ ተፈጽሟል::

4ኛው ሺሕ 3001 ዓ.ዓ. እሑድ ተነሥቶ በ4000 ዓ.ዓ. ረቡዕ ተፈጽሟል::

5ኛው ሺሕ 4001 ዓ.ዓ. ኀሙስ ተነሥቶ በ5000 ዓ.ዓ. እሑድ ተፈጽሟል::

6ኛው ሺሕ 5001 ዓ.ዓ. ሰኞ ተነሥቶ በ6000 ዓ.ዓ. ኀሙስ ተፈጽሟል::

7ኛው ሺሕ 6001 ዓ.ዓ. ዓርብ ተነሥቶ በ7000 ዓ.ዓ. ሰኞ ተፈጽሟል::

8ኛው ሺሕ 7001 ዓ.ዓ. ማክሰኞ ተነሥቶ በ8000 ዓ.ዓ. ዓርብ ይፈጸማል::

ለ) በዓመተ ምሕረት

1ኛው ሺሕ 1 ዓ.ም. ረቡዕ ተነሥቶ በ1000 ዓ.ም. ቅዳሜ ተፈጽሟል::

2ኛው ሺሕ 1001 ዓ.ም. እሑድ ተነሥቶ በ2000 ዓ.ም. ረቡዕ ይፈጸማል::

3ኛው ሺሕ 2001 ዓ.ም. ኀሙስ ተነሥቶ በ3000 ዓ.ም. እሑድ ያበቃል::

የዘመን መለወጫን ተከትሎ የሚከናወነውን የባሕረ ሐሳብ እወጃ በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንመለከታለን::

# ምዕራፍ ሦስት

# የባሕረ ሐሳብ እወጃና ክብረ በዓሉ

## 3.1 የባሕረ ሐሳብ እወጃ ምንድን ነው?

የባሕረ ሐሳብን ምንነት ባለፈው ምዕራፍ ገልጸናል፡፡ ባሕረ ሐሳብ በጠባቡ ሲተረጎም የዘመን መለወጫ ዕለት ከሚታወጀው የተዘዋዋሪ አጽዋማትና በዓላት ጋር ይዛመዳል፡፡

የእወጃ መነሻ ግሡ አወጀ ኾኖ አዋጅ መናገር፣ ለፈፈ፣ ለሕዝብ የሚነገር ደንብ፣ ውሳኔ፣ ትእዛዝ እንደሆነ ደስታ ይገልጻሉ (1962: 910)፡፡

በዚህ መነሻና ይዘት በቤተ ክርስቲያን የሚደረገው የባሕረ ሐሳብ አዋጅ ከቤተ ክህነት ሊቃውንት በየአጥቢያው ለምእመን የሚነገር የዘመኑ አጽዋማትና በዓላት የሚያዙበትና የሚውሉበት ቀን የማስታወቅ፣ ዘመኑን በተለያዩ መነሻዎች የሚገለጹበት ብሎ መበየን ይቻላል፡፡ እንደ ደስታ አገላለጽ እወጃው ከዐውደ ዓመት ጋር ይያያዛል፡፡

የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ክብረ በህል በመስከረም መባቻ ዐውደ ዓመቱን ፈጽሞ የሚመጣ በመሆኑ በቤተ ክርስቲያን ሕዝቡ (ምእመኑ) ተገኝቶ የዘመኑ አጽዋማትና በዓላት ተሰብስበው በዕለቱ ይነገራታል፡፡ ዕለቱን በፀሐይ፣ በጨረቃና በሌሊት እያሰሉም ያወጡለታል (አሥርቆት ያደርጉለታል)፡፡

የባሕረ ሐሳብ እወጃ የሚካሄደው በዘመን መለወጫ ክብረ በዓል ላይ በመሆኑ የክብረ በዓልን ምንነት በሚከተለው ንኡስ ምዕራፍ እንመለከተዋለን፡፡

## 3.2. የክብረ በዓል ምንነት

ክብረ በዓል በማኅበረሰቡ የጋራ አከባበር በጥንቃቄ በተሰላ መርሐ ግብር በክብር የሚዘጋጅ ደስታን የሚያጎናጽፍ፣ በማኅበራዊ ልማድም ላይ የተመሰረተ ወይም በተለያዩ ባሕላዊ ቡድኖች (ተቋማት) የሚዘጋጅ እንደሆነ ሩት ግሪጎሪ ትገልጻለች (ኢንካርታ፣ 2006)፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በዓልን እንደሚከተለው ይፈቱታል፡፡

> *የደስታ፣ የዕረፍት ቀን፣ በዓመት፣በወር፣ በሳምንት የሚከበር፣ ያለፈ ነገር የሚታሰብበት ተዝካር፣ ሕዝብ የበዓሉን ምስጢር*

> *እያሰበ ደስ ብሎት ለብሶ አጊጦ የሚዘፍንበት፣ የሚዘምርበት፣ እልል የሚልበት ሽብሸባ ጭብጨባ ቀኒጽ (መፈንጨት፣ መዝለል፣) ነፈርዓጽ (ዝላይ) የሚያደርግበት፤ ሲያረግድ፣ እስክታ ሲወርድ፣ በአንገቱ የሚቀጭበት እንደ ጥጃ የሚፈነጭበት ነው (1948፣ 278)፡፡*

እንደ ኪዳነ ወልድ አገላለጽ በዓል ሥርዓታዊ ሆኖ በተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚከበር ደስታን ፈንጣቂ፣ ሐሴትን አብሳሪ፣ ከዘወትሩ (ከአዘቦቱ) የተለየ ማለፊያ አልባሳትን የሚጎናጸፍበት ክዋኔውም እርካታን በሚያቀዳጅ በልዩ ልዩ መልክ የሚገለጽ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ባሳተመው "አማርኛ መዝገበ ቃላት" ክብረ በዓልን በየዓመቱ የሚከበር ትልቅ መንፈሳዊ በዓል በማለት ተርጉሞታል (1993፣ 375)፡፡


ለዚህ ብያኔ መነሻ የሆነ ለክብረ በዓል በደስታ ተክለ ወልድ የተሰጠ ትርጓሜ አለ፡፡ የበዓል ክብር፣ ገናን፣ ጥምቀትን፣ ትንሣኤን፣ ጰራቅሊጦስን፣ መስቀልን፣ ፍልሰታን፣ ኅዳር ሚካኤልን፣ ማዚያ ጊዮርጊስን ለመሰለ በዓል የሚደረግ ማሕሌት፣ ዘፈን፣ ንግሥ፣ እልልታና ደስታ፣ ሥራ አለመስራት፣ መንገድ አለመሄድ ነው ይሉታል (1962፤ 636)፡፡

በማኅበረሰቡ ውስጥ በተለይ በሃይማኖታዊው (መንፈሳዊ) አከባበር ዐቢይ ስፍራ ያላቸው በየተወሰነላቸው የጊዜ ገደብ ሲከበሩ በቋሚነትና በተዘዋዋሪነት የሚታወቁት የመለኮትና የቅዱሳን በዓላትን ከደስታ አተረጓጐም እናገኛለን፡፡ በሥራ ባለመጠመድ በዓልን በተለያዩ ክዋኔዎች በሐሴት ማክበር የሚቻልበት መሆኑን ከመዝገበ ቃላቱ አፈታት መረዳት ይቻላል፡፡

ክብረ በዓላት ሃይማኖታዊና ዓለማዊ በማለት በሁለት ዐበይት ክፍሎች ይመደባሉ፡፡

ዓለማዊው አከባበር ከሃይማኖታዊው ክብረ በዓላትና በዓላት ይለያል፡፡ ሃይማኖታዊው ትኩረቱ በአንድ እምነት ውስጥ የሚከበሩ ቅዱሳን ቀኖች ላይ ነው፡፡

በዓልን በጋራ ማክበር ከሰዎች መስተጋብር ወይም ተራክቦ የመነጨ ነው፡፡ ፎክሎሪስቶች እንደሚያምኑት የመጀመሪያው ክብረ በዓል የተከሰተው ቀደምት ሕዝቦች ከነበራቸው ወይም ካደረባቸው ጭንቀት የተነሣ ነው፡፡ የተፈጥሮ ኃይሎችን ካለመረዳት



▪ ቅድስት ልደታ ማርያምና የዘመን እወጃ በዐውደ ምሕረት





- መምህር ዘካርያስ አምባው የባሕረ ሐሳብ እወጃውን በዐውደ ምሕረት ሲያሰሙ

IES LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ከሚመጣባቸው ጭንቀት ለመገላገል በዓልን ማክበር እንደጀመሩ ተገልጿል (ሩት ግሪጎሪ፣ ኢንካርታ፣ 2006 ዓ.እ.)፡፡ ጥንታውያን ክብረ በዓላትና በዓላት ከእርሻ ዘርና የመከር ጊዜ ወይም ሙታንን ከመዘከር ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ እነዚህ እንደ ዓለማዊ በዓላት ተቆጥረው ሲቀጥሉ፣ ሃይማኖታዊ ተጽዕኖ ያየለባቸው ሆነው በዚህ ዘመን |ልው ሆነዋል፡፡ በርካታ ዓለማዊ አከባበሮችም ከታሪክ ክንዋኔ ጋር ተያይዘው ይከበራሉ፡፡

አክባሪው ከአከባበሩ ከሚያገኘው እርካታና ደስታ ባሻገር ክብረ በዓላት በርካታ ጠቀሜታዎችና እሴቶች አሉዋቸው፡፡ በክብረ በዓላቱ አረጋውያን ሕዝባዊ እውቀታቸውን (Folk knowledge) ለትውልድ ለማስተላለፍ መልካም አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል፡፡

የአንድ የተወሰነ ጎሳን ዕውቀት ለወጣቱ ትውልድ ለማስተላለፍም ይረዳል፡፡ ክብረ በዓላት የተለያዩ ዓይነቶች አሉዋቸው ብለናል፡፡ ሙታንን/ሰማዕታ ትን የማክበርና የመዘከር ሁኔታ በኅብረተሰቡ ውስጥ አስፈላጊው ክብረ በዓል ነው፡፡ ለምእታት ዓመታት የታሰቡ የዘመኑ ሰዎችም የቀጠሉበት ልማድ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስንክሳር መሠረት አገራዊና ዓለምአቀፋዊ ቅዱሳንና ሰማዕታት ታሪካዊ ሰዎች "ወበዛቲ ዕለት አዕረፈ" በዚህም ቀን እከሌ አረፈ፤ መታሰቢያው ነው እያሉ ያከብሩታል፡፡

በዓመት ውስጥ ያሉትን ወቅቶች (ክፍላተ ዘመን) መለዋወጥ መሠረት ያደረገ ክብረ በዓላትም አሉ፡፡ የመፀው (አበባ) በዓል፣ የመከር በዓል ይጠቀሳሉ፡፡ በኢትዮጵያ ከዘመነ አክሱም ገርምሮ "ተቀጸል ጽጌ" (አበባን ተቀዳጅ) የተሰኘ በዓል እስካሁን እየተከበረ ሲሆን በዓሉ የወቅቶችን ዑደት የሚከተልና በፀሐይና በጨረቃ ሥርዓተ ዘመን መሠረት የሚከናወን ነው፡፡

የክርስቲያን ክብረ በዓል ሁለት ዐበይት ክፍሎች አሉት፡፡ አንደኛው በየዓመቱ በቋሚነት የሚከበሩ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በየዓመቱ በአዋጅ የሚታወቁ ተዘዋዋሪ በዓላት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል እነዚህ ሃይማኖታዊ በዓላት የተለያየ ፈርጅ አላቸው፡፡ ለምሳሌ ክርስቲያንን ብንመለከት ሦስት ዐበይት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመርያው መለኮታዊ በዓላት (የእግዚአብሔር፣ የኢየሱስ ክርስቶስ፣ የሥላሴ)፤ ሁለተኛው የቅድስት ማርያም ወላዲተ አምላክ፣ ሦስተኛው የቅዱሳን አበው፣ እመው፣ የሰማዕታት መታሰቢያ በዓላት ናቸው፡፡ ቅዱሳኑ የተወለዱበት፣ ያረፉበትና ተአምራት ያደረጉበት ዕለት ይከበራል፡፡ ለአብነትም ቅዱስ ያሬድ ማኅሌታይ የተወለደበት ሚያዝያ 5 ቀን፣

ያረፈበት ግንቦት 11 ቀን በስሙ በታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ይከበራል። የቅድስና ክብር የተሰጣቸው አቤ ገላውዴዎስ የሰማዕትነት አክሊል የተቀዳጁበት መጋቢት 27 ቀን እንደሚከበር በስንክሳር ተገልጿል።

ኢትዮጵያ ከምታከብራቸው በዓላት መካከል አንዱ የዘመን መለወጫ ሲሆን በሁለት ፈርጅ ሃይማኖታዊና ዓለማዊ አከባበር አለው። በሃይማኖታዊ ገጽታው ቅዱስ ዮሐንስ ርእሰ ዐውደ ዓመት ይሰኛል። በቤተ ክርስትያኒቱ ባለው መንፈሳዊ አከባበር በዓላትና አጽዋማት ስለሚውሉበት ቀን የሚነገር አዋጅ ማሕሌት የማቆምበት፣ መንፈሳዊ ዝማሬና ትርዒት የሚቀርብበት ዝግጅት አለው።

በዓለማዊው ውስጥ በተለይ በመንግሥታዊ ድንጋጌ ከሁለቱም ጎራ በብሔራዊ ደረጃ የሚከበሩ በዓላት አሉ። ዓለማዊውን ስንመለከት ከአገር ነጻነትና አንድነት ጋር የተያያዙ ከፖለቲካዊ ሥርዓት ለውጥ ጋር የሚገናኙ በዓላት አሉ።

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት (1923-1967)፤ በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1967-1983)፣ የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት በኋላ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1983-) መንግስታት እንደየአቋማቸው በድንጋጌ ያወጡት የብሔራዊ በዓላት ዝርዝሮች አሉ።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የነገሡበት ጥቅምት 23፣ 1923 ዓ.ም. የዘውድ በዓል፣ ደርግ ስልጣን ላይ የወጣበት መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. የአብዮት በዓል ሆነው ተከብረው አልፈዋል። የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) ደርግን ያስወገደበት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. በየዓመቱ ይከበራል።

ከብሔራዊ በዓላት መካከል መስከረም 1 ቀን የአዲስ ዘመን መባቻ ሲሆን እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ ኤርትራ ከእናት ሀገሯ የተቀላቀለችበት በዓልም በተደራቢነት ይታሰብ ነበር።[9]

ከአርበኝነትና ከተጋድሎ ጋር የተያያዙ በዓላትም የካቲት 23 ቀን የዓድዋ ድል መታሰቢያና ሚያዝያ 27 ቀን የድል በዓል[10] ናቸው። ሃይማኖታዊ ዐውድ ያላቸው

---

[9] መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተቀላቀለችበት አክት ፌደራል ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በአዋጅ ያናገሩበት ነው።

[10] ሌሎች መጠሪያዎች የአርበኞች መታሰቢያ ቀን፣ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት መናገሻ ከተማቸው የገቡበት እየተባለ ቢጠራም ሕጋዊ ስሙ የድል በዓል ነው።

ብሔራዊ በዓላት ደግሞ ከክርስትናው ረድፍ፣ መስቀል መስከረም 17 ቀን፣ ገና (ልደት) ታህሣሥ 29 ቀን (በየአራት አመቱ በ28 ይውላል)፣ ጥምቀት ጥር 11 ቀን፣ በመጋቢት ወይም በሚያዚያ የሚውሉት ስቅለትና ትንሣኤ ሲሆኑ፤ ከእስልምናው ረድፍ ተዘዋዋሪ ቀናት ያላቸው መውሊድ፣ ኢድአል አድሃ (አረፋ)ና ኢድአልፈጥር (ረመዳን) ናቸው::

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ትኩረት የሚያደርገው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በታላቅ መንፈሳዊ (ሃይማኖታዊ) ሥርዓት የምታከብረው የዘመን መለወጫ ርእሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ ክብረ በዓል ላይ ነው::

ለክብረ በዓሉ ምክንያት አንዱ ከአሮጌው ወደ አዲሱ ዘመን የሚደረገው ሽግግር ነው:: የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት የሚለወጠው ከሦስት ወራት ክረምትና ጠንካራ ዝናባማ ወቅት ወደ ብራነት እየተለወጠ ወደ ዘመነ መፀው የሚያመራበት መሆኑ ነው:: መፀው የሚብተው መስከረም 26 ቢሆንም የዓመት መባቻው ግን በመስከረም 1 ቀን ይውላል::

## 3.3. የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ ልዩ ልዩ መጠሪያዎች እንዴትነት

የኢትዮጵያ የአዲስ ዓመት መባቻ በልዩ ልዩ መጠርያዎች ይጠራል:: ብዙኃኑ ሕዝብ በዓለማዊው ገጽታ የሚያውቀው የዘመን መለወጫ እንቁጣጣሽ ሲሆን፣ በክርስቲያናዊው በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትውፊት “ርእሰ ዐውደ ዓመት” እና “ቅዱስ ዮሐንስ” ተብሎ ይታወቃል::

*ሀ) ርእሰ ዐውደ ዓመት*

ርእሰ ዐውደ ዓመት፣ የዓመት ዙረት መነሻ ዋና ዕለት ማለት ነው:: በኢትዮጵያ ቀመር መስከረም 1 ማለት ነው:: ሰባቱ ዕለታት ዐውደ ዕለት ተብለው 52 ሳምንታት ተመላልሰው ዐውደ ዓመትን ይሰጣሉ:: ለነርሱም መነሻ የሚሆነው መስከረም መባቻ ርእሰ ዐውደ ዓመት ይሰኛል::

ቅዱስ ያሬድ በመጽሐፈ ድጓው የዘመኑ ሁኔታን በተለይ የመባቻው ቀን መታሰቢያ በኃይለ ቃሉ ይገልጸዋል:: “ውስተ ርእሰ ዐውደ ዓመት፣ ተጽሕፈ ተዝካርከ ባርከኒ እንሣእ በረከትከ”፤ የስምህ መታሰቢያ በዓመቱ መጀመሪያ ተጽፏል:: በረከትህን አገኝ ዘንድ ባርከኝ መርቀኝ (38 ዓ.ቀኃሥ፤ 249)::

በአክሊሉ ገብረ ኪሮስ አገላለጽ መሠረት ዐውደ ዓመት የዓመት ቁጥር ማለት እንደሆነ መስከረም እንድንቀ ብሎ አቆጣጠሩ መጀመሩን ያሳያል። በሕዝቡም ዘንድ ዐውደ ዓመት ተጋንኖ መነገሩ የጨዋታ ሥነ ሥርዓት፣ የተድላ ደስታ ብዛት፣ የአለባበስ ወግና ሥርዓት ሁሉ ስለሚታይበት ነው (1978፡2)።

ርእሰ ዐውደ ዓመቱ በመስከረም ወር በተለይም መስከረም 1 ቀን ሆኖ መገኘቱ ልዩ አጋጣሚ መሆኑን መሠረት ይጠቅሳሉ። በኢትዮጵያ የዓመተ ዓለም አቆጣጠር መሠረት ዓመቱ በቀመሮች ከተከፋፈለ በኋላ ተረፈ ዘመኑ ለአበቅቴና ለመጥቅዕ መንሥኤ እንዲሆን፣ በፀሐይና በጨረቃ ጥምር አቆጣጠር ለሚገኙት አጽዋማትና በዓላት ዋና መሣሪያቸው መስከረም 1 ቀን ነው።

ለየክፍለ ዘመናቱና ለቀንና ሌሊት መተካከል (ዕሪና መዓልት ወሌሊት) በልዩ ልዩ ሰንጠረዦች ለሚገኙ የሥርዓተ ሐሳብ ወገኖች ሁሉ መስከረም 1 ቀን ማዕከላዊ ካስማ ነው። (1981:199)

(ለ) ቅዱስ ዮሐንስ

አዲስ ዓመት መባቻው ቅዱስ ዮሐንስ ተብሎም ይታወቃል። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ከሚታወቁት ሁለት ዮሐንሶች በተለይ መጥምቁ ዮሐንስ የተባለውን ይመለከታል። ሁለቱ በኢትዮጵያ አቈጣጠር ውስጥ የተሰጣቸው ድርሻ አለ። ሐዋርያውና ወንጌላዊው ዮሐንስ ከሦስቱ (ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ) ወንጌላውያን ጋር በየአራት ዓመቱ ለሚመላለሱት ዓመታት መጠርያነት ያገለግላል። መጥምቁ ዮሐንስ ግን የአዲስ ዘመን መባቻ መጠርያነትን ይዟል።

የዘመነ ወንጌል፣ የአዲስ ኪዳን ዘመን መነሻ ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚታወቀው፤ ከአሮጌው ዘመን ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲሱ ዘመን አዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ አዋጅ ያሰማው መጥምቁ ዮሐንስ ነው።

ከኢትዮጵያ አዲስ ዘመን መባቻ ጋር በምሥጢር ለማገናኘት ከዘመን አለዋወጥ ትእምርታዊ አካሄድ እንዲኖረው ሊቃውንቱ የመስከረም 1 ቀን ምትክ መጠርያ እንዲሆን አደረጉ።

መሠረት እንደጠቀሱት የመጥምቁ ዮሐንስ (ቅዱስ ዮሐንስ) ተግባር ለዘመነ ወንጌል በር ወይም መነሻ ሆኖ መገኘቱን በመረዳት የቤተ ክርስቲያን አበው የበዓላትን ድንጋጌ በወሰኑበት ጊዜ ነቢየ ልዑል የተሰኘው የመጥምቁ ዮሐንስ መታሰቢያ በዓል

የኢትዮጵያ ርእሰ ዐውደ ዓመት በሚሆን በመስከረም አንድ ቀን እንዲከበር አደረጉ (1981:200)።

በቅዱስ ያሬድ ድጓ መጽሐፍ "ውስተ ርእሰ ዐውደ ዓመት ተጽሕፈ ተዝካርከ - የዐውደ ዓመት ራስ በሚሆን ቀን መታሰቢያህ እንዲደረግ ተጻፈ።" ተብሎ የተጻፈው ይህንኑ ለማመልከት ነው። በባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት በየመጽሐፎቻቸው የርእሰ ዐውደ ዓመቱን ቀን ዕለተ ዮሐንስ እያሉ ሲይመውት ይገኛል።

ለምሳሌ በቀለ በ1986 ዓ.ም. ስለ ዘመን መለወጫ እንቁጣጣሽ ባቀረበችው ሐተታ መስከረም 1 ቀን በመጥምቁ ዮሐንስም፣ በወንጌላዊው ዮሐንስም እንደሚጠራ በመነን መጽሔት ላይ አገኘሁት ያለችውን ጽሑፍ በማስረጃነት አቅርባለች። የመጽሔቱ አዘጋጅ ሊቀ ሥዩማን አክሊሉ ገብረ ኪሮስ (እርሷ ለአለቃ ነቢየ ልዑል የቀረበ አድርጋዋለች) «እንቁጣጣሽና ዘመነ ዮሐንስ እንዴት አብሮ ሊገጥም ቻለ? ልዩነትስ አለውን» ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ «ዘመነ ዮሐንስ ስንል ሁለቱ ዮሐንሶች አሉና ዘመኑ በማንኛው ዮሐንስ እንደተሰየመ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። ዘመኑ የተሰየመው አራተኛ ውን ወንጌል በጻፈው በዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ነው» ብለዋል።

ጸሐፊዋ ያነጋገረቻቸው መምህር ሀብተ ማርያም ተድላ መስከረም መባቻ ከመጥምቁ ዮሐንስ ስም በመነሣት ቅዱስ ዮሐንስ መባሉን ገልጸውላታል። ሁለቱም ሊቃውንት ሁለት የተለያዩ ጉዳዮችን አንደኛው «ዘመነ ዮሐንስ»ን ሁለተኛው «ዕለተ ዮሐንስ»ን ገልጸዋል።

ለምሳሌ በጥናቷ የሰጠችው ድምዳሜ ሁለቱም ዮሐንሶች የመስከረም መባቻ መጠሪያ መሆናቸው፣ ሁለቱም ሊቃውንት ለአንዱ ጉዳይ የተለያየ አቋም እንዳላቸውና የተጻፈ ማስረጃ ቢኖር ኖሮ ሊቃውንቱ የሚሏቸው ምክንያቶች በተመሳሰሉ ነበር ብላለች።

መሠረታዊ ስህተትዋ ዘመንና ዕለትን መቀላቀሏ ነው። በኢትዮጵያ ትውፊት የመስከረም መባቻ በወንጌላዊው ዮሐንስ ስም ተጠርቶም፣ ተጽፎም አያውቅም። አክሊሉም ሆኑ ሀብተ ማርያም እውቀታቸውም፣ አቋማቸውም ተመሳሳይ ነው። ለዓመታቱ ወንጌላዊ ዮሐንስ፣ ለመባቻው ዕለት መጥምቁ ዮሐንስ መጠርያ ስለመሆኑ ሲያስተምሩም፣ ሲጽፉም ሲገልጹ የኖሩ ናቸው።

## 3.4 የርእሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ አከባበር

የርእሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ ክብረ በዓል በኢትዮጵያ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ሁሉ የሚከበር ነው:: ርእሰ ዐውደ ዓመት የዘመን መለወጫ በዓል መሆኑ ባለፈው ምዕራፍ ተገልጿል:: በዓሉ በቤተ ክርስቲያኒቱና በምእመናኑ ዘንድ እንዴት እንደሚከበር ሊቀ ጠበብት ጥበብ ይኄይስ እንደሚከተለው ይገልጹታል::

በየትኛውም ቤተክርስቲያን የዘመን መለወጫ አከባበር ከዋዜማ ጀምሮ እስከ ዕለቱ ድረስ ልዩና ሙሉ አገልግሎት የሚሰጥበት ነው::

በዋዜማው ጳጉሜን 5 ቀን (በሠግር ዓመት ዘመነ ሉቃስ ጳጉሜን 6) በየአጥቢያ ቤተክርስቲያን ማሕሌት ይቆማል:: የሚቆመውም ለበዓሉ የተዘጋጀው መዝሙርና መልክአ ዮሐንስ መጥምቅ ነው:: ማሕሌቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የጾም ቀን ካልሆነ በቀር ጧት ቅዳሴ ይገባሉ:: ምእመናንም ይገኛሉ::

ቅዳሴ ካበቃ በኋላ በዮሐንስ መጥምቁ ስም በታነፁት አብያተ ክርስቲያናትና በዕለቱ ንግሣቸው የሚከበረው እንደ ራጉኤል ባሉት በዓላት፣ ታቦተ ሕግ ወጥቶ ዑደት ይደረጋል፤ ይነግሳሉም የባሕረ ሐሳብ አዋጅም ይታወጃል::

በዚያን ጊዜ ያለው ማሕሌቱ ቀለሙ ዜማው የአገልግሎት ስልቱ መነሻ ዜማው የቅዱስ ያሬድ ድርሰቱ ይቃኛል:: ቀጥሎ ዝማሜው ከዚያ ቁም ጸናጽል መረግድ፣ ጽፋት ይደረጋል:: ሊቃውንቱ የሚቀኙዋቸው ቅኔዎች ሦስት ዋዜማና አንድ ሥላሴ ወይም ዘይእዜ ሲሆኑ በተለያዩ የያሬድ ዜማ ስልቶች (ግእዝ፣ ዕዝልና አራራይ) እንደአግባባቸው ያዜሙታል:: እነዚህም የአዲሱን ዘመን በዓል አስመልክቶ የሚደረሱ ናቸው::

ማሕሌት ፍችው፣ ምስጋና ዝማሬ መዝሙር ማለት ሲሆን የአገልግሎት ምስጋና ስምም ነው:: ከዋዜማው በኋላ ሌሊት የሚባለው ቀለም ከዚቅ ጋር የተያያዘ ነው:: ዚቅም የሚገባው ከመልክአ ዮሐንስ ላይ ነው (ካሴት ቍጥር 2)::

ቅዱስ ዮሐንስ የዘመን መለወጫ መሆኑን መረጃ የሚሰጥ የመልክዑ ደራሲ የደረሰለት ቅኔ አለ:: ቃሉም የበዓሉን ምስጢር የሚገልጽ ነው::

ሰላም ለሥዕርተ ርእስከ

እንተ ደለዋ እኂቴ

ወለርእስከ ሰላም ዘተመትረ

ከመ ናቡቴ፡፡

ርእሰ ዐውደ ዓመት ዮሐንስ

ወላዴ መጥቅዕ ወአበቅቴ፡፡

መብልዐ ዜና ፍቅርከ

ወነገረ ጽድቅከ ስቴ፣

ያስተፌሥሕ መላእክተ

ወሰብአ መዋቴ፡፡ (ደስታ፣ 1944፤4)

ምስጋና ለሚገባት

የራስህ ጠጉር ሰላም እላለሁ

እንደ ናቡቴ በግፍ የተቆረጠ

አንገትህን ሰላም እላለሁ፡፡

የዓመቱ መባቻ መነሻ የሆንክ ዮሐንስ

አበቅቴና መጥቅዕ አስገኝ ነህ፡፡

ጣፋጭ ምግብ የሆነው ፍቅርህና

የእውነት መጠጥ የሆነው ማስተማርህ

መላእክትንና ሟች ሰውን ደስ ያሰኛል፡፡

አበቅቴና መጥቅዕ የዓመት በዓላትና አጽዋማት የሚወጡበት መሣሪያዎች ስለሆኑ በሊቃውንቱ ታስበው በባሕረ ሐሳብ እወጃ ጊዜ የሚቀርቡት በዚያን ቀን ስለሆነ የመልክኡ ደራሲ ይህንን ቃል ተናግሮታል፡፡ እንደ ያሬድ ፈንታ ማብራሪያ አበቅቴ የሌሊት መባቻ የሚታወቅበት፣ መጥቅዕ በዓላትና አጽዋማት የሚወጡበት ነው፡፡

እነዚህ ሁለቱ መሣሪያዎች ባሕረ ሐሳብ በሚታወጅበት ጊዜ ሊቃውንቱ አስልተውና አጥንተው የሚያቀርቡዋቸው ናቸውና ደራሲው የሊቃውንቱን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ይህን መልክአ ደረሰ፡፡ መልክኡ ከተጸነጸለ፣ ከተመረገደ በኋላ ዝቅ ብሎ ከመልክኡ የሚገባ በመሆኑ ስሙ ዚቅ ተብሎ ተሰይሟል፡፡ የበዓሉ አንድ መገለጫ በወረብ የሚቀርበው ምስጋና ነው፡፡ መልክኡ እንዳለ ሳይሆን ገላጭ የሆነውን ንባብ ብቻ

"ርእሰ ዐውደ ዓመት ዮሐንስ

ወላዴ መጥቅዕ ወአበቅቴ" ይወርቡታል:: (ካሴት ቁጥር 3:2000)

ይህ በሊቃውንት ተወስኖለት በየዓመቱ የሚወረብ ወረብ ነው:: ወረብ ፣ መንፈሳዊ የካህን ዜማ በምላት ሳይሆን በከፊል የሚደረግ ነው (ደስታ፣ 1961:)::

ወረበ ሲልም ዜማን እንደ መሰለው አንዱንም ጠቅሶ ቀነቀነ ፤አዜመ ማለት ሲሆን፣ ዜማውም ንዑስ መረግድ፣ ዐቢይ መረግድ፣ ድርብ መረግድ፣ ጽፋት ይባላል:: የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ በከበሮና በጸናጽል አራተኛው ድፋት ግን ጭብጨባ ይጨመርበታል:: የካህናቱ ሽብሸባና ውዝዋዜ ራሱ ትእምርታዊ ነው:: በሌላ ምዕራፍ እንመለከተዋለን::

ከመልክኡ በኋላ ሊቃውንቱ በግጻዌ ሥርዓት መሠረት ለበዓሉ የሚስማማውን ምስባክ ይነግራሉ:: ምስባኩ ከመዝሙረ ዳዊት የሚወጣ ነው::

«ወትባርክ አክሊለ ዓመተ ምሕረትከ

ወይጸግቡ ጠላተ ገዳም

ወይረውዩ አድባረ በድው::»

«የምሕረትህን ዓመት አክሊል ትባርካለህ

ምድረበዳዎችም ጠልን ይጠግባሉ፤

የምድረበዳ ተራሮች ይረካሉ::» ማለት ነው፤(መዝሙር 64፡ 11-12)::

የዋዜማውና የበዓሉ ዕለት ማሕሌት ሒደት እንደሚከተለው ነው:: የአንድ በዓል ዋዜማ ከቀኑ 9ሰአት ጀምሮ የሚከናወን ሥርዓት ነው:: የበዓሉ ቀን በጾም ከዋለ ቅዳሴ የሚገባው እኩለ ቀን በ6ሰዓት ተኩል ነው:: የቅዱስ ቁርባን ሥርዓተ ቅዳሴ የሚከናወነው በነግህ ሲሆን የማሕሌቱ አገልግሎት ግን ከመንፈቀ ሌሊት ዝምሮ ሲከናወን ያድራል:: በግጻዌ መሰረት ከመዝሙረ ዳዊት የሚወጣ ጥቅስ ይኖራል:: እርሱም ምስባክ ይባላል:: ለበዓሉ የተመደበ ወንጌልም አለው::

ምስባክ ሰበከ ከሚለው ግስ ሲወጣ አስተማረ ማለት ሲሆን ቅድመ ወንጌል የሚታወጅ ነው:: የምስባክ ይዘት አንድ ተኩል ጥቅስን የያዘ ነው:: ማለትም ባለ ሦስት መስመር ሆኖ ሁለቱ የአንድ የጥቅስ ቁጥር ሆኖ ሦስተኛው የተከታዩ ቁጥር ከፊል ንባብ ነው:: በተመሳሳይ ዜማም ይዘመራል:: ዲያቆኑ መጀመሪያ ምስባኩን አሰምቶ ካወጀ በኋላ ምእመናን ይቀባበሉታል:: በተመሳሳይ ለሁለተኛ ጊዜ ይደግሙታል:: ሦስተኛው ላይ አካሄዱ ይለያል:: ዲያቆኑ ሃሌ ሉያ በማለት በጉልህ ድምጽ ይዘምራል::

ምስባኩ አካሄዱ እንዲህ ነው።

1 ዲያቆን ምስባክ ይሰብካል፣

2 ምእመናን ይቀበላሉ፣

3 ዲያቆን ይሰብካል፣

4 ምእመናን ይቀባበላሉ፣

5ኛው የጋራ ነው።

ዲያቆኑ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ መስቀል ይዞ መስበኩ ነቢያት እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠውን ተስፋ በጊዜያቸው ለመናገራቸው አምሳል ነው። ምስባኩ ሲሰበክ ዲያቆኑ ሁለት ጊዜ ሕዝቡ ሦስት ጊዜ በድምሩ አምስት ጊዜ መባሉ ስለ 5500 ዘመን ትንቢት ለመነገሩ ምሳሌ ነው። በ6ኛው ቁሱ ወንጌል ማለቱ በ6ኛው ሺሕ ጌታ ሰው ሆኖ ለማስተማሩ አምሳል ነው።

ዳግመኛም ይህ የዘመናት ቁጥር ከጥንተ ፍጥረት አንስቶ እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የነበረውን የዓመተ ፍዳ ዘመን ይወክላል። ዲያቆኑ ጃንጥላ ተይዞለትና መስቀሉን ይዞ ፊቱን ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ አድርጎ ሥርዓቱን ያከናውናል። እንደዘመን መለወጫና ትንሣኤን በመሰሉ በዓላት ምእመናኑ ምስባኩን በተራቸው ሲያዜሙ የከበሮ ድምጽ እንዲሰማ ይደረጋል። በሥርዓተ ማሕሌቱ፣ በወረቡ ካህናቱ ዝማሬና ሽብሸባ በሚያከናውኑበት ጊዜ የዜማው እውቀት ያላቸው ምእመናን ይቀበሏቸዋል፤ ሌሎች በጭብጨባና በዕልልታ ያጅቧቸዋል።

የዘመን መለወጫ ርእሰ ዐውደ ዓመት ዕለተ ዮሐንስ በዓልን በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን መስከረም 1 ቀን 1999 ዓ.ም. (ሰኞ) ተገኝቼ አክብሬአለሁ።

የቤተ ክርስቲያኒቱ አከባበር ለየት የሚያደርገው ታቦተ ሕጉ መንገሡና በዐውደ ምሕረቱ የባሕረ ሐሳብ አዋጅ መታወጁ ነው።

በዋዜማው ከተደረገው ሥርዓት ባሻገር በዕለቱ ቅዳሴ ሲቀደስ የዕለቱ ቅዳሴ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን 14 መደበኛ ቅዳሴያት መካከል አንዱ የሆነው ቅዳሴ ዘአትናቴዎስ ነው፤ በቅዳሴው ጊዜ የተነበበውና የተዜመው ምስባክ ከዋዜማው የተለየ ነው። እንዲህ ይላል:-

«ማህል ወርትዕ ተራከባ፣

ጽድቅ ወሰላም ተሳዕማ፣

ርትዕሰ እምድር ሠረጸት»

«ይቅርታና ቅንነት ተገናኙ

ጽድቅና ሰላም ተስማሙ

ቅንነት ከምድር በቀለች።»(መዝ. 84÷11-12)

በአዲስ ዓመት መባቻ ይቅርታና ምሕረት የሚገናኙት በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት መሆኑን ቤተክርስቲያን ታውጃለች። በመጥምቁ ዮሐንስ (ዕለተ ዮሐንስ) አማካይነትም የምሕረት ዓመት (ዓመተ ምሕረት) መገኘቱንም ታስተጋባለች። ቅዳሴው እንዳበቃ በ፫ ሰዓት ላይ በግቢው ውስጥ ያለው ሌላኛው ቤተ ክርስቲያን የደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ታቦተ ሕግ በታላቅ አጀብ መጥቶ ከልደታ ታቦተ ሕግ ጋራ አብረው በመሆን በልደታ ሕንፃ ቤተክርስቲያን ዑደት አደረጉ። በዑደቱ ልብሰ ተክህኖ፣ ድርብ ጥንግ የለበሱ ካህናት የሰንበት ትምህርት ቤተ መዘምራንና ምእመናን በዝማሬው ተሳትፈዋል። ዘመኑ መለወጡን የሚያውጅ የጥሩንባ ድምጽም ተስተጋብቶአል።

የባሕረ ሐሳቡን አዋጅ በታቦተ ሕጉ ፊት፣ ዐውደ ምሕረቱ ላይ ሆነው የቤተ ክርስቲያኒቱ መምህር ዘካርያስ አምባው አውጀዋል። በዓመቱ ውስጥ የሚውሉትን ተዘዋዋሪ አጽዋማትና በዓላትን ለሕዝበ ክርስቲያኑ ገልጸውታል።

የእወጃውን ገጽታና ይዘት በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን። ከእወጃው በኋላ የቤተ ክርስቲያኒቱ አለቃ መልአከ ሰላም ኀይለ ገብርኤል አሥርቶቱን ሲያሰሙ ቡራኬም ሰጥተዋል። በከበሮ በታጀበ ድምጽ ዘመነ ማርቆስ 1998 ዓ.ም. ማለፉን ዘመነ ሉቃስ 1999 ዓ.ም መተካቱን አብሥረዋል።

IES LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

## 3.5 በባሕረ ሐሳብ እወጃ ሰዓት የሚደረጉ ክዋኔዎች

በብሔራዊ ደረጃ የዘመን መለወጫ በዓል ቢከበርም በተለይ «ቅዱስ ዮሐንስ» በሚል መጠሪያ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ዐውድ ሰጥታ በታላቅ መንፈሳዊ ሥነሥርዓት ታከብራለች:: የዘመን መለወጫው የመንግስትም የቤተ ክርስቲያንም አዲስ ዓመት መባቻ ነው::

እንደ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጎርጎርዮስ ሐተታ በሀገሪቱ የክረምቱ፣ የጨለማው ወራት ተፈጽሞ የበጋው የጥቢው ብርሃን የሚፈነጥቅበት ወር መስከረም ነው:: መስከረም ድኅረ ክረምት እንደማለት ነው::

በሃይማኖታዊ ትውፊቱ ደግሞ ወደየቤተ ክርስቲያኑ እየሄደ ለዚህ ያደረስከኝ አምላኬ ተመስገን፣ የከርሞ ሰው በለኝ፣ ተርፎ ለሚቀረው እድሜ አትንፈገኝ ብሎ ፈጣሪውን ይለምናል:: ካህናቱም በቤተ ክርስቲያን ለበዓሉ የሚገባውን ስብሐተ እግዚአብሔር ያደርሳሉ:: ኋላም መምህሩ ወይም መሪጌታው ካባ ላንቃ ለብሶ መስቀሉን ይዞ በዓመቱ የሚውሉትን አጽዋማትና በዓላት ያውጃል፣ ባሕረ ሐሳብ ያወጣል:: ቀጥሎም ፍሬያተ ምድር፣ እጣኑ፣ ጣፉ፣ ዘቢቡ፣ ስንዴው፣ በመሶበ ወርቅ እየቀረበ ይባረካል (ጎረጎርዮስ፣ 1974: 143)::

የባሕረ ሐሳብ አዋጅና አሥርቆት ምን ምን እንደያዘ ከቤተ ክህነት ሊቃውንት ጉባኤ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስና ራድ አስረስ እንደሚከተለው ይገልጹታል::

> «መስከረም 1 ቀን ጾም ካልሆነ ከቅዳሴ በኋላ ከሰርሖተ ሕዝብ በፊት፤ ጾም ከሆነ ግን ከኪዳን በኋላ ከቅዳሴ በፊት፣ የባሕረ ሐሳብ ሊቅ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ፣ መጾር መስቀል ይዞ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ያውጃል:: ሀ) ዐጭር የሥነ ፍጥረትን ታሪክ ለ) የቅዱስ ድሜጥሮስን ዐጭር ታሪክና ሐ) የባሕረ ሐሳብን መሠረታዊ አመጣጥ በዐጭሩ አስረድቶ የዓመቱ አበቅቴና መጥቅዕ፣ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉባቸውን ዕለታት ያውጃል:: በመቀጠልም በአሥርቆቱ ሥነ ሥርዓት ዓመተ ዓለምን በፀሐይና በጨረቃ በመቀመር ከዚህም ዓመተ ፍዳንና ዓመተ ምሕረትን በመለየት ሠርቀ ሌሊትን፣ ሠርቀ ወርኅንና ሠርቀ መዓልትን በማብራራት ያሠርቃል::» (ካሴት ቁጥር 2)

የእወጃው ይዘት በየአብያተ ክርስቲያናቱ እንዳሉት መምህራን ዕውቀት የማጠርና የመርዘሙ ሁኔታ አለው:: አንዳንዱ በመግቢያው ላይ ያለውን የባሕረ ሐሳቡን ታሪክ ሲያሳጥር፤ ፈጽሞም የሚተወው አለ:: ሌላው ደግሞ ታሪኩን በሙሉ ዘርዝሮ በማስረዳት ይናገራል::

እወጃው በራሱ የተለያዩ ክፍሎች አሉት:: በመግቢያው ሰላምታ ካቀረበ በኋላ በፈጣሪ ስም ጸሎት ያደርጋል፤ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ ብሎ እምነቱን በሥላሴ ላይ መሥርቶ ይጀምራል:: በመጀመሪያው ክፍል በባሕረ ሐሳብ ምንነት መግለጫ በመስጠት አስፈላጊነቱን በተለይ ካህን ሊያውቀው እንደሚገባ አጽንዖት ሰጥቶ ያብራራል:: ቀደም ባሉት ዓመታት በልደታና በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት አጥኚው ከተከታተላቸው የባሕረ ሐሳብ እወጃዎች ያካተቱትን፣ የ1999 ዓ.ም. እወጃው ከመግቢያ ቀጥሎ ወደ ድሜጥሮስ ታሪክ በመግባቱ ከመነሻው ማንሳት የሚገባውን የሥነ ፍጥረት ታሪክ አልገለጸውም::

የድሜጥሮስን ታሪክ ከ“ሚስቱ” ጋር ያለው ተዛምዶ በሚገልጸው ክፍል ሁለት ውስጥ የአማርኛው ትረካ ሚስቱ ስሟ “ልዕልተ ወይን” እንደሆነ ይገልጻል:: ግብፃዊቷን እንስት በአበሻ ስም ይጠራታል:: በቃል እየተነገረ የመጣ በመሆኑ በሌሎች ተረኮች ስሟ ከወይን ጋር ያለውን ተዛምዶ ሳይለቅ በሌላ አጠራር “አስካለ ወይን” ይላታል::

የልደታው አዋጅ ነጋሪ በትረካቸው ውስጥ የድሜጥሮስን “ሚስት” ሁለቱን መጠሪያዎች አፈራርቀው ተጠቅመዋል:: ሁለቱ በ“ባልና ሚስትነት” አብረው ለ48 ዓመታት ሲኖሩ በግብረ ሥጋ እንደማይተዋወቁ ለዘመናት መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ከመኝታቸው እየተገኘ ክንፎቹን እያለበሰ ይጠብቃቸው እንደነበር ይተርካል:: ድሜጥሮስ ያለ ጊዜው ያፈራ ወይንን ከመብላት ይልቅ እንዲባረክበት ለፓትርያርክ ዩልዮስ ይዞ ሲሄድ ያልጠበቀው ነገር ያጋጥመዋል:: ጳጳሱ መድከሙ ከርሱ በኋላ ፓትርያርክ የሚሆነው ያለ ጊዜው ያፈራ ወይን ይዞ የሚመጣ መሆኑ ታውቆ ሕዝቡ ይህን ዐይቶ ድሜጥሮስን እንደትረካው ያልተማረውን ተሾምልን ይሉታል:: ይሾማል::

በአንደኛው ተረክ ዩልዮስ ድሜጥሮስን አግኝቶት የሚሾምላችሁ እርሱ ነው ብሎ ሲያርፍ፤ በሌላኛው ተረክ ደግሞ ሳይገናኙ አስቀድሞ በትንቢት መልክ ዩልዮስ፣ ድሜጥሮስ የሚባል ያለጊዜው ያፈራ ወይን ይዞ የሚመጣ እርሱን ትሾማላችሁ ብሎ ሳይገናኘው አረፈ ይላል:: በቃል እየተተረከ የሚመጣ አፈታሪክ የተለያየ አቀራረብና የራሱን እውነታ ይዞ ስለሚገኝ ልዩነት ይፈጥራል::

በትረካው ሦስተኛው ክፍል ላይ የሚገኘው የትንሣኤ በዓልና ሌሎች አጽዋማትና በዓላት በየዓመቱ የሚገኙበትን መንገድ ድሜጥሮስ እንዴት እንዳገኘ የሚገልጽበትና

መንፈስ ቅዱስ የገለጸለትን ሰባኤ ገብዮ ያገኘውን በተሾመ በ26 ዓመት እንደጻፈው ይገልጻል።

የስሌት ሁሉ ዐምዶች የሆኑትን መጥቅዕና አበቅቴን በብዙ ጥረት ያወጣው በመስከረም ጊዮርጊስ (23) ሰባኤ ገብዮ የጥቅምት ሚካኤል (12) ተገልጾለት እንደሆነ ይተርካል። በቀጣዩ ክፍል ዕለታት፣ ወራትና ዓመታት የሚሰፈሩበት፣ የሚቈጠሩበትን የአዕዋዳት (ዐውዶች) ስልት የቀረበበት መንገድ ነው። በእነዚህ አዕዋዳት መሠረት ዓመታቱን ከአዳም፣ ከኢየሱስ፣ ከሰማዕታት በመነሳት በልዩ ልዩ መነሻዎች ይቈጥራል፤ የልደታው አዋጅ ነጋሪ ዓመታቱን የቆጠሩት በዓመተ ዓለምና በዓመተ ምሕረት ብቻ ነው።

ቀደም ባሉት ዓመታት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት አጥኚው በተከታተላቸው እወጃዎች ዓመታቱ በፀሐይና በጨረቃ አቈጣጠር፤ በዓመተ ዓለም፣ በዓመተ ፍዳ፣ በዓመተ ምሕረት፣ በዓመተ ሰማዕታት የተገለጹባቸው አሉ።

አዋጅ ነጋሪው የ1999 ዓ.ም. አጽዋማትና በዓላት የሚውሉባቸውን ዕለታት ያወጁት ዓመታቱን በአበቅቴና በመጥቅዕ በቃላቸው በማለት ነበር።

አጥኚው በሌሎች ዓመታት ከተከታተላቸው እወጃዎች የልደታው የሚለየው ዓለም ያልፋል ተብሎ በሚታመንበት 2480 ዓ.ም. አጽዋማት የሚያዙበት፣ በዓላት የሚውሉበት ቀኖች በባሕረ ሐሳብ መታወጁ ነው። አዋጁ ዓለም ያልፍበታል ተብሎ እስከሚጠረጠርበት መጋቢት 30 ቀን 2480 ዓ.ም. የደብረ ዘይት ዕለት ድረስ ያሉትን አጽዋማትና በዓላት ዘርዝሯል። በቃል ሲተላለፍ እንደኖረው ምጽአተ ዓለም የሚሆነው በእኩሌታ ጾም የደብረዘይት ሰንበት ዕለት ነው።

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እንዳለው የድሜጥሮስ ትረካ ሁሉ በግብጽዋ የኮፕት ቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ የታሪክ ይዘት ያለው ትረካ አለ።

የእስክንድርያ 12ኛው ፓትርያርክ የነበረው ድሜጥሮስ ወደ ፓትርያርክነት የመጣበት መንገድ ቀዳሚው ፓትርያርክ ዩልያኖስ በመልአክ በራዕይ የተገለጸለት "የወይን ዘለላን የያዘ አንድ ሰው ወደ አንተ ይመጣልና እርሱን ይዘህ ጸሎት አድርግለት" ባለው መሠረት ከድሜጥሮስ ጋር መገናኘቱን ይተርካል። ያልተማረው ድሜጥሮስ በሰማያዊ ጸጋ ተሞልቶ ማንበብና መጻፍን አውቆ የቤተክርስቲያን መጻሕፍትንና ትርጓሜያቸውን ማጥናቱንም (ሐሳበ አበቅቴን ማዘጋጀቱ) ያወሳል (El-Kereza, 1994)።

ከኮፕቲክ ትረካ የኢትዮጵያው የሚጨምረውና የሚያሰፋው በርከት ይላል። የድሜጥሮስ ሚስት በኮፕቲኩ ትረካ የተጸውዖ ስም የሌላት ወይም ያልተጠቀሰላት

ሲሆን በኢትዮጵያው ግን ሀበሽኛ ስም ልዕልተ ወይን፣ አስካለ ወይን የተሰኙ ስሞች አላት:: የመኝታቸው ታሪክና መልአኩ ክንፉን ዘርግቶ ያደርግላቸው የነበረው ጥበቃ፣ በመልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ስለመሆኑ የሚያወሳ ተረክ በኢትዮጵያ እንጂ በኮፕቲኩ የለም:: [11]

የባሕረ ሐሳቡ ሊቅ እወጃቸውን እንዳበቁ የደብሩ አለቃ መልአከ ሰላም ኃይለ ገብርኤል የአሥርቆት (የማውጣት) ሥርዓት ዓመታቱን በመቀመር፣ ሠርቀ ሌሊቱንና ሠርቀ ወርኅን፣ ሠርቀ መዓልቱንም በማውሳት እንዲህ አሥርቀውታል::

> ሃሌ ሉያ በዘንዜክር ሐሳባተ ሕገ ወዓመታቲሁ ወትእዛዛቲሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ሀሎነ በዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ ያብጽሐነ እስከ ዘመነ ዮሐንስ ዜናዊ በሰብዓ ምእት ወአርብዐ ምእት ፺ወ፱ ዓመተ ዓለም፣ በ ፶ ምእት ወ፭ቱ ምእት ዓመተ ኩነኔ ወበ ፲ወ፱ቱ ምእት ፺ወ፱ ዓመተ ምሕረት፤ ዮም ሠረቀ ለነ ወርኃ መስከረም ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ወርኃ ጥቅምት:: በሰላመ እግዚአብሔር አሜን:: አሚሩ ሠርቀ መዓልት፤ ፲፬ ሠርቀ ሌሊት፤ ፲፰ ሠርቀ ወርኅ ፮ ጥንተ ዮን ዮም ኮነ በዛቲ ዕለት ዘተበሥረ በአፈ ካህን ኀሩይ ወለባዊ::

የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕጉንና ትእዛዙን ዓመታቱንም በምናስብበት በዛሬው ቀን ከወንጌላዊው ሉቃስ ዘመን ወደ ዜናዊው ዮሐንስ ዘመን እንዲያሸጋግረን ሃሌ ሉያ እያልን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን:: በ7499 ዓመተ ዓለም፣ በ5500 ዓመተ ኩነኔ፣ በ1999 ዓመተ ምሕረት ዛሬ ቡሩክ የመስከረም ወር እንደባተልን እንዲሁም የእግዚአብሔር ሰላም ከጥቅምት ወር መባቻ ያድርሰን አሜን:: የመዓልት ብተት 1፣ የሌሊት ብተት 14፣ የጨረቃ ብተት 18፣ ጥንተ ዮን 6:: ይህ ኅሩይ ለባዊ በሆኑ ካህን እንደበት በዛሬው ቀን የተነገረ ነው::

---

11 ዲሚትር በግሪክ ሚቶሎጂ ካሉት ሴት አማልክት አንዷ ስትሆን የእርሻ፣ ዘር (ሰብል) አምላክ ተደርጋ ትወሰዳለች:: ከድሜጥሮስ ተረክ ጋር የሚዛመድ ጉልህ ነጥብ ማግኘት ባልችልም መያያዣ ቀጭን ክር ያለ ይመስለኛል:: በ <Cliffs Notes on Mythology> (1973) እንደ ተጻፈው የዲሚትር ተረክ ከሰብል (ገብስ) ልደትና ኅልፈት ጋር የሚያያዝ ነጥብ አለው:: በየዓመቱ ገብስና ወይን (ሰብል) ዳግም እየተወለዱ ካለመኖር ወደመኖር እየመጡ የሚታዩበት ሁኔታ ለሰብአዊ ምውታን የትንሣኤ ተስፋ ናቸው:: የወይን ገበሬ የነበረው ድሜጥሮስ ለሐሳበ አበቅቴ መወለድ መሠረት ያደረገው ሦስተኛው ቀን ማክሰኞ በሥነ ፍጥረት አትክልት፣ አዝርእት ዕፅዋት የተፈጠሩበት ነው:: በሐሳበ ድሜጥሮስ ተስፋ ትንሣኤ የሚታወቅበት ይሆናል:: ፍጥረታቱን ለማስተማሪያና ለማሳሰቢያ ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ ፈጥሮአቸዋልና:: «በ እምኔሆሙ ለምሀሮ፣ ወበ እምኔሆሙ ለተዘክሮ» እንዲል መርሐ ዕውር::

## 3.6 የባሕረ ሐሳብ እወጃ ከፎክሎር ተግባራት አኳያ

ፎክሎር ልዩ ልዩ ተግባራት ይኖሩታል። አምስት ዐበይት ክፍሎች የመግለጥ፣ የማጠናከር፣ የመትከል፣ የማምለጫ፣ የማስተማርና የመግታት የመቆጣጠር ተግባራት እንዳሉት ፈቃደ ይገልጻል (1991:17)። የባሕረ ሐሳብ እወጃ በእነዚህ የሥነ ቃል ዐበይት ተግባራት ሊገለጽ የሚችል መሆኑን ከክዋኔው መረዳት ይቻላል። በእወጃው ሰውና ሌሎች ፍጥረታት መቼ እንደተፈጠሩ የሚገልጽ ትረካ አለው። ለዚህም በሰው ልጅ ለሚፈጠረው ጥያቄ ምላሽ ይሆናል። የዓለም አፈጣጠርና የሰውን ልጅ ድቀት ለመረዳት በታሪካቸው ወይም በአፈ ታሪካቸው የተረዱትን በየጊዜው በተረኮቻቸውና በባህላቸው እያጠናከሩ ይቀጥላሉ። አዳምና ሔዋን በኃጢአት በመውደቃቸው ምክንያት ለ5500 ዓመታት በዓለም ፍዳ ያለፈው ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በመስቀሉ ሰላምን ከሠራ በኋላ በዓመተ ምሕረት ዓለም መለወጡን ይተርካሉ።

ሥነ ቃላዊ በሆነው አተራረክ ካህኑ ፊቱንም በርሱ ዘንድ ለመትከል ይረዳል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ሥላሴያዊ ይትበሃልን የሚከተሉ በመሆናቸው በዕለታዊ ሕይወት ስመ ሥላሴን ያነሳሉ። ያማትባሉ፣ ስሙን ይጠራሉ። አዋጅ ነጋሪው ካህንም የሚያንጸባርቀው ይህንኑ ነው። በ1999 ዓ.ም. የልደታው አዋጅ ነጋሪ በጊዜ ምክንያት እወጃቸውን ስላሳጠሩት በሥላሴ ላይ የተመሠረተውን አነጋገር ሳይገልጹት አልፈዋል። ይትበሃሉን ለማሳየት ግን አጥኚው በ1993 ዓ.ም. በቅድስት ሥለሴ ካቴድራል የተከታተለውን እወጃ እዚህ ላይ መጥቀስ አስፈልጓል። የሥላሴው ካህን ማወጅ የጀመሩበት መንገድ ለምዕመናንና ካህናት ተአምኖ ሥላሴን በሚያጸናበት በሚተክልበት መንገድ ነው። እንዲህ አሉ፤

> በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን»፣ በአብ ስም አምኜ አብን ወላዲ ብዬ፣ በወልድ ስም አምኜ ወልድን ተወላዲ ብዬ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜ መንፈስ ቅዱስን ሠራፂ ብዬ፣ ምንም ለአጠይቆተ አካላት እግዚአብሔር በአካል ሦስት ብዬ ብማር ባስተምር በባሕርይ፣ በኅልውና በፈቃድ በአገዛዝ አንድ የባሕርይ አምላክ ብዬ አምኜ አጽዋማትና በዓላት የሚገቡበትና የሚውሉበት ወርና ቀን ወስኖ ለመናገር ረድኤተ እግዚአብሔርን ምርኩዝ አድርጌ ተመርኩዤ በፍቅር በትህትና ጸንቼ ከፊታችሁ ቆሚያለሁ።

የባሕረ ሐሳብ እወጃ አንደኛው ግቡ ትውፊታዊውን ዕውቀት ከሕዝብ ማስተላለፍ ነው። ጊዜን መስመር ማስያዝ በቤተ ክርስቲያንና በምዕመናን ሕይወት ውስጥ ተሳስሮ እንዲዘልቅ ለማድረግ ያለፈ ነገርን በመተረክ ያቀርባል።

እወጃው እንደቀመሩ ሁሉ የዛሬን (የዕም)፣ የትናንትን (ትማልም)፣ የነገን (ጌሰም) አስተባብሮ የያዘ ነው። የዘመን መለወጫው ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር የተያያዘ መሆኑ፣ መከበር ያለበትም በክርስቲያናዊ መንገድ መሆኑን ያጠይቃል።

እወጃው ምእመናኑ ዓመቱን እንዴት መኖር እንዳለባቸው ክርስቲያናዊ ሕይወቱን እንዴት መጠበቅ እንዳለበት፣ በዓመት ውስጥ የበሎት ምግቦች የሚበሉበት፣ የጾም መባልዕት የሚስተናገዱበትን ጊዜ ለይቶ ያሳያል። መንገድ ይጠርጋል። የማስተማር ተግባርም አለው። ባሕላዊ እውቀቱን ለማስተላለፍ ተተኪንም ለማዘጋጀት ይረዳል። ፋሲካን ለማክበር ከመዘጋጀት በፊት መጾም እንደሚገባ በምሳሌያዊ አነጋገር ያስገነዝባል። «ሳይጾሙ ፋሲካ፣ ሳያዝኑ ደስታ የለም» እንዲል።

ኅብረተሰቡ ዕለትን ከቅዱሳን መታሰቢያ ጋር አቆራኝቶ የሚያይበት ልማድ ስላለው ሲገለጽም ከቁጥር ይልቅ መታሰቢያ ከተደረገለት ቅዱስ ወይም ጻድቅ ጋር ያዛምደዋል። ቁጥር ረቂቅ ነገር ነው። በቅዱሳን የተሰየሙ ቀናት ከቁጥራቸው ይልቅ መታሰቢያ የተደረገለት ቅዱስ ጐልቶ ይታይበታል። 12 ቁጥርን ለቀን መጥሪያ ከማዋል ይልቅ በሚካኤል ስም መጥራት ግዘፍ ያለው እይታ አለው። የመልአኩ ምስል፣ ጠባቂነቱ፣ ተዓምር አድራጊነቱ ስለሚመጣ ትእምርታዊ ገጽታው ጐልቶ ይመጣል። የቀኑ ቅዱስ የሚለምኑት መልአክ ስለሚሆን ዕለቱ ከአንዝ ይልቅ አካል ይሆናል። አስተምህሮታዊ ፋይዳም ይኖረዋል። ኅብረተሰቡ የሚካኤል ማኅበርተኛ ስለሚሆንም ከዕለታዊ ሕይወቱ ጋር ይያያዛል።

ስለዚህ የ1999 ዓ.ም. አዋጅ ነጋሪው ጾመ ነነዌ የሚገባበትን፣ ሆሳዕና የሚውልበትን ቀን ሲናገሩ ወሩንና ቁጥሩን ብቻ ገልጾ ማለፉን አልወደዱትም። እንዲህም አሉ፤ «ጥር 21 ቀን የአስተርዕዮ ማርያም ዕለት ጾመ ነነዌ ሆነ። በዓለ ሆሳዕና መጋቢት 23 ቀን የመጋቢት ጊዮርጊስ ሆነ።»

የአስተርዕዮ ማርያም ዕለት ጾመ ነነዌ ይያዛል ማለታቸው ወር በገባ ሁሌ 21 ኛው ቀን የማርያም መታሰቢያ ቢሆንም የጥሩ ግን ለየት የሚለው በዘመነ አስተርእዮ (ኤጲፋንያ) ውስጥ መሆኑ ነው። የትኛዋ 21 ለሚለው በአስተርእዮ ውስጥ የምትውለዋ ብሎ ለመመለስ ይረዳል። ይህም ስርዓትን የመተከል ልማድ ይሆናል።

አዋጅ ነጋሪው በትረካው ፍሰት ውስጥ ፋሲካ በሚያዝያ በሚውልበት ጊዜ የማይነገረውን በ1999 ዓ.ም. ግን በመጋቢት ውስጥ ስለዋለ አንድ ብሂል በጣልቃ ገብነት አስገብተዋል።

ጠንቀቅ በሉ፣ ሕርመትን አዘውትሩ በማለት በእወጃው ለየት ያለ ነገር መኖሩን ይጠቅሳሉ። ታዳሚው የሚሞላው ብሒልም ተንሀባርቋል። የዓመቱ ትንሣኤ መጋቢት

30 መሆኑን ካህኑ ሲያውጁ በማስከተል አድማጭ እንዲተረጉማት የተዉለት ሐረግ ለየት ባለ ድምፀት «አሀ! ሚያዝያ በሙሉ ተበልቷል ማለት ነዋ» በማለት የተናገሯት አለች:: ይህም በቅብብሉ «ሚያዝያ ከተበላ ሰው ተበላላ» ከሚለው ብሂል ጋር ይያያዛል::[12]

አዲስ መስመር በተመለከተ የሰው ልጅ በጂኦግራፊ ከተከለለው ከጠባብ መንደሩ በጥቅሉም ከምድራዊው ቁሳዊ አጥርና ድንበር በምናቡ እንደሚያመልጥ በፈቃደ ተጽፏል (1991:18)::

ከዚህ ጋር የሚዛመድ ከጊዜና ዘመን አኳያ የመውጣት አቡቀለምሲሳዊ (አፖካሊፕቲክ) እይታ እንዳለ ከባሕረ ሐሳብ እወጃው ማግኘት ይቻላል:: ዘመናትን መቆጣጠሩ፣ መነሻውንና መድረሻውን መረዳቱ፣ በምጽአት ቀን ከሚድኑት ሕያዋን (በጎች) ጋራ ለመሳተፍ እግዚአብሔር ወሳኝ በመሆኑ ከአሸናፊው ወገን ለመሆን ማምለጫ ውስጥ ይገባል:: 1999 ዓ.ም. ላይ ሆኖ የምጽአት ዘመን ይሆናል ተብሎ በሚገመተው 2480 ዓ.ም. ላይ ማረፍ ከጊዜው ቅንብብ አልፎ ማምለጥ ነው:: የስምንተኛው ሺሕ ማክተሚያ ሲያስበው ከቦታና ከጊዜ ወጥቶ መነጠቁ፣ ማምለጫ ይስተዋላል::

የልደታው አዋጅ ነጋሪ የዘመን እወጃ ያደረጉት ለባተው ዓመት ብቻ ሳይሆን ዓለም ታከትማለች ተብሎ ለሚታሰበው 2480 ዓ.ም (7980 ዓ.ዓ.) ጭምር ነው:: የዚያን ዘመን አጽዋማትና በዓላቱ የሚውሉበት ዕለታት ሲያውጁ እንደያዙት ዓመት ምሉዕ አይደለም:: ከርእሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ ተነሥተው እስከ እኩሲታ ጾም ወይም በዓለ ደብረ ዘይት ነግረው አቆሙት፤ እሑዱ የደብረ ዘይት ዕለት ምጽአት የሚሆንበት ተብሎ በመታመኑና ከዚያም በኋላ ሁሉም ነገር አልቦ ስለሚሆን ለማይኖር ነገር አላወጁትም፤ እንዲህ ነገሩት::

> የደብረዘይት ተውሳክ 11 እና መባጃ ሐመር 18 አንድነት ሲጠቀለሉ 29 ሆነ:: መጋቢት እሑድ ይብታል:: ከእሑድ እስከ እሑድ 8 ፣ ከእሑድ እስከ እሑድ 15፣ ከእሑድ እስከ እሑድ 22፣ ከእሑድ እስከ እሑድ 29 ሆነ ይኋል:: የመጋቢት በዓለ እግዚአብሔር መጋቢት 29 ደብረ ዘይት ይውላል:: ያን ጊዜ

---

[12] በቅዱስ ዮሐንስ እለት የባሕረ ሐሳብን እወጃ መስማት ከብዙ አንጻር እርካታን የሚያጎናጽፍ ነው:: በዕድሜና በጤና ምክንያት መገኘት ለማይችሉ በስሚ ስሚ ስለ ዕለቱ በዕለቱ በቤተክርስቲያን የታወጀውን በተለይ ጾም የሚገባበት በዓሉ የሚውልበት ስለሚነገራቸው እንደተገኙ ያህል በመቁጠር ይደሰታሉ:: በቅርቡ ከሕይወት የተለዩ አንዲት ባልቴት በየዓመቱ የባሕረ ሐሳቡን እወጃ በማዳመር አቀርብልኝ ብለው ነበር:: በተለይ የሚታወሰኝ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም የትንሣኤ በዓል መጋቢት ፳፰ እንደሚውል ስነግራቸው «ውይ ውይ ሚያዝያ ሙሉውን ተበላ አትለኝም እንዴ፤ መከራችን መብዛቱ 'ሚያዝያ ከተበላ ሰው ተባላ' ይባላል» አሉኝ:: በዘመኑም በሥርዓት ለውጥ ለማድረግ የጦርነት ፍልሚያ ይካሄድበት ስለነበረ መገጣጠሙ ገረመኝ::

ይህ ዓለም ተለውጦ፣ ይህ ዓለም ጠፍቶ አልቦ ወርኅ ወኢዐሐይ፣ ኢክረምት ወኢሐጋይ - ክረምትና ሐጋይ፣ ሌሊትና መዓልት (ጨረቃና ፀሐይ) መፈራረቅ ያቆማሉ።

በባሕረ ሐሳቡ እወኛ ጊዜ ስለ ድሜጥሮስ የሚቀርበው ትረካ የቀመሩን የትመጣ ያሳያል። ስለቀን አቆጣጠር ለማወቅ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አስፈላጊነቱን፣ መልአኩ ሁለቱን ተጋቢዎች መጠበቁ ታማኝነትና ምንኩስናን ማስተማሩ ያሳያል። በተለይም ሥርዓተ ምንኩስናን ለሚያራምዱት ኦርቶዶክስና ካቶሊክ ጠቃሚ ምልክታቸው ስለሆነም ሥነ ቃሉ ሃይማኖታዊ ተግባርም ያመላክታል። ዐዋጁ የሚታወጅ ሆኖ ምእመኑ ታዳሚ የሚሆንበትና አዎንታዊ አጸፋ የሚመልስበት ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ምዕራፍ አራት

# የርእሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ በዓል ትእምርቶች

## 4.1 የትእምርት ምንነት

ሰዎች ማኅበረሰብን ይመሠርታሉ፡፡ በሚኖራቸውም ተራክቦ ሃይማኖትና ባህልን የሚገልጹበት ትእምርትና ፍችም ይኖራቸዋል፡፡ ትእምርት በኪዳነ ወልድ ክፍሌ ምልክት፣ አምሳል፣ አብነት፣ ዐላማ፣ ታምራት ጉድ ነው (1948:228)፡፡

ትእምርት ለአንድ ነገር ወይም ሐሳብ ውክልና የሚሰጥ ነው፡፡ አንዳንድ ትእምርቶች እንደ ሰንደቅ ዓላማና የትራፊክ ምልክቶች በግዘፍ የሚታዩ ሲሆን፣ ሌሎች ሙዚቃና የንግግር ቃላት በድምፅ የሚገለጹ ናቸው፡፡ ትእምርቶች በዐውደ ሃይማኖት ውስጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ምእመናኑ ይግባባሉ፤ መረጃም ይለዋወጣሉ፡፡ ኩደን እንደጻፈው ትእምርት ሕይወት ያለውም ይሁን ግዑዝ አንድ ነገር የሚወከልበት ነው፡፡ ይህም ለተለየ ሁኔታ ግዘፍ የሚነሳበት ብሎም ብርሃን የሚሰጥበት ነው፤ እንቅስቃሴ ወይም ድርጊያዎች እና አካላዊ ውዝዋዜዎችም ትእምርታዊ ናቸው፡፡ ይበልጥኑ ሃይማኖታዊና የዘር ጊዜ ሥርዓቶች (rites) በትእምርታዊ እንቅስቃሴዎችና አካላዊ ውዝዋዜዎች የታደሉ ናቸው፡፡ በተለይ በግእዝ ሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ በጉልህ የሚታይ ነው፡፡ (1998፣884-85)

ኅብረተሰቡና ሃይማኖቶች ሥዕላዊ ትእምርቶችን በመጠቀም ራሳቸውንና መሠረተ ሐሳባቸውን ለመግለጽ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ አብዛኞቹ ሃይማኖቶች እምነታቸውን የሚወክሉባቸው ትእምርቶች አሏቸው፡፡ በዊትኒ ስሚዝ (1994-1095) እንደተገለጸው መስቀል የክርስቶስን ሞትና የክርስቲያኖችን እምነት፣ ማኅተመ ሰሎሞን ደግሞ የአይሁዶችን አስተምህሮ ይወክላል፡፡

ብዙዎቹ በዓላት፣ ወታደራዊ ሰላምታዎችና ሃይማኖታዊ ምስጢራት ትእምርታዊ ገጽታ አላቸው፡፡

## 4.2 በባሕረ ሐሳብ እወጃ ላይ የሚታዩ ትእምርቶችና ውክልነታቸው

በርእሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ ዕለት በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በሚኖረው የባሕረ ሐሳብ እወጃ ወቅት በተለይ በዐውደ ምሕረት ንግሥ በሚኖራቸው የሚታዩት ትእምርቶች በርካታ ናቸው፡፡ ትእምርቶቹ በካህናትም ሆነ በምእምናኑ ዘንድ ትዝታና ጉጉትን፣ መንፈሳዊ ሐሴትን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በዓለ ንግሥ፣ በዐውደ ምሕረቱ በተከናወነው የዘመን



▪ ታቦተ ሕግ



- ቁጠማና ዘመን



- ኅብረ ዝማሬ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

መለወጫ አከባበር የታዩት ትእምርቶች ዝማሬ፣ ሽብሸባ፣ ታቦተ ሕጉ፣ መስቀል፣ የጢፍ(ሻማ) ብርሃን፣ ጥሩምባ፣ ቄጤማ (አደይ አበባ) ወዘተ. ናቸው።

ሀ) ቅዱስ ዮሐንስ

የዘመን መለወጫ ዕለቱ መጠርያው "ቅዱስ ዮሐንስ" (ዕለተ ዮሐንስ) በራሱ ትእምርታዊ ነው። በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያው ክፍል እንደተገለጸው በድምፅ ከሚገለጹት የንግግር ቃላት አንዱ መጠርያ በመሆኑ፣ የቅዱስ ዮሐንስ ውክልነቱ ተጠቃሽ ነው። ዮሐንስ በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት መካከል ያለ መሸጋገሪያ በመሆኑ መባቻው የርሱ ቄምሳል ሆኗል ። ዕለተ ዮሐንስ የዓመት መባቻ በጥንተ ዕለት (ከእሑድ ተነሥቶ ቅዳሜ የሚያበቃ)፣ በጥንተ ቀመር (ከማክሰኞ ተነስቶ ሰኞ የሚያበቃ)፣ በጥንተ ዮን (ከረቡዕ ተነሥቶ ማክሰኞ የሚያበቃ) ይገለጻል። እነዚህ ሦስት ጥንታት በባሕር ተመስለው ይቀርባሉ። ዘመኑን በባሕር ለመመሰሉ "ባሕረ ሐሳብ" ን ልብ ይሏል። "ሠለስቱ ጥንታት ሀለዉ ውስተ ባሕር" «ሦስት ጥንታት በባሕር (በዘመን) ውስጥ አሉ» እንዲል!


ለ) አደይ አበባና ቄጠማ

አደይ አበባ ጠንካራው ክረምት አብቅቶ መስከረም ሲጠባ መስኩ ሁሉ በአደይ አበባ የሚያሸበርቅበትን ሁኔት የሚደሳይ ነው።የክረምት ክፍለ ዘመን እየተገባደደ ወደ መፀው (የአበባ ዘመን) የሚተላለፍበትን መንገድ የሚጠቁም አምሳል ነው።

በኦሪት እንደተጻፈው በኖኅ ዘመን በዓለም የጥፋት ውሃ ደርሶ ነበር። ኖኅ ከነቤተሰቡ በመርከብ ተጠልሎ የዳነ ሲሆን፣ ማየ አይኅ (የጥፋት ውሃ) መጉደሉን ማረፊያ መኖሩን እንዲያረጋግጡለት ከተላኩት አዕዋፍ አንዷ ርግብ ነች። በመጀመሪያ ጉዞዋ ማረፊያ በማጣቷ ስትመለስ፣ ዳግመኛ ስትላክ የንፍር ውሃው እንደጎደለ ባንዳንድ ቦታ ላይም ያገኘችውን ቄጠማ ምልክት ይሆናት ዘንድ ለኖኅ የምስራች ብላ እንዳመጣችለት ሁሉ በዘመናት ለውጥ በቅዱስ ዮሐንስም ዕለት ቄጠማ መጎዝጎዙ ክረምቱ የማብቃቱ አዲስ ዘመን የመባቱ አርአያ፣ ምሳሌ ነው።

ሐ) ታቦተ ሕግ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለስርዓተ አምልኮ ከምትጠቀምባቸው ንዋያተ ቅድሳት ዋነኛ ታቦተ ሕጉ ነው። በበዓላት ንግሥ ጊዜ ታቦተ ሕጉ በዐውደ ምሕረቱ ይገኛል። በዘመን መለወጫ ቅዱስ ዮሐንስ በዓልም በዓለ ግሥ በሚኖርባቸው አብያተ ክርስቲያናት ዑደት ይኖራል። የታቦተ ሕጉን ትእምርት በተመለከተ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ



- እወጃውና ኅብረተሰቡ



- አደይ አበባና ዘመን

እንደገለጹት (ካሴት ቁጥር 2) በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ታቦተ ሕጉ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ጸዋሬ ታቦት (ታቦቱን የተሸከመው) ካህን የጸወርተ መንበር ኪሩቤል ምሳሌ ነው።

መ) ጥሩምባ፣ ደወልና ከበሮ

ታቦተ ሕጉ ዑደት በሚያደርግበት ጊዜና የባሕረ ሐሳብ እወጃ በታወጀበት ሰዓት የጥሩምባ፣ የደወል(መጥቅዕ)፣ የከበሮ ድምጽ መስማቱ የራሱ ምሳሌ አለው።

በሊቀጠበብት ጥበብ ማብራሪያ (ካሴት ቁጥር 2) መጥቅዕ የሚደወለው አንድ የተፈለገ ነገር ለመሥራት ሲፈለግ ነው። በደወል ድምፅ ሰው እንደሚሰበሰበው ሁሉ ከዓመት እስከ ዓመት የሚውሉ አጽዋማትና በዓላት ሁሉ በአንድ አዋጅ ውስጥ በመጥቅዕ አማካይነት ይሰበሰባሉ። ጥሩምባ መነፋቱም ዘመነ ማርቆስ 1998 ዓ.ም. አለፈ፤ ዘመነ ሉቃስ 1999 ዓ.ም. ተተካ ብሎ በራሱ አመል ሲገልጥ ነው። ከበሮውም ደወሉም ሁሉም የምሥራች መግለጫ ነው።

ባለፈው ዓመት ይመግብ የነበረው ወንጌላዊ ምግብናውን ፈጽሞ ለሚተካው ወንጌላዊ ምግብና ማስረከቡን ለመግለጥ በከበሮና በነጋሪት በእንቢልታና በደወል በቃጭልም በእልልታና በጭብጨባ ዐዋጅ ይደረጋል። ይህም በመስከረምና ጥቅምት መካከል ከሚውለው አይሁድ በዓለ መጥቅዕ (አዲስ ዓመት) ጋር ይዛመዳል (ዘሌዋ.23፣23)።

ሠ) ሥነ ስቅለትና መስቀል

ሥነ ስቅለትና መስቀሉ በቤተክርስቲያን ሁሌም የሚኖር ነው። በባሕረ ሐሳብ እወጃም ሊቀ መጾር መስቀል ይዞ ይገኛል። ዐውዳዊ ፍቹ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛ መሆንን ከዓመተ ፍዳ ወደ ዓመተ ምሕረት መሸጋገራችንን ያም የሆነው ከ5500 ዓመት በኋላ ጌታ ተወልዶ፣ ተጠምቶና ተሰቅሎ በትንሣኤው የምሕረት ዓመት ማምጣቱን ያጠይቃል።

ረ) ሻማ (ጧፍ)


ሻማ (ጧፍ) በቤተ ክርስቲያን በዐውደ ምሕረት ካህናቱም ሆኑ ምእመናኑ ለኩሰው ይታያሉ። አንድም ክርስቲያኖች ዘመናትን የሚያለዋውጡበት ኢየሱስን ከብርሃን ጋር ያዛምዱታል። የዓለም ብርሃን ብለውም ይጠሩታል። አንድም ዘመኑ ወደ አዲስ ብርሃናማ ብሩ ዘመን መለወጡን ምሳሌ ያደርጋል። ከባሕረ ሐሳብ እወጃ በኋላ በአሥርቆት ጊዜ በሚኖረው ቡራኬ በመሰበ ወርቅ የሚቀርቡት ስንዴና ወይን ዕጣንና ጧፍ የአዲሱን አመት አዝመራ በረከት ያመለክታሉ። በትንሽ መሰበ ወርቅ በዚያን ቀን በዓመቱ መባቻ ጸሎት የሚደረግባቸው ከዓመት እስከ ዓመት ድረስ መገልገያ ለሚሆኑ መሳሪያዎች (ንዋያት) ሁሉ ጸሎት ነው።



▪ ሽብሸባ



▪ ጥሩንባና ዘመን




- ኅብረ ዝማሬ



- ዘመ'ንና ከበሮ



- ዘመነ ሉቃስ 1999 ዓ.ም.



- ጧፍና ዘመን

ሰ) ቅዱሳን

በኢትዮጵያ ባሕረ ሐሳብ ውስጥ የቅዱሳን ስም በትእምርትነት ይገኛል። በቀዳሚው ምእራፍ እንደተገለጸው የአራት ዓመት ዐውድ በወንጌላውያን ተሰይሟል። እያንዳንዱ ዓመት በሐዲስ ኪዳን ቀኖና ቅደም ተከተል መሠረት በማቴዎስና ማርቆስ፣ በሉቃስና ዮሐንስ ስም ተሰይሟል። በኅብረተሰቡ በተለይም በገጠሩ ዘንድ ከቁጥር ጭማሬ ይልቅ የወንጌላውያኑ መመላለስ ያረካቸዋል። ማቴዎስ ዞሮ መጣ ይላል። በወንጌላውያኑ ስም በመመርኮዝም ምሳሌያዊ ንግግር «በዮሐንስ እረስ በማቴዎስ እፈስ» «ሉቃስ በሊዕኻ ድቃስ፣ ተተሓሒዝካ ምልቃስ» (ሉቃስ በልተህ መተኛት፣ ተያይዘህ መላቀስ) ብሎ ፈጥሮለታል። ስድስተኛዋ ጳጉሜን በዘመነ ሉቃስ መጨረሻ የምትውል በመሆኑ ሠግረ ዮሐንስ ትባላለች። ምክንያቱም ከሉቃስ በኋላ ዮሐንስ ተራምዶ የሚገባባት በመሆኑ በእርሱ ትጠቀሳለች።

በአዲስ ዓመት መባቻ ያለው ልማዳዊው የመልካም ምኞት መግለጫ የዘመን ትእምርት ባሕር መሆኑን ያጠይቃል። «እንኳን ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ በደህና አሸጋገረዎ» መሻገር ባሕርን ወንዝን ይመለከታል። ለዘመን ስለተሰጠውም «ባሕረ ሐሳብ» የቁጥር ዘመን ብሎታል።

እያንዳንዱ ሃይማኖት የራሱ የሆነ መለያ ትእምርት አለው። በተለይም በሥዕሎችና በምስሎች ይገለጻል። መስቀል የክርስትና ትእምርት ሲሆን የጥንት ክርስቲያኖች ኢትዮጵያን ጨምሮ መርከብ (ሐመር) የክርስትና ትእምርት አድርገው ይጠቀሙበታል። ምእመናን በባሕረ ሕይወት ያንሳፍፋልና በቤተ ክርስቲያን ይወከላል።

ወንጌላውያንም የየራሳቸው ትእምርት አላቸው። ማቴዎስ በገጸ ብእሲ፣ ማርቆስ በገጸ አንበሳ፣ ሉቃስ በገጸ ላሕም፣ ዮሐንስ በገጸ ንሥር ይመሰላሉ። ለወንጌል ጸሐፍት ወንጌላዊ የሚለው ተቀጽላ የተሰጣቸው ድኅረ ሐዋርያት ዘመን ነው።

እነዚህ ምስሎች የተገኙት ከራዕየ ሕዝቅኤልና ከራዕየ ዮሐንስ ነው። በተለይ በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 6 እስከ 10 ውስጥ የሚከተለው ይገኝበታል። «በዙፋኑም ዙሪያ አራቱ እንስሶች አሉ፤ እነርሱም በፊትም በኋላም ዐይኖችን የተመሉ ናቸው። ፊተኛውም እንስሳ አንበሳ ይመስላል፤ ሁለተኛውም ጥጃን፣ ሦስተኛውም እንስሳ ሰውን ይመስላል። አራተኛው የሚበር ንስርን ይመስላል።» ለእያንዳንዱ ወካይ የሆነው ምልክት አመጣጥ የተገኘው ከጻፉት ጽሑፍ በመነሳት ነው። ማቴዎስ ትረካውን የጀመረው ከክርስቶስ (የሰው ልጅ) ትውልድ በመሆኑ በሰው ሲመሰል፣ ማርቆስም የመጥምቁ ዮሐንስ ተልዕኮ የተጀመረው ከዱር በመሆኑና በረሃ የአንበሳ መናኸሪያ በመሆኑ በአንበሳ፣ ሉቃስ የካህኑ ዘካርያስን ታሪክና የላሕም መስዋዕት በማሳየቱ

በላሕም፣ ዮሐንስ ወንጌሉ ረቂቁን ዓለም አልፎ በምጥቀት በመንዝዝ ነገረ መለኮትን በማጉላቱ በንሥር ተመስለዋል። (ኢቫንጀሊስት፣ ኢንካርታ 2006)

ሸ) ዝማሬና ሽብሸባ

በርእሰ ዐውደ ዓመቱ ንግሥ ጊዜ ካህናት የሚያቀርቡት ዝማሬና ሽብሸባ አካላዊ ውዝዋዜና እንቅስቃሴ ትእምርታዊ ገጽታ አለው።

መልአከ ብርሃናት አድማሱ ጀንበሬ ስለመዘምራን አምሳል በጻፉት የሚከተለው ይገኛል።

> «መዘምራን በዜማ እየቃኙ በመቋሚያ ሲዘሙት፣ በከበሮና በጸናጽል ሲመረግዱት፣ ሲጸፉት አንዳንድ ጊዜም በእግራቸው ሲያሸበሽቡ፣ በእጃቸው ሲያጨበጭቡ ይታያሉ። ይህም ሥራቸው ታላቅ ምሥጢር ያለው ነው። የኢትዮጵያ መዘምራን በዝማሜ ጊዜ ታጥቀው ከፊት ወደኋላ ከኋላ ወደፊት፣ ከቀኝ ወደግራ ከግራ ወደቀኝ እያሉ ሲዘሙ፣ አንዳንድ ጊዜም በግንባራቸው እየሰገዱ ሲነሱ በመታየታቸው አይሁድ ጌታን በሌሊተ ዐርብ ከጌቴሴማኒ ወደ ቤተ ቀያፋ፣ ከቀያፋ ወደ ጲላጦስ ሲወስዱት፣ በፊት ያሉቱ ወደ ኋላው በኋላው ያሉቱ ወደፊቱ፣ በቀኙ ያሉቱ ወደ ግራው፣ በግራው ያሉቱ ወደቀኙ እየገፉ እያዳፉ በግንባሩ እየተከሉ መውሰዳቸውን፣ በእግራቸው ሲያሸበሽቡ በእግረ አይሁድ መረገጡን ሲጸፉና በእጃቸው ሲያጨበጭቡ በጥፊ መመታቱን፣ ሲመረግዱ ኩርዓተ ርእሱን ያሳስባሉ።

የሐር ገመድ ባንገታቸው አጥልቀው በግራቀኝ ትከሻቸው ላይ ሲታይ በገመድ መታሠሩን ያመለክታሉ። መቋሚያቸውን በትከሻቸው ተሸክመው መኻል ለመኻል እየሄዱ ሲያስረግጡ መስቀሉን ተሸክሞ ከሊቶስጥራ እስከቀራንዮ መሄዱን፣ መቋሚያቸውን ከትከሻቸው አንሥተው ወደ ላይ አቅንተው ከፍ አድርገው ይዘው ሲታዩ «ጸማዕኩ» ባለ ጊዜ ሐሞትንና መጣጣውን ከርቤ ቀላቅለው በዘንግ አሥረው በመስቀሉ ላይ ሳለ ወደ አፉ ማቅረባቸውን ያስባሉ፣ ያሳስባሉ።» (1940:57)

ቀ) ሰንደቅ ዓላማ

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ በአገሪቱ ሰንደቅ ዓላማ ቀለሞች አረንጓዴ ብጫ ቀይ መልክ የተቀባበት ከመሆኑ ባሻገር በንግሡም ዕለት ዓላማው ይውለበለባል። ከአገሪቱ ሌላ የቤተክርስቲያኒቱ ትእምርት ሆኖም ይታያል። በዊልያም ስሚዝ እንደተገለጸው ሰንደቅ ዓላማ አገርን ወይም ተቋምን

እምነትን ወይም ሐሳብን ሊወክል ይችላል:: መረጃም ያስተላልፋል:: ሃይማኖቶችና አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸው የሆነ ሰንደቅ ዓላማ ይኖራቸዋል:: (1974:850)

በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ማርያም በእወጃና በአሥርቆቱ የነበረው ሥርዓት የኢትዮጵያ ስመሆኑ፣ ዘመኑ የሚለወጠው፣ ዓመቱ የሚቀመረው በማሕሌት የሚታጀበው ለየት ያለ አቆጣጠር ባላት ኢትዮጵያ ስመሆኑ ሰንደቅ ዓላማው በትምእርትነት ይገልጻል:: በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሰንደቅ ዓላማ ላይ «ነዋ ወንጌለ መንግሥት» (የመንግሥት ወንጌል እነሆ) የሚል ሐረግ ተጽፎበታል::

በርእሰ ዐውደ ዓመቱ አከባበርና በባሕረ ሐሳቡ እወጃ ጊዜ ህልዉ የነበሩት ትእምርቶች በቁስ፣ በንግግር ቃላት፣ በድምፅና በአካላዊ ውዝዋዜ መከሰታቸው በየክፍሉ ከቀረበው ትንተና መረዳት ይቻላል:: አንዳንዶቹ ትእምርቶች በሌሎችም በዓላት የሚታዩ ቢሆንም በዘመን መለወጫው ዕለት የቀረቡበት መንገድ ግን ከዘመን ቀመሩ ዐውዳዊ ፍች ጋር ተያያዘው ነው::

# ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ባሕረ ሐሳብ ትውፊት ድርሳን ውስጥ አንድ ዐቢይ ሐሳብ ይገኛል።

«ታውቅ ዘንድ የዘመንን ምሥጢር የምትቆጥር አንተ ብልህ ሰው ይኸንን እወቅ፣ ልብ አድርግ» ይላል። በዚህ በዘመን መለወጫ ዕለት በኢትዮጵያ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስለሚካሄደው የባሕረ ሐሳብ እወጃ በመስክ ጥናት ተደርጓል። ፎክሎራዊ ገጽታውም ተፈትሿል።

ክዋኔው በቪዲዮና በፎቶግራፍ ካሜራዎች፣ በመቅረጸ ድምፅም ተሰብስቧል። ጥናቱ ከዐውደ ምሕረት (መስክ) መልስ የተገኙ ካልዓይ መረጃዎችን አካትቷል።

ጥናቱ በዋናነት በአዲስ አበባ ማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተከበረውን የዕለተ ዮሐንስ ርእሰ ዐውደ ዓመት ከተለያዩ አንጻሮች ለመመልከት ጥሯል። ጥናቱ የተካሄደበት ፍኖት በቀዳሚው ምዕራፍ ላይ ተዘርዝሯል።

በሁለተኛው ምዕራፍ የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ለየት ያለ የጉባኤ ትምህርት እንዳለውና ባሕረ ሐሳብ እንደሚባል፣ የአቈጣጠሩ መነሻና ልዩ ልዩ ቀመሮች እንደመደርደሪያ ማስገንዘቢያ ቀርቦበታል።

የዘመን መለወጫው ዕለት በልዩ ልዩ መጠሪያዎች ቅዱስ ዮሐንስ፣ ርእሰ ዐውደ ዓመት ተብሎ እንደሚታወቅና በበዓሉ ዕለት የአከባበሩ ሁኔታ፣ የባሕረ ሐሳብ እወጃውና ጓዞች የተካተተበትን ምዕራፍ ሦስት ይዟል።

በዘመን መለወጫው ዕለት የሚታዩ የበዓል ትእምርቶች ምንነትና ውክልነታቸው የዘመንን ምስጢር በሚያጎላ መልኩ በምዕራፍ አራት ተመልክቷል። ከሥነ ቃል ተግባራት አኳያ የባሕረ ሐሳብ እወጃ የመግለጥ፣ የማጠናከርና የመትከል፣ የማምለጭ፣ የማስተማርና የመግታት - የመቆጣጠር ተግባራት ጋር ሰምና ፈትል ሆኖ ለመገኘቱ የቀረቡት ማስረጃዎች አሳይተዋል።

## ይሁንታ

ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም ልዩ ካደረጋት ነጥቦች መካከል አንዱ የዘመን አቆጣጠር ሥርዓቷ ነው። ከወራት አደረጃጀት የነሣ «13 የፀሐይ ወራት» ያላት አገር እየባለች ትጠራለች።

ባሕረ ሐሳብ እየተባለ የሚጠራው የዘመን ቀመሯ ጊዜን በቅደም ተከተል ሰከንድ (ካልዒት) እና ደቂቃ፣ ቀንና ሳምንት፣ ወርና ወቅት (መፀውና በጋ፣ ጸደይና ክረምት)፣

ዓመትና ኢዮቤልዩ፣ ምእት ዓመትና ሺሕ ዓመት (ሚሌኒየም) ብላ መድባዋለች:: የጊዜ ክፍልፋዮችን አነሣሥና ዕድገት ከውጪ ከመጡ ሐሳቦች ጋር አዛምዳ ጥንታዊ መሠረቱን ሳይለቅ እስካሁን አቆይታዋለች::

ይሁን እንጂ አገሪቱ ለዚህ የዘመን አቈጣጠር ዘርፍ የሰጠችው ትኩረት አናሳ መሆኑ ይታያል:: በሃይማኖታዊው ሆነ በዓለማዊ መዕር የመን መለወጫን በየዓመቱ ከማክበር ውጪ ስለ ዘመን አቈጣጠሩ ትውፊቱ በዕውቀት ላይ ተመሥርቶ ማወቅ ብለም ማሳወቅ አስፈላጊነት አለው::

የባሕረ ሐሳብ ጽንሰ ሐሳብና መጠርያው በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዲታወቅ ማድረግ፣ በጥንታዊነቷ የምትታወቀዋ ሀገር በዘመን ቀመር አጀማመር ውስጥ ያላትን ድርሻና ከሌሎች ጋር የነበራትን ግንኙነት መረዳት፣ አንድን ዘመን በልዩ ልዩ የአቈጣጠር መነሻዎች በፀሐይና በጨረቃ መንገድ ያደራጀችውን ሥርዓት መገንዘብና ስለ አቈጣጠሩ ያሉ ልዩነቶችን መመርመር አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም:: ይህን ለመሥራት የተናጠል ጥረት ሳይሆን በቅርብ የሚመለከታቸው ተቋማትባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ቤተ ክህነት ወዘተ. ሊያተኩርበት ይገባል::

ልዩ በሆነው አቈጣጠሯ በዘመን መለወጫ ዕለት በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የሚኖረው አከባበር የቱሪስቶችን ቀልብ ሊስብ የሚችል መሆኑ በዶክመንተሪ ፊልም ቢሠራለት፣ በየቋንቋው መጻሕፍት ቢዘጋጁለት መገናኛ ብዙኀን ትኩረት ቢሰጡት ተጠቃሚ የሚሆኑት አገሪቱና ሕዝቦቿ ናቸው:: የዘመን አቈጣጠር በኢትዮጵያ ጥንታዊውን መሠረት ሳይለቅ፣ ሌሎች የተውትን በምልዐት ተጠብቆ መቆየቱን መረዳትና ማስፋፋት ከሁሉም የሚጠበቅ ድርሻ ነው::

ዘመንና ሐሳበ ዘመን ዐቢይ ሥነ ማኅበራዊና ሥነ መለኮታዊ ርእስ ጉዳዮች መሆናቸውና የዘመን አቈጣጠር ምርጫም ማኅበራዊ ሕይወትን ከመተርጐም አኳያ የሚታይ በመሆኑ ከፍተኛ የመንፈሳዊ ትምህርት ተቋማት በሥርዓተ ትምህርታቸው ሊያካትቱ ይገባል::

ቅዱስ አውጎስጢኖስ እንደተናገረው፣ «ቃለ እግዚአብሔርን ለመስበክ ሰዋሰው እንደሚያስፈልግና ያለ እርሱም አገባብን ሳያውቁ ማስተማር እንደማይቻል፤ በአምልኮት ጊዜ እግዚአብሔርን ለማመስገን ዜማ እንደሚያስፈልግ ሁሉ፤ ቤተ ክርስቲያንን ለማስተዳደር፣ ምሥጢራትን ለማቀበል ሥርዓተ ሕግና ቀኖና እንደሚያሻው ሁሉ፤ ባሕረ ሐሳብም (ሐሳብ) የዘመን አቈጣጠርና የቤተ ክርስቲያንን በዓላትና አጽዋማት ለማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው» (Coyne,1983:60)::

# ስምዓት (ቢብሊዮግራፊ)


ስምስም በቀለ፤ «እንቊጣጣሽ በአዲስ አበባ የልጃገረዶች ዘፈን ይዘት ቅርስና ሥነ ቃላዊ ትንታኔ»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ዲማጽ ፣ 1986::

ላዕከ ማርያም ወ/ኢየሱስ፤ *መጽሐፈ ስንክሳር*፤ አዲስ አበባ፣ 1993::

ሔኖክ ያሬድ፤ «ባሕረ ሐሳባችን» በሪፖርተር ጋዜጣ፣ ቅጽ 13፣ 2000፣ ሰኔ 1::

__________፤ «ለሚሌኒየሙ የተዘጋጀው ዓርማ እንዲቀየር ተጠየቀ» በሪፖርተር ጋዜጣ፣ ቅጽ 12፣ 1999፣ ታኅሣሥ 8::

__________፤ «የወራት ስያሜ» በአዲስ ዘመን ጋዜጣ 43ኛ ዓመት፣ 1976፣ የካቲት 11::

መሠረት ስብሐት ለአብ፤ *ትውፊታዊ ኅሳበ ዘመንና ታሪክ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አቋም*፤ ሆንግ ኮንግ፣ ኒው ላይፍ ሊትሬቸር፣ 1981::

*መጽሐፍ ቅዱስ*፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት፣ 1953 ዓ.ም::

*መጽሐፈ ድጓ*፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት ፣38 ዓመተ ቀኃሥ::

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፤ *ካሴት ቁጥር2*፣ 1999::

አክሊሉ ገብረ ኪሮስ፤ «ዐውደ ዓመት»፣ *በአዲስ ዘመን ጋዜጣ*፣ 46ኛ ዓመት ቁጥር 1፣ 1978፣ መስከረም 1::

አድማሱ ጀምበሬ፤ *የበገና መዝሙር*፤ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማ/ቤት፣ 1940::

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማ/ቤት፣ 1948::

ክፈለው ዘለቀ፤ «የአውራኅ ስም በኢትዮጵያ»፤ *በየካቲት* መጽሔት ቅጽ 16፣ ቁ.4፣ 1985::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤ *ኣማርኛ መዝገበ ቃላት*፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማ/ቤት፣ 1993::

የወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር፤ *የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የባህል ፖሊሲ*፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1995::

ያሬድ ፈንታ፤ «ባሕረ ሐሳብ» *Ethiopian Review Of Cultures* (Vol IV-V), **1994-1995::**

------------- ፤«*መርሐ ዕውርና ግጽው ዘሰንበተ ክርስቲያን*»፤ **1993 (ያልታተመ)::**

------------- ፤*መጽሐፈ ግጻዌ ሐዲስ ዘተሰናአወ በአርባዕቱ ክፍላተ አዝማን*፤ አዲስ አበባ፣ **1997::**

ደስታ ተክለ ወልድ፤ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማ/ቤት፣ **1962::**

ዳንኤል ሠይፈ ሚካኤል፣ «ሐሳበ ዘመን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን» *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንት ዛሬና ነገ*፣ አዲስ አበባ፣ ብራና ማ/ቤት፣ **1994::**

ጌታቸው ኃይሌ፤ *ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቈጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ*፤ ኮሌጅቪል፣ **1993::**

ጎርጎርዮስ (አባ)፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፤ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማ/ ቤት፣ **1974::**

ጥበብ ይኄይስ፤ *ካሴት ቁጥር 2*፣ **1999::**

ፈቃደ አዘዘ፤ *የሥነ ቃል መምሪያ*፤ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ **1991::**

Coyne,G.V(ed.). *Gregorian Reform of the Calendar*. Vaticano: 1983.

Cuddon, J.A.*The Penguin Dictionary of Literary Terms and Literary Theory*. England: Penguin Books, 1998.

Dorson, Richard M. ed. *Folklore and Folklife: An Introduction.* Chicago: University of Chicago Press, 1972.

Dundes, Alan. *The Study Of Folklore*. Engle Wood Cliffs,N.J: 1965.

"Evangelist". *Microsoft Encarta,* 2006 [CD]

"Folklore". *The Book World Encyclopedia*. U.S.A: 1994.

"Feasts and Festivals". *The World Book Encyclopedia*.U.S.A. World Book International. Vol.7,1994.

Fritsch, Emmanuel. *The Liturgical Year Of The Ethiopian Church*. Addis Ababa: Master Printing Press,2001.

Gregory, Ruth. "Feasts and Festivals". *Microsoft Encarta*, 2006

"Holidays". *The Encyclopedia Americana.* 1995.

Robert Jerom Smith: "Social Folk Custom Festivals and Celebrations" In M. Richard Dorsen(ed). *Folklore and Folklife Introduction.* London: 1972.

Neugebauer, Otto. *Ethiopic Astronomy and Computes*, Weien: 1979.

Pankhurst, Sylvia. *Ethiopia: A Cultural History.* London, 1955.

"Pope Demetrius The Vinedresser" *In EL-KERAZA Magazine.* Cairo: Vol 3, No. 6, 1994.


"Religious Symbol" *The World Book Encyclopodia* (William Smith), USA: 1974.

"Symbol" *The World Book Encyclopedia.* (Whitney Smith), USA: 1994.

Walelgn Emiru."*The Dynamics Of Religious Ritual and Secular Cermonies in Public Places of Addis Abeba (Spatial, Temposal and Symbolic Aspects)*". Department of Anthropology, M.A. Thesis, School of Graduate Studies, AAU: 2003.



▪ የዘመን ቡራኬ



▪ የባሕረ ሐሳብ እወጃ በቅኔ ማሕሌት

▪ በዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን 1991 ዓ.ም.

# አባሪ-1

## የ1999 ዓ.ም. የባሕረ ሐሳብ እወጃ
## በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ማርያም በመምህር ዘካርያስ አምባቸው የተነገረ

እንደምን አደራችሁ? እንደምን ሰነበታችሁ? እንደምን ከረማችሁ? በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፣ አሜን::

ባሕረ ሐሳብ የተዘዋወረ ቀለም ነው:: ሐሳብ ባሕር ሲል ነው፣ ሐሳብ ሲል ቁጥር ማለቱ ነው:: ይህንን ባሕረሐሳብ ሁሉም ሊማር ይገባዋል:: ወደ ባዕድ ሀገርት ሰዶ፣ ተመልሶ መሔድ ይመጣል:: በዚያን ጊዜ አጽዋማትን አውቆ ለመጾም በዓላትን ለይቶ ለማክበር ነው:: ይህንን ያልተማረ ካህን በደረቅ ወንዝ ይመስላል:: ለጥቆም በሩቅ ነጋድያን ሲያዩት ቀጠሉ ለምልሞ፣ አሸዋው ተቆልሎ ይታያቸዋል:: ከጥላው አርፈን ጥሬ ቆርጥመን ውሃ እንጠጣለን ይላሉ:: ግን አጥተው ይመለሳሉ:: ይህን ያልተማረ ካህን ምእመናን ከሩቅ ሲያዩት አብቦ ጠምጥሞ ካባውን ደረቦ ይታያቸዋል:: አባታችን አጽዋማትን አውጥቶ በዓላትን ለይቶ ይነግረናል ብለው ሲሄዱ አፍረው ይመለሳሉ::

«ካህን ዘኢየአምር ዘንተ–ሐሳበ ይመስል ከመ ፈለግ ዘአልቦ ማይ ወከመ ሀገር ዘአልቦ ቅጽር» እንዲል::

ይህን ድሜጥሮስ ተናግሮታል:: ድሜጥሮስ ማለት መነፅር ነው:: መነፅር የራቀውን አቅርቦ የቀረበውን አጉልቶ ያሳያል:: እርሱ አጽዋማትን አቅርቦ በዓላቱንም አጉልቶ ያሳያልና::

ይህ እንደምን ነው ቢሉ አርማስቆስና እንድራያንቆስ የሚባሉ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ:: አንድርያቆስ ድሜጥሮስን ወለደ:: አርማስቆስ ልዕልተ ወይንን ወለደ:: የልዕልተ ወይን አባት ሞተ:: እንድርያቆስ ከልጁ ድሜጥሮስ ጋር አሳደጋት::

ሁሉም ለአቅመ አዳም ለአቅመ ሔዋን በደረሱ ጊዜ የወንድሙን ልጅ ለልጁ አጋባ::

ለምን ቢሉ በዘመናቸው አሕዛብ በዝተው ምእመናን ያነሱበት ነውና ሕንፃ ሃይማኖት ከሚፈርስ ሕንፃ ሥጋ ይፍረስ ብለው ነው:: «ወንድሜ እህትህ አልነበርኩም እንዴ»

«ያባታችን ፈቃድ እፈጽም ብዬ ነው»

«በድንግልና አንኖርም ከፈቃድህ አልወጣም»

በድንግልና አብረው ኖሩ። በአንድ አልጋ አንድ ምንጣፍ አንጥፈው አንድ ልብስ ተጎናፅፈው 48 ዘመን ሲኖሩ በግብረ ሥጋ አይተዋወቁም ነበር።

ይልቁንም መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ቀኝ ክንፉን ለርሱ፣ ግራ ክንፉን ለርስዋ አድርጎ አድሮ ማለዳ በመስኮት ሲወጣ ያዩት ነበር። በአምሳለ ርግብ ሲሄድ ይታያቸው ነበር።

ድሜጥሮስ ወይን አጸድቆ ድኮ ታጥቆ ሞፈር አርቆ ይኖር ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ያለጊዜው ያፈራ የወይን ዘለላ አግኝቶ መጣ። ወንድሜ እንደምን በጊዜ መጣህ አለችው። እኔም አንተም ልንበላ አይገባንም። ጸሎት ተቀብለን እንምጣ አለችው።

ሊቀጳጳስ ዩልዮስ ነበር። እኔ ደከምኩ ሌላ ሰው ምረጡ። አባታችን አንተ መርጠህ ስጠን አንጂ እኛ ምን እናውቃለን አሉ፤ እንግዲያውስ እናንተ ሰባኤ ግቡ እኔም እገባለሁ አለ ሰባዔ በገባበት መልአኩ ተገልጾ ያለ ጊዜው ያፈራ ወይን ይዞ የሚመጣ አለ። የንን ሾሙላቸው አለው።

ድሜጥሮስ ወይን ያገኘበት መልአኩ ለዩልዩስ የነገረበት ሰዓቱ አንድ ሆኗል። ወዲያው ለሕዝቡ ወጥቶ ያለጊዜው ያፈራ ወይን ይዞ የሚመጣ ሰው አለ፤ ሾሚላችኋለው አለው። ይህን ተናግሮ አልሰነበተም ወዲያው ሞተ።

ድሜጥሮስ ወይኑን ይዞ ሲመጣ ሊቀጳጳሱ ሙቶ የቀረበው ደረሰ። ይህ ለሊቀጳጳሱ የሚገባ ወይን ተቀበሉልኝ አላቸው። አባታችን ያለን ደረሰ ብለው ከእልፍኝ አስገብተው አኖሩት። ከንጉሡ አልመከሩምና መከሩና ተሾምልን አሉት። እኔ ባለሕግ ነኝ፤ አባታችን ተሾምልን ብሏልና ተሾም አሉት። ሥርዓቱን ንገሩኝ አላቸው። «አንቀጸ አባግዕ» «አንቀጸ ብጹዓን» ወንጌል አንብቦ ተርጉም ነው አሉት። ያርዩስ ያኮስ አሉት፤ ይደልዎ ማለት ነው።

ድሜጥሮስ ተሹሞ ሲኖር የሕዝቡ ኃጢያት ተገልጾ ይታየው ነበር። አንተ በቅተሃል ብላ ደሙን ተቀበል አንተ አልበቃህም ቆይ ይላቸዋል። ሕዝቡ በሀሜት ተሞሉ። ሕጉን ሰርቶ በማርቆስ መንበር መቀመጥ አነሰውና እኛን በቅተሃል አልበቃህም ይለናል እያሉ በሐሜት ስለተሞሉ መልአኩ ተገልጾ ለዲሜጥሮስ በሚስትህና በአንተ መካከል ያለውን ግለጽላቸው ብሎ አላቸው።

በስምንተኛው ቀን አግብዖተ ግብር ነበርና ሕዝቡ እንጨት ይዘው እንዲመጡ አዘዛቸውና ይዘው መጡ ቆልሎ እንደ ደመራ ደምሮ እሳት አያይዞ ቅዳሴ ገባ፣ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ሲወጣ እኩሉ ነድዶ አገኘው፤ ከእሳቱ መካከል ወዲያ ወዲህ እያለ ይመላለስ ነበር። ሚስቱም አስካለ ወይን በምቅዋመ አንስት ነበረችና አስካለ ወይን፣ አስካለ ወይን ብሎ ጠርቶ ፍሕሙን በመንናፀፊያው አጎናፀፋት እርሷም ሴት ወንዱን፣ ልጅ ዐዋቂውን ዙሩ ብታራግፈው ከማገ አንድ ሳይጠቁር ሳይቀነብር ተገልጧል።

ሕዝቡ አባታችን ምስጢሩን ግለጽልን አሉት።

ይህ እሳት ዘሀው እኔንም እሷንም እንዳልነካን እኔና እሷ 48 ዓመት በአንድ አልጋ በአንድ ምንጣፍ ስንኖር በግብረ ሥጋ አንተዋወቅም ነበር። እናንተ እኔን እማችሁ በሐሜት ስለተጎዳችሁ መልእኩ ግለጻላቸው ብሎኝ ነው።

አባ አባ ስረይ ለነ ኀድግለነ ኃጢአትነ ብለው ከጫማው ወደቁ።ይፍታሕ ወይኅድግ ሊቀካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ ኃጢአታቸውን አስተሰረየላቸው። ኑዛዜ ያን ጊዜ ተጀመረ ይላሉ።

ከዚህ አስቀድሞ የነበሩ ሊቃውንት አጽዋማት በዓላት እየተፋለሱባቸው ሲያዝኑ ሲተክዙ ይኖሩ ነበር። ዘመኑን ሦስቱን ወር ለአንድ ወንጌላዊ ሦስት ወር ከ 4 ጳጉሜን ለአንድ ወንጌላዊ አካፍሏቸዋል።

አምስተኛዋን ከነግህ እስከ ቀትር ለአንድ፣ ከቀትር እስከ ሠርክ ለአንድ፣ ከሠርክ እስከ መንፈቀ ሌሊት ለአንድ፣ ከመንፈቀ ሌሊት እስከ ነግህ ለአንድ፣ አካፍሏቸው ነበር። ስድስተኛይቱን አራቱ ከዋክብት እንዲሁ በኪክሮስ ተካፍለዋቸው ነበር።

ጾምንም ጾመ ነነዌ፣ ጾመ ኢየሱስን የጥምቀት ሳኒታ አስገብተው የካቲት 22 ቀን ይጨርሳሉ። በመጋቢት 22 ሆሣዕና በ27 ስቅለት፣ በ29 ትንሣኤን ያደርጋሉ።

ትንሣኤ እንደዛሬ እሑድ ብቻ አይውልም ነበር ሰኞ ማክሰኞ ሮብ ኀሙስ ዓርብ ቀዳሜ እንደተገኘው ያውሉት ነበር።

ይልቁንም እርሱ (ድሜጥሮስ) ያዝን ይተክዝ ነበርና በመስከረም ጊዮርጊስ ሰባኤ ገብቶ የጥቅምት ሚካኤል ተገልጾለት መጣ፤ ከመስከረም ጊዮርጊስ እስከ ጥቅምት ሚካኤል ቢቆጥሩ 20 ይሆናል።

ከ20 የተገኘው አንዱ ይኸ ነው፤ ድሜጥሮስ ከቀኑ 7፤7 ሰዓት ከሌሊቱ 23 ይጸልይ ነበር።

ስለምን የቀኑን አሳንሶ የሌሊቱን አበዛ ቢሉ ቀን የተጣላ ሲያስታርቅ የተበደለ ሲያስክስ የሞተ ሲያስቀብር ሲውል ነበር:: ስለዚህ የቀኑን አሳንሶ የሌሊቱን አበዛው:: ሌሊቱን 24 እንጂ 23 ነው ቢሉ አንዲቷ ጥቂት ጥቂት ያርፍባት ይቀድስባት ነበር:: ቀን የሚጸልየው ሰባት ጊዜ ሰባት ሲደምሩት 49 ይሆናል:: በ30 ቢገድፉት 19 ይሆናል:: ጥንተ መጥቅዕ ይኸ ነው:: የሌሊቱ 23 ጊዜ 7 ሲገጥሙት 161 ይሆናል:: በ30 በ30 ሲገድፉት 11 ይተርፋል:: ጥንተ አበቅቴ ነው:: አበቅቴና መጥቅዕ ሲደምሩት 30 ይሆናል:: አበቅቴ ቢያንስ መጥቅዕ ቢበዛ ከ30 አይወጡም ከ30 አይወርዱም ሁሉ 30 ናቸው::

አበቅቴ ወ መጥቅስ ክልኤሆሙ ኅቡረ አይበዝሁ እም 30 ወኢይወኅድ እም 30 ወትረ ይከውኑ 30:: እንዲል መርሐ ዕውር፤ አበቅቴ ማለት ኅልቁ ዘመን ማለት ነው:: መጥቅዕ ማለት ነጋሪት ማለት ነው:: ስለምን በቁሙ መጥቅዕ አለው ቢሉ "ወብሂለ መጥቅዕሂ አስተጋብአ ብሂል እስመ ከመ መጥቅዕ ዘዕዕ ወዘዕብን ዘብርት ወዘሐፂን ያስተጋብእ ዝርዋነ ከማሁ ወእቱሂ ያስተጋብእ አጽዋማተ ወበዓላተ ዘኵሎን ዓመታት" እንዲል:: መርሐ ዕውር መጥቅዕ አስባሳቢ ማለት ነው:: የእንጨትና ድንጋይ የብርትና የብረትም ደወል ሰዎችን እንደሚሰበስብ መጥቅዕም በዓመታት ውስጥ ያሉትን አጽዋማትና በዓላት ይሰበስባል:: ዳግመኛም መጥቅዕ ነጋሪት በተመታ ጊዜ ሰውን ሁሉ ካንድ ቦታ ሰብስቦ እንዲያስገኝ ይኸም አጽዋማትንና በዓላትን ባንድ ዕለት ስብስቦ ያስገኛልና:: ጾመ ነነዌ፣ ጾመ ኢየሱስ፣ ጾመ ሐዋርያት፣ ከሰኞ፣ ረክበ ካህናት፣ ምሕላ ጾም ከረቡዕ፣ ዕርገት ከኀሙስ፣ ስቅለት ከዓርብ፣ ደብረዘይት ሆሣዕና ትንሣኤ ጰራቅሊጦስ ከእሑድ እንዳይወጡ ወስኖ ደንግጎ በአራቱ መዕዘን ዓለም ላሉ ሊቃነ ጳጳሳት ለከላቸው:: ለወንድማችን መልካም ጾም ተገልጾለታል:: አሜን ወአሜን ብለው አስተምረውታል:: እስከዚህ ድረስ መቅድም ነው::

ከዚህ በላይ ለዚህ ዓለም 7 መስፈሪያ መቁጠሪያ አሉት:: እሊሁ 7ቱ አዕዋዳት ይላቸዋል:: ማን ማን ናቸው ቢሉ ዐውደ ዕለት፣ ዐውደ ወርኅ ዐውደ ዓመት፣ ዐውደ ፀሐይ (ዐውደ ፀሐይ ዐውደ ዓመት ካለው ይገባል) አንድ ወገን ዐውደ ጨረቃ፣ ዐውደ ቀመር፣ ዐውደ ማኅተም፣ ዐውደ አበቅቴ::

ዐውደ ዕለት ማን ማናቸው ቢሉ ከእሑድ እስከ ቅዳሜ 7ቱ ዕለታት ናቸው:: በእነዚህ ተመልሶ አንድ ይላል እንጂ፤ 9 አይልም ተመላልሰው ይኖራሉ:: ዐውደ ወርኅ ማለት 30ው መዓልት ናቸው:: 30 ሲደርስ 1 ይላል እንጂ 31፤32 አይልም:: እሊህ ሲመላለሱ ይኖራሉ::

ዐውደ ዓመት ማለት ምን ማለት ቢሉ 365 በዘመነ ሉቃስ 366 ከዚያ ሲደርስ 1 ይላል፡፡ እሲህ ሲመላለሱ ይኖራሉ፡፡

ዐውደ ፀሐይ ከዐውደዓመት አንድ ወገን ነው፡፡ በ28 ዓመት ይመላለሳል፡፡

ዐውደ ጨረቃ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ 394 ቀን ነው፡፡ ዐውደ ቀመር ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ 532 ዓመት የሚቀመርበት ዐቢይ ቀመር ይባላል፡፡ ዐውደ ማኅተም ምን ማለት ነው ቢሉ 76፤76 ዓመት የሚፈራረቅበት ማዕከላዊ ቀመር ይባላል፡፡ ዐውደ አበቅቴ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ 19፤19 ዓመት የሚቀመርበት ንኡስ ቀመር ይባላል፡፡ ዐቢይ ቀመር መደቡ 14፤ የሚደርስ 15ትም ይሆናል፡፡ ማዕከላዊ ቀመር መደቡ 6 የሚደርስ 7ትም ይሆናል፡፡ ንኡስ ቀመር መደቡ ሃስት የሚደርስም ይሆናል፡፡

ዐቢይ ቀመር፣ ማዕከላዊ ቀመር፣ ንኡስ ቀመር እንደ ድርብ እንደማድጋ ሁሉም መስፈሪያ መቁጠሪያ ናቸው፡፡ በአንደኛው ዐቢይ ቀመር አራት ሰንበታትኒ ጊዜ ዐውደ ማኅተም ይገኙበታል፡፡

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ 7499 ዓመት ሆነ ይኋል ይህንን ይደረጃል፡፡ ሰባቱን መቶ አራት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ለዐቢይ ቀመር ለ14 ወንበር 532 ሰጥቶ ምን ይተርፋል? 51 ይተርፋል ጠቅለል ለማድረግ ነው፡፡ ከ51ዱ ለሁለት ንኡስ ቀመር ከ20ው አንድ ከ40ው ሁለት አንስቶ 13 አስቀርቶ ሲሰጡት 13 ይተርፋል፡፡

ስለጀመርነ ቆጠርነ ስላልተፈጸምነ አተትነ «አሐደ አትት ለዘመን» ብሎ አንድ ቀንሶ 12 ወንበር ሆነ ይላል በዘመነ ሉቃስ፡፡ ከዚህ 12 ወንበር 11፡11 አበቅቴ ይነግል 12 ጊዜ 11 120 ብሎ አንዳንድ 12 ጊዜ 11 ሲጨመር 132 ይሆናል፡፡

ከ100 ው 10ሩን አስቀርቶ 90ውን በ30፡በ30 ገድፎ ከ30ው ሲገድፋት 12 ይተርፋል 12 አበቅቴ ከዚህ ይገኛል፡፡ መስከረም መዓልቱ 30፣ ሌሊቱ 30 በ4፡በ4 ሰባኤ ቢገድፋት 4 ይተርፋል፡፡ ጥቅምት መዓልቱ 30 ሌሊቱ 30 በ4፡በ4 ሰባኤ ቢገድፋት 4 ይተርፋል (ሁለቱን ሲደምሩት) 4+4 ይሆናል 8፡፡ ከ8 አንድ ይገኛል፡፡ አንድ ሕፀፅ ከእዚህ ተገኘ፡፡

ከኅዳር እስከ ታኅሣሥ፣ ከጥር እስከ የካቲት እንዲህ እያልክ አውጣ፡፡

1 ሕፀፅ፡ 1 መዓልት፡ 12 አበቅቴ ሲደምሩት 14 ይሆናል፡፡ በዛሬው ዕለት ያደረው መስከረም 1 ቀን በዘመነ ሉቃስ 14 ሌሊት ነው፡፡ ከዚሁ ከ12ቱ ወንበር መጥቅዕ

ስማግኘት 19፡19 ይነሱዋል ይህንን አጋጥመው ሲገድፉት 18 ይተርፋል 18 መጥቅዕ 12 አበቅቴ ሲያገኙት 30 ይሆናል፡፡

መጥቅዕ ቢበዛ አበቅቴ ቢያንስ፣ አበቅቴ ቢበዛ መጥቅዕ ቢያንስ ከ30 አይወጡም ከ30 አይወርድም፡፡

«አበቅቴ ወመጥቅዕ ክልኤሆሙ ኅቡረ ኢይበዝኑ እም30 ወኢይውኅዱ እም30፣ ወትረ ይከውኑ 30» እንዳለ መርሐ ዕውር፡፡ መጥቅዕ 14ን አይነካም፡ ከ14 በላይ ሲሆን ከ15ጀምሮ እስከ 30 ይወሰዳል፡፡

መጥቅዕ በመስከረም ይወድቃል፡፡ ነነዌ በጥር ትሆናለች፡፡ ከ14 በላይ ሲሆን መጥቅዕ በጥቅምት ይወድቃል፡፡ ጾመ ነነዌ በየካቲት ትሆናለች፡፡ ዘንድሮ ከ14 በላይ ነው፡፡ መጥቅዕ (መስከረም) ላይ ይወድቃል ማለት ነው፡፡

መስከረም ሰኞ ባተ፤ ሰኞ እስከ ሰኞ 8፤ ሰኞ እስከ ሰኞ 15፤ ማክሰኞ 16፤ ሮብ 17፤ ኀሙስ 18 ኀሙስ ላይ ወደቀ፡፡ የኀሙስ ተውሳክ 3 ሲደምሩት 21፤ መባጃ ሐመር 21፤ ተገኘ፡፡ ጾመ ነነዌ ተውሳክ የላትም፡፡ በመባጃ ሐመር በደረቅ ይውላል፤ ጥር መቼ ይብታል፤ ሳኒታውን አይለቅም፡፡ ማክሰኞ ይብታል፡፡ ማክሰኞ እስከ ማክሰኞ 15፤ ማክሰኞ እስከ ማክሰኞ 22፣ አንዷን ታግሶ ከኋላ በ21 ጾመ ነነዌ ጥር 21 ቀን የአስተርዕዮ ሆነ፡፡

የጾመ ኢየሱስ (ዐቢይ ጾም) ተውሳክ 14 ነው፡፡ 14 እና 21 ሲያገናኙት 35፡፡ 30ውን ገድፎ 5 ይተርፋል፡፡ የካቲት መቼ ይብታል ኀሙስ፡፡ ኀሙስ 1፤ ዓርብ 2፤ ቅዳሜ 3፤ እሁድ 4፤ ሰኞ 5፤ የካቲት 5 ቀን ዐቢይ ጾም ይገባል፡፡ የደብረ ዘይት ተውሳክ 11 ነው፡፡ 11 ና 21 ሲያገናኙት 32 30ውን ገድፎ 2 ይተርፋል፡፡ መጋቢት ቅዳሜ ይብታል፡፡ ቅዳሜ 1 እሁድ 2፤ መጋቢት 2 ደብረዘይት ሆነ፡፡ የሆሳዕና ተውሳክ 2 ነው፡፡ 2 እና 21 ሲያጋጥሙት 23 ይሆናል፡፡ መጋቢት የሚብተው ቅዳሜ ነው፡፡ ቅዳሜ እስከ ቅዳሜ 8፤ ቅዳሜ እስከ ቅዳሜ 15፤ ቅዳሜ እስከ ቅዳሜ 22፤ እሁድ 23፤ የመጋቢት ጊዮርጊስ ሆሣዕና ሆነ ማለት ነው፡፡

የስቅለት ተውሳክ 7 ነው፡፡ 7 እና 21 ሲያገናኙት 28 ይሆናል፡፡ መጋቢት የባተው ቅዳሜ ነው፡፡ መጋቢት 8፤ 15፤ 22፤ 29 ቅዳሜ ይውላል፡፡ አንዷን ታግሦ መጋቢት 28 ዓርብ ስቅለት ይውላል፡፡

የትንሣኤ ተውሳክ 9 ነው፡፡ 9 እና 21 ሲገጥሙት 30 ነው መጋቢት ቀዳሚ ይብታል፡፡ 8፤15፤21፤29 ቀዳሚ ይውላሉ፡፡ እሑድ 30፤ መጋቢት 30 ቀን ትንሣኤ ነው፤ ሚያዚያ በሙሉ ተበሏታል ማለት ነው፡፡

ረክበ ካህናት ተውሳክ 3 ናት፡፡ 3 እና 21 ሲገጥሙት 24 ይሆናል፡፡ ሚያዚያ ሰኞ ይታበታል፡፡ ሰኞ እስከ ሰኞ 8፤ 15፤ 22፤ 23 ማክሰኞ፤ 24 ረቡዕ ሚያዚያ ተክለ ሃይማኖት ረክበ ካህናት ይውላል፡፡ የዕርገት ተውሳክ 18 ነው፡፡ 18 እና 21 ሲገጥሙት 49 ይሆናል፡፡ 30ውን ገድፎ 9 ይቀራል ግንቦት 9 ኀሙስ ዕርገት ይውላል፡፡

የጰራቅሊጦስ ተውሳክ 28 ነው፡፡ 28 እና 21 ሲገጥሙት 49 ይሆናል፡፡ 30ውን ገድፎ 19 ይተርፋል፡፡ ግንቦት የባተው ረቡዕ ነው፡፡ ረቡዕ እስከ ረቡዕ 8፤ 15፤ ኀሙስ 16 ዓርብ 17፤ ቅዳሚ 18 እሁድ 19፤ ግንቦት 19 ጰራቅሊጦስ ይውላል፡፡ የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ 29 ነው፡፡ 21 ሲደምሩበት 50 ይሆናል፡፡ 30ውን ገድፎ 20 ይተርፋል፡፡ ግንቦት 20 ቀን ሰኞ ጾመ ሐዋርያት ይገባል፡፡

የምሕላ ጾም ተውሳክ 1 ነው፡፡ 21 ሲደምሩበት 22 ይሆናል፡፡ በግንቦት 22 ረቡዕ ምሕላ ጾም ትገባለች፡፡

የዕለታት ተውሳክ መጨረሻ 2፤ የመጥቅዕ መወሰኛ 15 ሁለቱ ሲጋጠሙ 17 ይህ የጾመ ነነዌ አይወርድ ነው፡፡ የዕለታት ተውሳክ መጀመሪያ 8፤ የመጥቅዕ መጨረሻ 13 ሁለቱ ሲጋጠሙ 21 ይህ የጾመ ነነዌ አይአርግ ነው፡፡ ጾመ ነነዌ ወደታች ስትወርድ ጥር 17 እንጂ 16ን አትነካም ወደ ላይ ስትወጣ፤ የካቲት 21 እንጂ 22ን አትነካም፡፡ የጾመ ኢየሱስ ተውሳክ 14፤14 እና 17 ሲደመር 31 30ውን ገድፎ 1 ይተርፋል፡፡ ወደታች ሲወርድ የካቲት፩ እንጂ ጥርን አይነካም፡፡

21 እና 14 ሲገጥሙት 45 ይሆናል፡፡ 40ውን ገድፎ 5 ይተርፋል፡፡ ወደ ላይ ሲወጣ መጋቢት 5 እንጂ መጋቢት 6ን አይነካም፡፡

የደብረ ዘይት ተውሳክ 11፤ 11 እና 17 ሲደመር 28 ይሆናል፡፡ ወደ ታች ሲወርድ የካቲት 28 እንጂ 27 አይነካም፡፡ 11 እና 21 ሲገጥሙት 32 ይሆናል፡፡ 30ውን ሲገድፉት 2 ይተርፋል፡፡ ወደ ላይ ሲወጣ ሚያዚያ 2 እንጂ 3 አይወጣም፡፡

የሆሳዕና ተውሳክ 2፤2 እና 17 ሲደመር 19 ይሆናል፡፡ ወደታች ሲወረድ መጋቢት 19 እንጂ 18ን አይነካም 2፤ እና 21 ሲገጥሙት 23 ይሆናል፡፡ ወደ ላይ ሲወጣ ሚያዚያ 23 እንጂ 24 አይወጣም የስቅለት ተውሳክ 7፤7 እና 17 ሲደመር 24

ይሆናል። ወደታች ሲወርድ መጋቢት 24 እንጂ 23 አይነካም 7 እና 21 ሲጋጠሙት 28 ይሆናል። ወደ ላይ ሲወጣ ሚያዚያ 28 እንጂ 29 አይወጣም። የትንሣኤ ተውሳክ 9፤9 እና 17 ሲደመርበት 26 ወደታች ሲወርድ መጋቢት 26 እንጂ 25 አይነካም። 9 እና 21 ሲገጥሙት 30 ወደ ላይ ሲወጣ ሚያዚያ 30 እንጂ ግንቦትን አይነካም።

የረክበ ካህናት ተውሳክ 3 ነው። 3 እና 17 ቢደምሩት 20 ይሆናል። ወደ ታች ሚያዚያ 20 እና 19 አይነካም፤ 3 እና 21 ቢገጥሙት 24 ይሆናል። ወደ ላይ ሲወጣ ግንቦት 24 እንጂ 25 አይነካም። የዕርገት ተውሳክ 18፣ 18 እና 17 ሲደመርበት 35 ይሆናል። 30ውን ገድፎ 5 ይተርፋል። ወደ ታች ሲወርድ ግንቦት 5 እንጂ 4 አይነካም 18 እና 21 ሲገጥሙት 39 ይሆናል። 30ውን ገድፎ 9 ይተርፋል። ወደ ላይ ሲወጣ ሰኔ 9 እንጂ 10ን አይነካም።

የጰራቅሊጦስ ተውሳክ 28 ነው። 28 እና 17 ሲገጥሙት 45 ይሆናል። 30ውን ገድፎ 15 ይተርፋል። ወደ ታች ሲወርድ ሰኔ 15 እንጂ 14 አይነካም። 28 እና 21 ሲገጥሙት 49 ይሆናል። 30ውን ገድፎ 19 ይተርፋል። ወደ ላይ ሲወጣ ሰኔ 19 እንጂ 20 አይነካም፤ ጾመ ሐዋርያት ከዚያ ቀጥሎ ነው።

የምሕላ ጾም ተውሳክ 1 ናት። 1 እና 17 ሲደመሩ 18 ይሆናል። ወደ ታች ሲወርድ ግንቦት 18 እንጂ 17 አይነካም፤ 1 እና 21 ሲገጥሙት 22 ይሆናል። ወደ ላይ ሲወጣ ሰኔ 22 እንጂ 23 አይነካም።

የዕለታት ተውሳክ በቅዳሜ ጀምሮ በዓርብ ያበቃል። የቅዳሜ 8፤ የእሁድ 7፤ የሰኞ 6፤ የማክሰኞ 5፤ የረቡዕ 4፤ የኀሙስ 3፤ የዓርብ 2።

እኒህ ሲሰበስቧቸው 35 ይሆናሉ። ከምን ተገኙ ቢሉ ከአዕጋረ ፀሐይ ይሏል። አዕጋረ ፀሐይ ስንት ናቸው ቢሉ 2100። ከ1000 ውስጥ 100 አቆይቶ 15 ኬክሮስ አሁንም ከ1000 ውስጥ 100 አቆይቶ 15 ኬክሮስ በድምሩ 30 ኬክሮስ 3000 ይሆናል። ከ3000 3 ኬክሮስ ሲያነሱ 3፤ 40 ይቀራል። ከ40 እና 40 መደብ አንዱን 40 ሲያካፍሉት 35 ኬክሮስ ይገኛል ከዚህ ተገኙ ነው።

የአጽዋማት ተውሳክ ሲሰበስቧቸው 94 ይሆናሉ እነዚህ ከምን ተገኙ ቢሉ ከአውታረ ፀሐይ ይሏል። አውታረ ፀሐይ ስንት ናቸው ቢሉ 5640 ናቸው እነዚህን ሲመዱባቸው 94 ኬክሮስ ይሆናሉ። ከዚህ ተገኙ።

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ኅመተ ወንጌላውያንን ለማወቅ 7499 ዓመታትን በ4፤በ4 መመደብ ነው። 1 ስታተርፍ ማቴዎስ፤ 2 ማርቆስ፤ 3 ሉቃስ፤ ትክክል ሲሆን ዮሐንስ ይሆናል፤ ይህንን ስንደረጀው በ7499 ስናካፍለው 1874 ደርሷቸው 3 ይተርፋል። ዘመነ ሉቃስ መሆኑ በዚሁ ይታወቃል። መጠነ ራብዒት ጳጉሜን 5ኛ መደብ ሆና ትቀርባለች ይህንን በ 7 በ 7 ሲገድፉት ጥንተዮን ትገኛለች።

አሁን ስንገድፈው 6 ነው የሚተርፈው። 6 ጥንተዮን ከዚህ ተገኘ። 2 አጽፈ አውራኅ፤ 1፤ መዓልት 6 ጥንተዮን ሲደምሩት 9 ይሆናል። 7 ሲገድፉት 2 ይተርፋል። ዛሬ ዕለቱ ሰኞ መሆኑ በዚህ ይታወቃል።

እንዲህ በየወሩ አጽፈ አውራኅን እየደመሩ ዕለታትን ማግኘት ይቻላል። ማውጣት ይቻላል።

አዕማድ የሚባሉ፤ አዕማድ የሚሆኑ፤ አዕማድ የሚያሰኙ 42 ናቸው። ማን ማን ናቸው ቢሉ 19 መጥቅዕ፤ 11 አበቅቴ 30። 5 ጳጉሜን፤ 6 ሕፀፅ 41። 1 ጥንተዮን 42 ይሆናሉ። ከምን ተገኙ? ከ5000፤ 2 ከ2000-40 ተገኝቷል። ስለምን ከብዙው ጥቂት፤ ከጥቂቱ ብዙ እንዲገኝ አደረገ ቢሉ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ5 ገበስ እንጀራ፤ በ2 ዓሣ፤ 5000 ሕዝብ አጥግቦ 12 ሌማት መሶብ ተርፎ ተነሥቷል።

ዳግመኛም በአንድ ዓሣ፤ በ7 ገበስ እንጀራ 7000 ሰዎች አጥግቦ 7 ሌማት (መሶብ) ተርፎ ተነሥቷል።

መዋዕለ ዓለምን ለማወቅ፤ መዋዕለ ዓለምስ ነገር እንደምን ነው? የመዋዕለ ዓለም ነገር እንደምን ነው ቢሉ ይህ ዓለም 7980 ዘመን ሲደርስ ይህ ዓለም ያልፋል። ይጠፋል። ይህንንም ሲደረጁት በ19 ሲገድፉት 7980፤ 19 ይተርፋል። «አሐደ አትት ለዘመን» ብሎ የሚገኘው 18 ወንበር ነው። መስከረም የሚውለው ማክሰኞ ነው። ዘመኑ ዮሐንስ ነው። ከ18 ወንበር 11/11 አበቅቴ፤ 19/19 መጥቅዕ አንሥቶ ሲገድፉት አበቅቴ 18 መጥቅዕ 12 ይገኛል። 1 ሕፀፅ፤ 1 ዕለት 20 ሌሊት በዚያን ጊዜ አደረ ማለት ነው። መስከረም 1 ቀን መጥቅዕ 12 ስለሆነ በጥቅምት ይወድቃል።

መስከረም የባተው ማክሰኞ ስለሆነ ጥቅምት ኀሙስ ነው እስከ ኀሙስ 8፤ ዓርብ 9፤ ቅዳሜ 10፤ እሁድ 11 ሰኞ 12 ጥቅምት 12 የሚከሌል ዕለተ መጥቅዕ ወደቀ የሰኞ ተውሳክ 6፤ 6፤ እና 12፤ 18 መባጃ ሐመር ተገኘ። የነነዌ ሳኒታውን አይለቅም። ዓርብ እስከ ዓርብ 8፤ 15፤ ቅዳሜ 16፤ እሑድ 17፤ ሰኞ 18 ጾመ ነነዌ የካቲት 18 ቀን ይውላል።

ዐቢይ ጾም (ጾመ ኢየሱስ) ተውሳክ 14፤ 14 እና 18 ሲገጥሙት 32 ይሆናል። 30ውን ገድፎ 2 ይይዟል። መጋቢት እሁድ ይብታል። ሰኞ 2፤ መጋቢት 2 ጾመ ኢየሱስ ይገባል። የደብረ ዘይት ተውሳክ 11፤ 11 እና 18 ሲገጥሙ 29 ይሆናል። የመጋቢት በዓለ እግዚአብሔር፤ በዘመነ ዮሐንስ ደብረ ዘይት ይውላል። ያንጊዜ ይህ ዓለም ተለውጦ፤ ይህ ዓለም ጠፍቶ «አልቦ ወርኅ ወኢፀሐይ፤ ኢክረምት ወኢሐጋይ» ይሆናል።

ክረምትና ሐጋይ፤ ሌሊትና መዓልቅ መፈራረቅ ያቆማል። ያንጊዜ ኑ የአባቴ ቡሩካን በጎቹ ብሎ ይሰበስባል፤ ፍየሎቹን ያርቃል።

ያድነን፤ ይሰውረን ከመዓቱ በእንተ ማርያም ወላዲቱ ወስብሐት ለእግዚአብሔር በምድር ሰላም ይሁን ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይግባው።

# አባሪ-2

## የኮኘት ቤተ ክርስቲያን ትረካ

ስለ ሊቀ ጳጳስ ድሜጥሮስ ታሪክ የኮኘት ቤተክርስቲያን ትረካ የሚከተለው ነው።

### (ሀ) የወይን አትክልት ባለቤት

ዐስራ ሁለተኛው የእስክንድርያ ሊቀጳጳስ አባ ድሜጥሮስ ቀዳማዊ ንጹህ ድንግል የሥጋን ምኞትና የተፈጥሮን ባሕርይ ድል ያደረገ ታላቅ አባት ነበር። ጥቅምት 12 ቀን 224 ዓ.ም አረፈ።

የዐስራ አንደኛው የእስክንድርያ ሊቀጳጳስ የቅዱስ ዩልያኖስ ዕረፍት በተቃረበ ጊዜ የጌታ መልአክ በራዕይ ተገለጸለትና ስለ ቅዱስ ድሜጥሮስ ነገር ነገረው። ከርሱ በኋላ ፓትርያርክ ሊሆን የሚገባው እርሱ እንደሆነም ሲያስረዳው ምልክት ሰጠው።

በመኘታው ሳለ መልአኩ «ነገ የወይን ዘለላን የያዘ አንድ ሰው ወደ አንተ ይመጣልና እርሱን ይዘህ ጸሎት አድርግለት» አለው። ያን ጊዜ ቅዱስ ዩልያኖስ ከእንቅልፉ ነቃና ከርሱ ጋር ለነበሩት ጳጳሳትና ካህናት ራዕዩን ነገራቸው።

በሚቀጥለው ቀንም እንዲህ ሆነ። ቅዱስ ድሜጥሮስ ያለጊዜው ያፈራ የወይን ዘለላን አግኝቶ ቡራኬን ለመቀበል ወደ ቅዱስ ዩልያኖስ ይዞት መጣ። ያን ጊዜ ፓትርያርኩ እርሱን በእጁ ይዞ «ከእኔ በኋላ የናንተ ፓትርያርክ ሊሆን የሚገባው ይህ ነው»ብሎ ከርሱ ጋር ለነበሩት ነገራቸው። ያን ጊዜ ጸሎት አደረገለትና ሊጳስ ቆጶሳቱ ይዘውት ሄደው እስከ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ እረፍት ድረስ ስርዓተ ጸሎቱን በሚፈጸመበት ቦታ አቆዩት። ድሜጥሮስም በሰማያዊ ጸጋ ተሞላ ጌታም አእምሮውን አበራለትና ማንበብና መጻፍን አውቆ የቤተክርስቲያን መጻሕፍትንና ትርጓሜያቸውን አጠና። በሚያስተምርበት ጊዜም ጸጋ የተሞላበት ቃል በረከት ከአንደበቱ ይፈልቅ ጀመረ።

### (ለ) የሐሳበ አበቅቴ መስራች

አጽዋማትና በዓላት የሚውሉባቸው ዕለታት በማይናወጥ መሠረት ላይ ጸንተው እንዲኖሩ የሚወሰንበት ሐሳበ አበቅቴን ያዘጋጀ ዲሜጥሮስ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ አርባውን ቀን እንደጾመ ክርስቲያኖችም በዓለ ጥምቀቱን

ካከበሩ በኋላ ወዲያውኑ አርባውን ቀን ከጾመ በኋላ ቆይተው ጾመ ህማማትን በተለይ ይጾሙ ነበር፡፡ ክርስቲያኖቹ ሚያዚያ(ኒሳን) በ14ተ በዐስራ አራተኛው ቀን ትንሣኤን ከአይሁድ ጋር ባንድነት ያከበሩ ነበር፡፡ እንዲህም ያደረጉት የክርስቲያን ፋሲካ ከሙሴ ፋሲካ በኋላ የሚውል፣ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ መታሰቢያ እንደሆነ ስላልተረዱ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ድሜጥሮስ ለአጽዋማትና ለክርስቲያን ቅዱሳት በዓላት የማይናወጽ መሠረት እንዲኖራቸው ለማድረግ እጅግ ተጠንቅቆ ዓቢይ ጾምንም ከሰሙነ ህማማት ጋር አገናኝቶ ሠራው፡፡

ድሜጥሮስ ይህን የጾም ቀጥር አዋጅ ለኢየሩሳሌሙ ጳጳስ ኢጋቢዮስ ለአንጾኪያው ፓትርያርክ ማክሲመስ፣ ለሮም ፓትርያርክ፣ ለኤፌሶንና ለሌሎችም ጽፎ ላከ፡፡ ሁሉም ተቀብለው አጸደቁ፡፡

ከዐስራ ስድስተኛው መቶ ዘመን ጀምሮ ሐሳብዋን ከለወጠችና የጎርጎርዮስ ሐሳበ ዘመን ከተከተለች ከሮም ቤተክርስቲያን በቀር እስከ ዛሬ ድረስ የድሜጥሮስን ህግ ተከትለው ይሠራሉ፡፡ በዚያን ዘመን የትንሳኤን ቀን ለመወሰን ታላቅ ኀላፊነት የተሰጠው ለእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት በመሆኑ ፍጹም ደስታን የሚሰጥ ትንሳኤን ክርስቲያኖች ባንድ ቀን ያከብሩት ዘንድ ወደ ዓለሙ ሁሉ የትንሣኤን በዓል መልዕክት ይልክ ነበር፡፡

(ሐ) ንጽሕናው

ከንጽሐ ልቡናው የተነሳ እግዚአብሔር በቅዱስ ድሜጥሮስ ላይ አድሮበት ኖረ፡፡ ጸሎተ ቅዳሴውን ከፈጸመና ሕዝብም ቅዱሳት ምስጢራትን ለመቀበል ፊት ለፊት ከቀረቡ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚገባቸውን ሰዎች በእጁ ይዞ ወደ እርሱ ሲያቀርብ ማየት የሚችልበትን ጸጋ ለርሱ ተሰጥቶት ነበር፡፡

ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል የማይገባው ሰው ቢቀርብ ግን ኃጢአተኛ መሆኑም ስለሚገለጽለት ቁርባኑን እንዲቀበል አይፈቀድለትም፡፡ ይህም ከልክላ ምእመኑ ኃጢአቱን አውቆ ንስሐ እስኪገባ ካህኑም ይቅርታ አድርጎለት «ከኃጢአትህ ተመለስ፤ ንስሐም ግባ ከዚያ በኋላ ቅዱሳት ምስጢራትን መጥተህ ትቀበላለህ» እስኪለው ድረስ ነው፡፡ በዘመኑም የርሱ ምእመናን የጸኑ ነበሩ፡፡

ኀጢአተኞችን እጅግ ይገስጻቸውና ንጹሕ ሕይወትንም ለመምራት ነሰሐ እንዲገቡ ያጽናናቸው ስለ ነበር ከእርሱ ወገን «ይህ ሰው ያገባ ነው እኛን እንዴት ሊገስጸን ይችላል» ብለው አጉረመረሙ፡፡

ኃያሉ ጌታም የርሱን ንጽሕና ያሳያቸው ዘንድ ፈቀደ። ስለዚህ የጌታ መልአክ በሌሊት ወደ እርሱ መጥቶ እንዲህ አለው።

«ድሜጥሮስ ሆይ የራስህን ደኅንነት አትሻ፤ ሌሎችንም በመጠራጠራቸው እንዲጠፉ አታድርግ» አለው። አባታችንም ነገሩን እንዲያብራራለት መልአኩን ጠየቀው፤ መልአኩም እንዲህ ሲል ነገሩን ቀጠለ «ከእነርሱ መጠራጠርን ታርቅ ዘንድ ባንተ በራስህና በሚስትህ መካካከል ያለውን ምስጢር ለሕዝቡ መግለጽ ይገባሃል።»

በሚቀጥለው ቀን ጥዋት ጸሎተ ቅዳሴን ካደረሰ በኋላ ሕዝቡን ከቤተክርስቲያን እንዳይወጡ አዘዛቸው። ድሜጥሮስ የጋለውን ከሰል (የእሳት ፍህም) አንስቶ በባለቤቱ የራስ መሸፈኛ መጎናጸፊያ ልብስና በራሱ ልብስ ላይ አስቀመጠው። ከዚያ በኋላ በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ (ዐውደ ምሕረት) ዞሩ፤ ልብሶቻቸውም ምንም አልተቃጠሉም። ህዝቡም በዚህ ተአምራት ተደነቁ። እርሱም እስከ ዛሬ ድረስ እርሱና ባለቤቱ እንደተጋቡ ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው እንዳልተዋወቁ ነገራቸው። የአባቱ የወንድም ልጅ መሆኗንና ወላጆቿ መሞታቸውን ከአረማውያን እርሷን ለመጠበቅ ከአባቷ ቤት አብረው ማደጋቸውን ገለጸላቸው። መጠራጠር ከሕዝቡ ተወገደና የዚህ አባትና የድንግል ባለቤቱን ንጽሕናን ተረዱ።

በጽጽስናው ዘመንም በኦርቶዶክስ እምነት የሚያምኑትን ማስተማርና ማጽናናትን አላቋረጠም። በሸመገለና በደከም ጊዜም ህዝቡን ያስተምር ዘንድ በቃሬዛ (በአልጋ) ተሸክመው ወደ ቤተክርስቲያን በሚወስዱበት ጊዜ የአንድ መቶ አምስት ዓምት አረጋዊ ነበር። ከዚሁም ሳያገባ ዐስራ አምስት ዓመት፣ ፓትርያርክ እስኪሆን ድረስ አርባ ሰባት ዓመት፣ በአገልግሎት አርባ ሦስት ዓመት አሳልፎ በሰላምና በፍቅር አረፈ። ጸሎቱና በረከቱ ከኛ ጋር ይኑር፣ በሰዎች ላይም ይደር። ለዘለዓለም አሜን።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# መረጃ አቀባዮች

| ተ. ቁ. | ስም | ዕድሜ | ሙያ | አድራሻ |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| 1 | አለቃ ያሬድ ፈንታ | 85 | የባሕረ ሐሳብና የግእዝ መምህር | አዲስ አበባ |
| 2 | ሊቀ ሥዩማን ራደ አስረስ | 68 | የሊቃውንት ጉባዔ ዋና ፀሐፊ | አዲስ አበባ |
| 3 | መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ | 60 | የሊቃውንት ጉባዔ አባል | አዲስ አበባ |
| 4 | ሊቀ ጠበብት ጥበብ ይኄይስ | 49 | የማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን መምህር | አዲስ አበባ |

# የባሕረ ሐሳብ እወጃ ፎክሎርነት

በ

ሔኖክ ያሬድ ፈንታ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዶክተር አባ ዳንኤል አሰፋ ______________
አማካሪ ፊርማ

አቶ ዘሪሁን አስፋው ______________
የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

ዶክተር ዮናስ አድማሱ ______________
የውጭ ፈታኝ ፊርማ